# ልጅነት
## ተመልሶ አይመጣም

በእምነት ገ/አምላክ



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ልጅነት
# ተመልሶ አይመጣም

በእምነት ገብረ አምላክ

አዲስ አበባ
፲፱፻፺፱ ዓ.ም

መብት የደራሲው ነው።
፩ኛ እትም

ከዚሁ ደራሲ የተዘጋጁ-
በዓለም ካለው ሁሉ ትልቁ ነገር (ትርጉም)።
የአንድ ቋንቋ እድገት ወይም አማርኛ እንደ ተስፋፋ።
የልጆች ሁኔታ በቤትና በትምህርት ቤት (ትርጉም)

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# ማውጫ፤

ይህስ ዱብ እዳ ነው። ........................................................................5
ድሮና ዘንድሮ።...........................................................................................9
የንጋት ኮከብ ቀኖች። ..............................................................................14
መበታተን። ..............................................................................................17
የጽሕፈት ሥራ። ........................................................................................22
በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። ................................................................31
የአዲሱ ሕይወት ጣዕም። .........................................................................36
የትምህርት ትርጉም። ...............................................................................40
ጉዞ ወደ ፈረንጅ አገር። ............................................................................43
በአዲሱ ዓለም .........................................................................................52
የወዲያ ወሬ.............................................................................................55
ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም።............................................................56
በፍቅር መነደፍ .........................................................................................60
እንቅፋት ..................................................................................................65
ቆርቆሮና ሰንበሌጥ....................................................................................73
የዘሩትን ማጨድ የአልኮል ጠንቅ.................................................................76
የአጋጣሚ ጉዳይ። ......................................................................................81
ስለደራሲው በጥቂቱ ...................................................................................89

# ለኢትዮጵያ አርበኞች መታሰቢያ።

ሞት አይቀርም ስም አይቀበርም።

## እውነት ነፃ ታወጣችሁአለች።

# ምዕራፍ አንድ።

# ይህስ ዱብ እዳ ነው።

ትላንት ማታ እንደ ወትሮው በቤቱ ደጃፍ ተቀምጬ ጥዋት ከሰፈር ወጥቶ ሲሰማራ የተመለከትሁትን ሰውና እንስሳ እንደ ገና ወደየቤቱ ሲመለስ አስተውል ነበር። የልጅ ልጆቼም ከትምህርት ቤት ተመለሱና በተቀመጥኩበት ክብብ አድርገውኝ ፤ እንደ ልማዳቸው ተረት እንድነግራቸው ይወትውቱኝ ጀመር። ማምለጥ የማይቻለኝ መሆኑን ተገንዝቤ ፈቃዳቸውን ለመሙላት ተነሣሁና ፤ ብርድ ጀማምሮ ስለነበረ ፤ ተሰብበን ወደ ቤት ገብተን በእሳቱ ዙሪያ ተቀመጥ። «ተረት ተረት የላም በረት የጦጢትን ብልጠት ፤ አህያን ደደብነት ፤ የቀበሮን ተንኰል ፤ የበግን ሞኝነት፥ የአንበሳን ወንድነት ፤ የሚያሞግሡት የማውቃቸውን ተረቶች ሁሉ ነግሬ አብቅቼ እንኳ ነበረ። የኔ የተረት ጎተራ ማለቁ ሲሆን፥ ግን ልጆቹ አይጠረቁ ፤ እንዲያውም ባሰባቸው እንጂ። ተረቱ ተሟጥጦ በቸገረኝ ጊዜም ልጆቹን እንደምን እንደማስተናግድ ሳወጣና ሳወርድ ፤ «እንደ እነ እርሱ ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በእኩያዎቼ ጋር እንሠራ የነበረውን ብነግራቸውሳ ይቀበሉኝ ይሆን?» የሚል ሃሳብ በአእምሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ።

በእኛ ልጅነት ጊዜ ትምህርት በሌለበት ቀን ማለዳ ተነሥተን ኳስ ፤ ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፤ ብይ ፤ ቆርኬ ፤ ስንጫወት እናረፋፍድና ይኸው ሲሰለቸን የላስቲክ ወንጭፋችንን ይዘን በኪሳችን ጠጠር ሞልተን ወፍና አሞራ አደን መሄድ ልማዳችን ነበረ። የምንገድላቸው ወፎች ለምን እንደሚረቡን አንዲት ጊዜ ስንኳ አስበን አናውቅም ነበረ። ታዲያ የአደኑ ምክንያት ወፎች የሰጠ ማነጣጠሪያ ዒላማ በመሆናቸው ብቻ ይሆን? ለሁሉም ነገር ዓርፈው ከሚንጫጩበት ዛፍ ወይም ምግብ ፍለጋ ጉንብስ ጉንብስ ሲሉ ፤ ወይም ድንጋይ ላይ ቁጢጥ ብለው አፋቸውን ሲያብሱ ፤ ብቻ ይገኙ እንጂ። የጠጠር ናዳ እያወርድን ፤ «እግሬ አውጭኝ» ስናሰኛቸው እንውል ነበረ። እግር ጥሎት ባጠገባችን የሚያልፍ ውሻም የፍቅራችን ልክ በድንጋይና በቅዝምዝም ሳይገለጽለት አይቀርም ነበረ። አንዳንድ የፈረዴብት ወፍ ተመትቶ ማምለጥ አቅቶት አባርረን በያዝነው ጊዜ ፤ ያች የመታችውን ጠጠር ያስሸተቱት እንደሆነ እንደሚያድን የሚል ባህል በእኛ ዘንድ ስለ ነበረ ወፉ በወደቀበት አቅራቢያ የሚገኘውን ጠጠር ሁሉ እየሰበሰብን ብናስሸትት እንኳ ፤ ሕክምናችን አስደሳች ውጤት አያገኝም ነበረ። ከአድን ምላሽ ሲሆንም ፤ አጥር አጠገብ የሚገኝ የኮክ መሳይ ዛፍ ያለበት አጥር ግቢ እኛ ወፎቹን እንደምናባርራቸው ሁሉ እኛንም እንደዚሁ የሚትያባርረን እስኪ መጣ ድረስ በረጅም ፤ ዘንግ ወይም በድንጋይ ሳንጐበኘው አናልፍም ነበረ። ፍሬው ምንም ጮርቃ ቢሆን እንኳ ፤ እንጃ አንድ ልዩ ጣዕም ነበረው! የሌላ ሰፈር ልጅም ድንበር ጥሶ ከሰፈራችን ክልል ውስጥ ቢገኝ ከእኛ አንዳችን ጠጋ ብሎ በእጁና በአፉ ለኮፍ ያደርገውና ፤ «እባክህን አንተ ልጅ በጉልበትህ አምላክ» በማለት ድሉን ለኛ ትቶ ሕይወቱን ካላተረፈ በቀር ወዮለት እንደቂሪላ ይለዋላ!

ታዲያ በልጅነቴ ጊዜ በትምህርት ቤት ስንማረው የነበረውን ለልጅ ልጆቼ ብዘረዝርላቸው ሲሰሙት ግድ የላቸው ፤ እነርሱ የሚፈልጉት ከላይ የጠቀስኩትን ዓይነት ታሪክ ነው። ይህን የሽፍትነት ታሪክ አሰምቻቸው ዝም ብል ደግሞ ዱካችንን ሊከተሉ መፈለጋቸው አይቀርም። ሥራችን አንዳንዴ አለንጋ ያስከትልብን እንደነበረ ነግሬ ባስጠንቅቃቸውም «መች እንደ እናንተ ምኞት ሆንንና ፤ እኛ ሰው ሳያየን ነው የምናደርገውና አንያዝም» ማለታቸው አይጠረጠርም።

መላው ጠፍቶ በሐሳብ ባሕር ተውጬ መውጫዬን ስሻ ከልጅ ልጆቼ አንዱ አሰፋ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ፤ ወርቅ በመሬት ወድቆ እንዳገኘ ሰው በደስታ እንጣጥ እንጣጥ ይል ጀመረ። እኛም «ምን አግኝቶ ይሆን?» ብለን ዓይን ዓይኑን ስናይ ቃሉን ቁርጥ ቁርጥ እያደረገ እንዲህ ብሎ ይጠይቀኝ ጀመረ? «አባባ ፤ ትልቁ እንደ ገና እንድናነበው ቢጽፉልን እንዴት ደስ ይለናል!» አየ ጉድ ዕዳው የኔው ኑራል ከቶ ወንድሞቼና እህቶቼም የአሰፋን ነገር እንደሰሙ «አዎን ጻፉልን» እያሉ ባንድ ቃል ይንጫጩብኝ ጀመረ። ታሪኩን በቃል ስነግራቸው ነገሬ ሳይሳካና አሳምሬ ሳላስረዳቸው ስቀር እንደገና እንድነግራቸው በጠየቁኝ መልሼ አስተካክዬ እነግራቸው ነበረ። እረ በጽሕፈት ሲሆን ምን በጀኝ፥ ልጅ ደግሞ እንዴ ነግረውት አይሰማ። በጽሕፈት ሲሆን ስሕተት የማይፈቀድ መሆኑን ይልቁንም መጽሐፍ እንደሆነ አንድ ጊዜ ከታተመ በኋላ መልሶ ማረም አለመቻሉን ላስረዳቸው ብል ሊገባቸው ነው? መልሳቸው አሁንም «ይጻፉልን፥ ይጻፉልን» ብቻ ነበረ። በወጣትነቴ ጊዜ የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርት አሠልጣኝ እንደነበርኩ፥ ዕድሜዬ ገፍቶ ሰውነቴ ጠና ባለ ጊዜም የተማሪዎች መጋቢ ስለነበርኩ የአጻጻፍን ጥበብ መከታተል ተግባሬ እንዳልነበረና ብጽፍም ንባቡ እንዳይስለቻቸው የምሰጋ መሆኔን ብገልጽላቸው ሊቀበሉ ነው? እንዲያውም ይህን ማለቴ አሳሰባቸውና አሁንም አንድ ላይ «ጻፉልን» እያሉ ጩኸታቸውን ቀጠሉ።

ጥንቱንም ጽሑፍ የምወድ ብሆን ኑሮ የሰዋሰውና የድርሰት መምህር እሆን እንደነበረ፥ ነገር ግን ስላልወደድኩት የጅምናስቲክ አስተማሪነትን እንደመረጥሁና አሁን «ጻፍ» እያሉ ሲያስቸግሩኝ፥ ባልሠለጠንሁበት ሞያ ገብቼ ስፈተፍት «የሰው መሳቂያ ታደርጉኛላችሁ» ብላቸው ጊዜ ምንም ፍንክች የለችም፥ «ጻፉልን» ብቻ። የማይቀርልኝ መሆኑን በተረዳሁ ጊዜ፥ የተሰጠኝን ሥራ በግዴ ተቀብዬ ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ጀመርኩ።

የሕይወቴ ታሪክ ባጭሩ ይህ ነው። ዕድሜዬ ኻያ አንድ ዓመት በሆነ ጊዜ፥ ትምህርቴን ፈጽሜ፥ ከፍ ብሎ እንዳመለከትኩት የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርት አሠልጣኝነት ዲፕሎማ ተቀብልኩ። ወደ አምሳው ዘመን እስከጠጋ ድረስም በአዲስ አበባና በሌሎች አውራጃዎች ወደ ልዩ ልዩ ትምህርት ቤት እየተዘዋወርኩ ይህንኑ ጅምናስቲክ አስተማርኩ። ከትምህርት ቤቶቹ መካከል በርከት ያሉ ዓመታት የቆየሁበት ግን የንጋት ኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበረ። ሰውነቴ ጠና ባለ ጊዜም ይህን ሥራ ትቼ በተማሪዎች መጋቢነት ኻያ ዓመት ሙሉ በነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሠራሁ ፡ እንግዲህ አሁን ይህን ታሪክ የምጽፈው በሰባ አድነኛው ዘመኔ መሆኑ ነው።



ገጽ 7 ትምህርት ቤቱ በቅዱስ ገብርኤል .......

ዕድሜዬን በሙሉው ያሳለፍኩት ቀድሞ ተማሪ ሆኜ፥ በኋላም በአስተማሪነት ከተማሪዎች ጋር ነው። ከአብሮ አደጎቼ ተማሪዎች ጋርም በመካከላችን «ምሥጢር» የሚባል ነገር ጨርሶ አይታወቅም ነበረ። ያንዳችን የግል ጉዳይ የሁላችን ነበረ። ያንዱ ልጅ አሳብ ደግሞ ቁም ነገር ሆነ አልሆነ የማኅበር ነበረ። በእየቀኑ ሕይወታችን የገጠመንና ያሰብነው ቀርቶ ባደግን ጊዜ ልናደርግ ያቀድነውን ሳይቀር እንደ ዕለት አጣዳፊ ጉዳይ እንመክርበት ነበረ።

ከተማሪዎቹ ጋርም በመካከላችን መግባባት ስለ ነበረ እክል ሲገጥማቸው መጥተው ያወያዩኝ ነበረ። «ተማሪ ደግሞ ምን ችግር አለበት?» ብለው የሚያስቡ ሰዎች ቢኖሩም፥ ይህን ጽሑፍ ዘልቀው እስኪያነቡ ድረስ ቢታገሡ፥ ሁሉን ከዚያው ያገኙታል።) ከሥራ ጓደኞቼ ከአስተማሪዎች ጋርም ማናቸውንም ጨዋታ እንጀምርና ጥቂት እንደቆየን ንግግራችን ወደ ኑሮ ጓደኞቻችን ወደ ተማሪዎች ነገር ሸርተት ብሎ፥ ወጋችን ዞሮ ዞሮ መጨረሻው ያው የተማሪዎች ጉዳይ ይሆናል። በነዚህ በአምሳ የሥራ ዓመታት ውስጥምከ ተማሪዎቼ ወላጆች ከብዙዎቹ ጋር ተዋወቅሁና በልጆቻቸው በኩል ስለሚገጥማቸው ችግር በአያሌው ያማክሩኝ ነበረ። አሁን ታዲያ እኒህ ነገር የማይገኝባቸው የልጅ ልጆቼ የልጅነቴን ጊዜ ታሪክ እንድጽፍላቸው ብለው አናስወጣ አናስገባ ሲሉኝ ጊዜ ከንዝናዜው እንዳርፍ ላደርገው የሚሻለኝን ሳወጣና ሳወርድ፥ በሕይወት ጐዳና አብረን የተጓዝነውን

የአንዳንድ ተማሪዎች የሕይወት ታሪክ ፍሬ ፍሬውን ከመጻፍ የተሻለ ሌላ አሳብ ስላልተገለጸልኝ ይህን ጽሑፍ በማዘጋጀት ቆረጥሁ።

እነሀ ታሪካቸው የሚጻፈው ወጣቶችም በግል ሕይወታቸው ውስጥ ገብቼ ገመናቸውን በመግለጼ በጽሞናና በስውር ያጫአወቱኝን፥ ወይም ለኔ ሳይታሰብ ጆሮዬ የቃረመውን፥ እንደዚሁም በሐሜትና በሹክሹክታ የሰማሁትን አደባባይ አውጭቼ በይፋ ስነጋገርበት እንዳይቀየሙኝ እለምናቸዋለሁ። ሆኖም፥ ምሥጢራቸው በመገለጹ የተሰማቸው ሐዘን ታሪካቸው ለዘላለም በመመዝገቡና የልጅ ልጆቼ ሲያነቡት በሚሰማቸው ደስታ እንዲካስ ተስፋ አደርጋለሁ።

አብሮ አደጎቼም የማኅበር ምሥጢራችንን ስላወጣሁ መሐላዬን በማፍረሴ፥ የሚቻል ቢሆን ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናቸዋለሁ። «ያን የድሮ ሕጋችንን ንቀን ነወይ ፤ ምን ቸገረኝ ብለህ ነው መሐላውን የረገጥኸው?» ብለው ቢከሱኝም፥ «ሕጉንም አልረሳሁም፥ የሥራሁትን ወንጀል ከባድነት እገነዘባለሁ» እያልኩ ለመከላከያ የማቀርበው ክርክርም ጨርሶ የለኝምና በዚያ ባወጣነው ሕግ መሠረት ቅጣቴ ተነግሮኝ ፍርዱን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ። ነገር ግን እነዚያ ሊፈርዱብኝ ችሎት ላይ የሚቀመጡት ዳኞች የኔን የሚመስል ወንጀል ሳይሠሩ አልቀሩምና አስቀድሞ እንዲመረመሩልኝ እለምናለሁ» እላቸውአለሁ።

ይህ ጽሑፍ በስሕተት በእጃቸው ገብቶ የሚመለከቱት ወላጆችም የቤተ ሰባቸውን የጓዳ ምሥጢር እንደዚህ አዝረክርኬ ሲያዩ ራሳቸውን ይዘው «አየ ጉድ እግዜር ይይልህ፥ አሁንስ እውነትም ስምንተኛው ሺ ደርሶአል ፤ እንዲህ ያለ ጉድ ከዚህ ቀደም ታይቶም ተሰምቶ አያውቅ» እያሉ ሲተክዙብኝ ይታየኛል። የወንዶቹስ እንኳ እንደሻው፥ ሴቶቹ ግን ዕንባው እንቅ እንቅ እያደረጋቸው ፤ አፍንጫቸውንም ወዲያው እንድጽፍላቸው ብለው አናስወጣ አናስገባ ሲሉኝ ጊዜ ከንዝናዜው እንዳርፍ ላደርገው የሚሻለኝን ሳወጣና፥ ሳወርድ፥ በሕይወት ጐዳና አብረን የተጓዝነውን የአንዳንድ ተማሪዎች የሕይወት ታሪክ ፍሬ ፍሬውን ከመጻፍ የተሻለ ሌላ አሳብ ስላልተገለጸልኝ ይህን ጽሑፍ በማዘጋጀት ቆረጥሁ።

እነሀ ታሪካቸው የሚጻፈው ወጣቶችም በግል ሕይወታቸው ውስጥ ገብቼ ገመናቸውን በመግለጼ በጽሞናና በስውር ያጫወቱኝን፥ ወይም ለኔ ሳይታሰብ ጆሮዬ የቃረመውን፥ እንደዚሁም በሐሜትና በሹክሹክታ የሰማሁትን አደባባይ አውጥቼ በይፋ ስነጋገርበት እንዳይቀየሙኝ እለምናቸዋለሁ። ሆኖም፥ ምሥጢራቸው በመግለጹ የተሰማቸው ሐዘን፥ ታሪካቸው ለዘላለም በመመዝገቡና የልጅ ልጆቼ ሲያነቡት በሚሰማቸው ደስታ እንዲካስ ተስፋ አደርጋለሁ።

አብሮ አደጎቼም የማኅበር ምሥሪራችንን ስላወጣሁ መሐላዬን በማፍረሴ፥ የሚቻል ቢሆን ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናቸዋለሁ። «ያን የድሮ ሕጋችንን ንቀህ ነወይ ፤ ምን ቸገረኝ ብለህ ነው መሐላውን የረገጥኸው?» ብለው ቢከሱኝም፥ «ሕጉንም አልረሳሁም፥ የሥራሁትን ወንጀል ከባድነት እገነዘባለሁ» እያልኩ ለመከላከያ የማቀርበው ክርክርም ጨርሶ የለኝምና በዚያ ባወጣነው ሕግ መሠረት ቅጣቴ ተነግሮኝ ፍርዱን ለመቀበል ዝግጁ

ነኝ። ነገር ግን እነዚያ ሊፈርዱብኝ ችሎት ላይ የሚቀመጡት ዳኞቼ የኔን የሚመስል ወንጀል ሳይሠሩ አልቀሩምና አስቀድሞ እንዲመረምሩልኝ እለምናለሁ» አላቸውአለሁ።

ይህ ጽሑፍ በስሕተት በእጃቸው ገብቶ የሚመለከቱት ወላጆችም የቤተ ሰባቸውን የጓዳ ምሥጢር እንደዚህ አዝረክርኬ ሲያዩ ራሳቸውን ይዘው «አየ ጉድ እግዜር ይይልህ፥ አሁንስ እውነትም ስምንተኛው ሺ ደርሶአል ፤ እንዲህ ያለ ጉድ ከዚህ ቀደም ታይቶም ተሰምቶም አያውቅ» እያሉ ሲተክዙብኝ ይታየኛል። የወንዶቹስ እንኳ እንዳሻው፥ ሴቶቹ ግን ዕንባው እንቅ እንቅ እያደረጋቸው ፤ አፍንጫቸውንም ወዲያው ወዲያው እየጠረጉ እየተንሰቀሰቁ የነገሩኝን ምሥጢር በማውጣቴ የሚሰማኝ ሐዘን የምሬቱን መጠን ልገልጽ ያዳግተኛል። እንደምን ቀና ብዬ ፊታቸውን አያለሁ? መቼም ከእንግዲህ ወዲህ የኔው መሳይ ዘርዛራ ካልሆነ በቀር ሰው ብሎ የሚያነጋግረኝ ማግኘቴን እንጃ። ወደ ምሽቱ አቅራቢያ ምድሩ ቀዝቀዝ ሲል በሰፈራችን ንፋስ ለመቀበል የምዘዋወረውን ልምዴን ትቼ የሰውን ዓይን በመፍራት ከቤቴ ምሽግ ሳልወጣ የልጅነቴን ጊዜ ታሪክ ስጽፍ የተረፈውን ዕድሜዬን መፍጀቴ ነው

## ምዕራፍ ሁለት።

# ድሮና ዘንድሮ።

ብርሃኑ ማለዳ ተነሥቶ የጽዳት ተግባሩን አከናውኖ ቁርሱን በላና ጓደኞቹን ከጐረቤት ተጣርቶ አብረው ወደ ትምህርት ቤታቸው ጉዞ ጀመሩ። አባቱ ያሰፉለትን አዲሱ ኮቱንና ቦለሌ ሱሪውን ለብሶ፥ ከቁመቱ ምንም ያህል የማያንሰውን ፊደለ ሐዋርያውን በእጁ ይዞ ጎርደድ ፤ ጎርደድ ሲልም፥ ከሩቅ ለተመለከተው ክንድ እንጂ ትንሽ ልጅ አይመስልም ነበረ። ልጆቹ መንገድ ለመንገድ ለመንገድ እየተላፉ ትምህርት ቤታቸው ወደሚገኝበት አጥር ግቢ በጊዜ ደረሱና በአካቢው የሚገኙትን ትልልቅ የዋንዛና የወይራ ዛፎች አልፈው ወደ ክፍላቸው በቀጥታ ገቡ። ትምህርት ቤቱ በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ፥ አለቃ ክንፈ የአበሻ ትምህርት የሚያስተምሩበት፥ በሕዝብ ዘንድ «የቄስ ተማሪ ቤት» እየተባሉ ከታወቁት ከጥንት ጀምሮ የዘመናቱን ሕጻናት በአገር ትምህርት እያሠለጠኑ ለቤተ ክህነትና ለጽሕፈት ሥራ ከሚያደርሱ፥ የአገር ልማድ እንዳይረሳ ባለ አደራዎች ከሆኑቱ ዓይነተኞች ብሔራዊ ትምህርት ቤቶች አንዱ ነበረ። ቤቱ የብዙ ትውልዶች ልጆች ያገለገለ መሆኑንም ከሁኔታው በጉልሁ ለመረዳት ይቻላል። ብርቱ ምሰሶዎች ባይደግፉት ኑሮ ካሁን ካሁን ይወድቃል የሚያሰኝ፥ ወደ ፀሐይ መውጫ ያዘመመ አንድ ትልቅ ጥድ ጥላ የሚጥልበት ነባር ቤት ነበር። ሌላ የማርጀቱ ምልክት እልፍ እልፍ ብሎ ልስኑ ተልጦ ግድግዳው ይታያል።

እነ ብርሃኑ ገቡና በእየስፍራቸው ቁመው ሁሉም አብረው ጸሎታቸውን ደግመው እንዳበቁ ትምህርታቸውን ጀመሩ። አርባ የሚያህሉ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተሰባጥረው በግድግዳው ዙሪያ ተቀምጠዋል። የሚማሩበትን ትጥቅ ስንመለከትም አንዳንዶቹ የፊደል

ሐዋርያን ስሌዳ፥ ገሚሶቹ የታተሙ መጻሕፍት የቀሩትን ግን የጥንቱን የብራና መጻሕፍት የያዙ መሆናቸውን እናያለን። አለቃ ክንፈም በትንንሾቹ ተማሪዎች መካከል በወንበር ላይ ጉብ ብለው ሲታዩ፥ በጫጩቶችዋ የተከበበችን ዶሮ ይመስሉ ነበረ። ጠና ባለው ሰውነታቸው ላይ ኮስታራው ግንባራቸውና አረጋዊ ጢማቸው ሲጨመርበት፥ ግርማቸው ለልጅ ቀርቶ ለዓዋቂም ይከብዳል። ልጆቹ ገሚሶቹ ፊደል ይቆጥራሉ ገሚሶቹ ወንጌል በአማርኛ ሲያነቡ፥ የቀሩት ደግሞ ዳዊታቸውን በግዕዝ ይደግሙ ነበረ። የትምህርት ጣዕም ገና ያልታወቃቸው አንዳንዶቹ ጀማሪዎችም ቃናው ወደ ለቅሶ ያዘነበለ ድምፅ እያሰሙ፥ ሁሉም ጉሮሮአቸው የሚፈቅድላቸውን ያህል እየጮኹ ሲያጠኑ፥ እንደ ልጆቹ ዕድሜና የድምፅ ሕዋሳት አፈጣጠር ልውጥውጥ የሆነው ድምፅ አንድ ላይ ሲሰማ በትልቅ ወርካ ላይ ሰፍረው የሚንጫጩትን ወፎች ይመስል ነበረ። ደግነቱ፥ እዚህ ሁሉ ጫጫታ መካከል አለቃ ክንፈ በፀጥታ ተቀምጠው ጨኸት ራስ ምታት እንኳ ሳያስነሣባቸው እያንዳንዱ ተማሪ የሚሠራውን ለመከታተልና ለመምራት ይችላሉ።

ስድስት ሰዓት የጥዋቱ ትምህርት ተፈጸመ። የብርሃኑ አባት አቶ ዓባይም ከሥራ ወደ ቤት ሲመለሱ በእግረ መንገዳቸው ልጃቸውን ለመውሰድ ወደ ትምህርት ቤቱ ጎራ ሲሉ ከአለቃ ክንፈ ጋር በግቢው በር አጠገብ ተገናኙ።

«ጤና ይስጥልኝ አለቃ ክንፈ፥ እንዴት ሰነበቱ»? አሉ አቶ አባይ።

«እግዚአብሔር ይመሥገን፥ እንደምን ሰንብተዋል?» ብለው መለሱ አለቃ ክንፈ።

«እንኳን አገኘሁዎ፥» አሉ አቶ አባይ «ስለ ልጄ ብርሃኑ ትምህርት ጉዳይ ልጠይቅዎ ስፈልግ መገናኘታችን በጀ፥ እባክዎን ልጁ በትምህርቱ እንዴት ነው?

«በርትቶአል ፤ ብርሃኑ ጎበዝ ልጅ ነች! አሁንማ ፊደሉን ከልሶ ወደ መልእክተ ዮሐንስ ተሻግሮአል፥ እንግዴህሳ ግዕዙንም መጀመሩ ነው» አሉ አለቃ ክንፈ።

አቶ አባይ ይህን እንደ ሰሙ በሐሳብ ተውጠው ጥቂት ጊዜ ዝም አሉና - «እህ፥ ነገርን ነገር ያመጣዋል፥ አሁን አንድ ነገር ትውስ አለኝ፥ እረ ካሉሳ ይህ አንድ ፍሬ ሕፃን - ባለፈው ጥቅምት ፲፯ ቀን አምስት ዓመት ሞልቶት አሁን ስድስተኛውን ይዞአል - ገና ፊደሉን ከመቀጥሩ ከማያስተውለው ቋንቋ ጋራ ትንቅንቅ ሲጀምር ፤ ነገሩ ሳይገባው ሲደግም የሚረባው ይመስልዎታል ወይ? የአማርኛን ፊደል እንኳ አሳምሮ አላጣራም። ባይሆን ወደ አሥሩና ወደ አሥራ ሁለቱ ዓመት ተጠግቶ አእምሮው ረጋ እስኪል ድረስ በዚያው ባደገበት ቋንቋ ቢማርና አእምሮው ሲጐለምስ ግዕዙን ቢጀምር የሚሻል አይመስልዎትምን?» አሉ አቶ አባይ።

«ሰሙ አቶ አባይ» አሉ አለቃ ክንፈ፥ «እኛ መቸም እግዚአብሔር የሰጠንን ከጥንት ከአባቶቻችን ከቅድም አያቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣልንን ግዕዝን ማስተማር አለብን እንጂ እንደምን ልንለውጠው እንችላለን? ለውጠን ብንገኝሳ ከሐድያን መሆናችን አይድሌም ወይ? ደግሞ ግዕዙን ትተን ዘመናዊውን ቋንቋ ብቻ ስናስተምር ግዕዙ ተረስቶ መቅረቱ ነው እኮ።»

«ክሕደት እዚህ ውስጥ ምን አገባው?» አሉ አቶ አባይ ከራቫታቸውን እያስተካከሉ ፤ «አማርኛ ቢሆንሳ የአባቶቻችን ቋንቋ አይደለም እንዴ? አባቶቻችን ያቆዩልንን ማክበር እንዳለብን ግልጽ ነው ፤ ይህን ማድረጋችን ግን ዘመናዊውን ማስናቅ የለበትም። የድሮ የሆነ ነገር ሁሉ በደፈናው ጥሩ ፤ ዘመን የወለደው የሆነው ፤ ሁሉ ደግሞ በደፈናው መጥፎ እንደ ሆነ ለማለት አንችልም። እኛም በዚህ ባሮጌው ጠባብ አስተያየት ታጥረን ከምንቀር ይልቅ ፤ ለሰው ልጅ በየጊዜው በሚገለጽለት አዲስ ጥበብ እየተሻሻልን ዘመናዊ ቋንቋችንን እያስፋፋን ወደ ፊት መራመድ የሚገባን ይመስለኛል። ለምሳሌ ፤ አንድ ልጅ በቤቱ ወላጆቹ በመሩት ፤ በትምህርት ቤት በሥለጠነውና በሕይወቱ በደረሰበትና በሌላውም ሰው ላይ ሲደርስ በተመለከተው ሁኔታ ሁሉ እየተመከረ ፤ ዕድሜው በገፋው መጠን ልብ እያበጀ ይሄዳል እንጂ ዘወትር ጥሬ ሕፃን ሁኖ አይቀርም። እንደዚሁ ባምሳያውም አንድ ሕዝብ ወይም ጎሣ ባለፈው ታሪኩና ከቀረው ዓለም ግንኙነት እያደረገ በሚቀስመው ጥበብ ፤ እየተመከረ ከዘመኑ ጋር እኩል ወደ ፊት ይራመዳል እንጂ አዲሱን ንቆ የጥንቱን ብቻ ይዞ እንደ ኩሬ ውኃ መተኛት የለበትም።»

«የኛ ሰው እኮ» አሉ አለቃ ክንፈ ጢማቸውን እያጫወቱና ራሳቸውን እየነቀነቁ ፤ «የባዕድን ነገር ማስገባት ሲጀምር ነው አጥራችን ተጥሶ አገራችን በጠላት የሚደፈረው። ስለዚህ አባቶቻችን ያቆዩልንን ብቻ አጠንክረን ይዘን የባዕድ ከሆነ ከማንኛቸውም ነገር ጨርሰን መወሰን ይገባናል» ብለው ሲያበቁ ጭራቸውን፥ ከትከሻቸው አንሥተው ቀኝ ግራ ይነሰንሳሉ።

እነኚህ ሁለት ሰዎች አገራችው አንድ፥ ዕድሜአቸውም ተቀራራቢ ሲሆን፥ አስተያየታቸው እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ መሆን የሚገርም ነው እኮ! ለአለቃ ክንፈ አልታያቸውም እንጂ፥ አቶ አባይ ያባቶቻቸውን አክባሪ መሆናቸውን ልጃቸውን «ቄስ ተማሪ ቤት» ማስገባታቸው ይመሰክርላቸዋል። ነገር ግን ባገራቸው ትምህርት ላይ የምዕራባውያን ትምህርት ጨረፍታ የቀመሱ በመሆናቸው ፤ አስተያየታቸው ከዚያ ከወትሮው ይበልጥ ሰፋ ያለ አድማስ ይሻ ነበረ። በነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል ያለው ልዩነትም የአስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የአለባበስም ጭምር ነበረ። አለቃ ክንፈ በአዘቦት ቀን የሚለብሱትን ጥንታዊ እጀ ጠባብና ሹራብ ቅድ ሡሬ ሲሆን፥ አደባባይ ሲወጡና በዓውደ ዓመት ዕለት ሸማውም በጃኖ ተለውጦ ሰማያዊ ከባቸውም ወይም በርኖሳቸውን ይደርቡበታል። ነጭ ጭራ ከጃቸው ተለይቶ አያውቅም። ከተወለዱበት ቀን አንስቶ እግራቸውን ጫማ (እርሳቸውም እንደሚሉት መጫሚያ) ጢማቸውንም ምላጭ የሚባል ዘመን አመጣሽ ኮተት ነክቶት ባለማወቁም ይመካሉ። አቶ አባይ ግን የዚህ የተባለው ሁሉ አንጻር ናቸው። ባለባበስ ከሆንስ ከፈረንጅ ያሳስታሉ። ኮትና ሰፊ ሡሬ ለብሰው፥ ከራቫት ማተብ በሸሚዛቸው አንገት አሥረው፥ ለዐይናቸውም መነጽር አድርገውለታል። በአለቃ ክንፈ ጢም ፈንታም ሪዛቸውን ነጋጠባ ሙልጭ አድርገው እየላጩት ጠጉር በቅሎበት የሚያውቅ አይመስልም።

«ይህን ፤ ጨዋታ እንዲህ በቁመናችን የምንፈጀው አይደለንም» አሉ አቶ አባይ። «የምሳ ሰዓትም ደርሶአል። እግዚአብሔር በፈቀደው ዕለት ቁጭ ብለን ጠላችንን እየጠጣን እስከ ዘለቄታው ዕለት ቁጭ ብለን ጠላችንን እየጠጣን እስከ ዘለቄታው ድረስ እንነጋገርበታለን እንጂ።?

«ይህማ የተሻለ ነው የሥላሴዎች ፈቃድ ይሁን» አሉ አለቃ ክንፈ ፤ «እንግዴህ ጠላውም ከወደ አናንተ ነው፥ የጎዳሩ አቦም ተቃርቦአል።»?

*   *   *

ብርሃኑና ሦስት ጓደኞቹ በአለቃ ክንፈ ትምህርት ቤት ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ተምረው ሲያበቁ ወደ «ንጋት ኮከብ» አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዛወሩ። አምስተኛቸው ይኄይስ የተባለው የአለቃ ክንፈ የወንድም ልጅ ግን በዲቁና ለመቀጠል እዚያው ቀረ።



ገጽ ፱ ስሙ አቶ አባይ >> አሉ አለቃ ክንፈ

## ምዕራፍ ሦስት።

# የንጋት ኮከብ ቀኖች።

የንጋት ኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሕንፃው ማማር የተመልካችን ዓይን ሁል ጊዜ እንደማረከ ነው። ከኮተቤ ጥርብ ድንጋይ የተሠራ ግርማማ ሞላላ ፎቅ ቤት ሆኖ የምድር ቤቱ የትምህርት ክፍሎችን ሲይዝ ደርቡ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ናቸው። በምድረ ግቢው እልፍ እልፍ ብለውም ተጨማሪዎቹ የትምህርት ክፍሎችና የአገልግሎት ቤቶች፥ የተማሪዎች የመኝታ ቤቶችና የመምህራን መኖሪያ ቤቶች ይገኛሉ። የአዳሪዎችንና ተመላላሾችን ቀላቅሎ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ዘጠኝ መቶ ልጆች ይማራሉ። «ዛሬ ማን ያሸንፍ ይሆን» ብሎ ብርሃኑ ዓለሙን ጠየቀው። ከነርሱ እልፍ ብለውም ቸኮልና መኰሪያ ጐን ለጐን ተቀምጠው ጨዋታውን ይመለከቱ ነበረ። (እኒህ አራቱ ልጆች በንጋት ኮከብ ትምህርት ቤት አዳሪዎች ሁነው፥ በአምስተኛ ክፍል አንድ ላይ ይማራሉ።) የአንደኛው ትምህርት ቤት ልጆች በጨዋታቸው ቅልጥፍናና በኳስ አቀባበል ዘዴአቸው የሚያሸንፉ ቢመስሉ እንኳ፥ መካቾቹ የንጋት ኮከብ ቡድን ገትረው ይከላከሉ ስለነበረ፥ በአዲሱ ዓመት በተደረገው በዚህ የመጀመሪያ ጊዜ ግጥሚያ አሸናፊ ሳይኖር ሁለት ለሁለት ተለያዩ። እኩል ለእኩል መለያየታቸውም የግጥሚያው መደምደሚያ የሚሆን ጭፋሮ መሳይ እንዲጫወቱ አልፈቀደላቸውም።

እነ ብርሃኑም የቡድናቸውን ሞያ አሞጋግሠው ተወዳዳሪዎቻቸውንም አኮስሰው፥ ከኳስ ሜዳው እልፍ ብሎ በካቡ አቅራቢያ ወደ ሚገኘው ጥድ አመሩ። ከጥላው ውስጥ ገሚሶቹ ተኝተው፥ የቀሩት ደግሞ ቁጭ ብለው መጻሕፍታቸውን ዘረጉና ያጠኑ ጀመር። ጊዜው፥ መስከረም ወደ ማለቁ ሲል ነው። የንጋት ኮከብ ትምህርት ቤት ከተሠራበት ተረተር ወደ ምሥራቅ ሲመለከቱ አደይ አበባው ዓይን እስከሚደርስበት ድረስ አገሩን ብጫ ቀልሞታል። አጥኚዎቹ በሚገኙበት ለምለም መስክ ዙሪያም ይኸው አበባ ከቦአቸው ትንሽ ነፋስ ሽው ሲል መዓዛው አፍንጫቸውን ይሰነፍጠው ነበረ። ልጆቹ አንዳንድ ጊዜ ጥናታቸውን አቋርጠው ሲነጋገሩ ላዳመጣቸው ሰው ባደጉ ጊዜ ስለሚፈጽሙት ሥራ ሐሳባቸውን በምኞት ሜዳ ስድ እየለቀቁት መስማቱ ደስ ይላል። ዛሬ አንዳቸው ሐኪም ሆኖ ስለሚሠራው ድንቅ ሕክምና ሲያወራላቸው አንዱ ደግሞ መሐዲስ ሁኖ ስለሚመሠርተው ሕንፃ ይናገራል። ነገር ግን እነዚሁኑ ልጆቹ በሳምንቱ ስንሰማቸው ሥራቸውን ለዋውጠው መሐዲሱ ደራሲ ሆኖ ይገኛል። ታዲያ ሐሳባቸው ሲረጋጋ መስማት አይሻልም ወይ? ልጆቹ ሁሉ የለበሱት የደንቡን አጭር እጅጌ ኮትና ቁምጣ ሡሬ ጥቃቅን ነገር የቤታቸው ሁኔታ ሊገመት ከሚቻለው በቀር ሁሉም አንድ ይመስሉ ነበረ።

«ይ አበባ ምነው ለዘለዓለም ሳይረግፍ እንዲሁ እንደ አማረበት በቀረ» አለ ቸኮል።

«አበባ ካልረገፈ እኮ ፍሬ አይገኝም» ብሎ መለሰ ብርሃኑ።

በተቀመጡበት ሁነው ከአድማሱ አቅራቢያ ትንሽ ትንሽ የሚታየውን የዝቋላን ተራራ ሲያስተውል የቸኮል ሐሳብ ሕፃንነቱን በደስታ ወደ አሳለፈበት ወደ ቤቱ ተመለሰ።

መንደሩ ወንዙ ሸንተረሩ ፤ ያ ገና የሚጫወቱበት ለጥ ያለው ሜዳ ፤ ያ ትግል የሚገጥሙበት ለምለሙ መስክ እየታየው የአገሩና የዘመዶቹ ናፍቆት ልቡን ሞላው። አገሩ ከአዲስ አበባ በባቡርና በመኪና የሦስት ቀን መንገድ ነው። አባቱም በልጅነታቸው ለጌታ አድረው ዕድሜአቸውን በወታደርነት የፈጁትና አሁን በርሥታቸው ላይ የሚቀመጡት ሽማግሌው አቶ ከበደ ናቸው። ቸኮል ሁለተኛው ልጃቸው ሁኖ፥ ቁመቱ ዘለግ ያለ፥ አቋቋሙ የቀና ሰውነቱ ሙሉ ባለ ብስል መልክ ነበረ።

አጭር ከረጅም ጋር መጐዳኘቱ ይገርማል። ፈጣሪ ይህን ማድረጉ ረጃጅሞችና አጫጭሮች ወገን እየለዩ እንዳይተላለቁ አስቦ ይሆን? ከቸኮል የማይለይ ጓደኛው መኩሪያ ነበረ። እንደተመለከትነው ሁሉ፥ ቸኮል ሁለተኛው ልጃቸው ሁኖ፥ ቁመቱ ዘለግ ያለ፥ አቋቋሙ የቀና ሰውነቱ ሙሉ ባለ ብስል መልክ ነበረ።

አጭር ከረጅም ጋር መጐዳኘቱ ይገርማል። ፈጣሪ ይህን ማድረጉ ረጃጅሞችና አጫጭሮች ወገን እየለዩ እንዳይተላለቁ አስቦ ይሆን? ከቸኮል የማይለይ ጓደኛው መኩሪያ ነበረ። እንደተመለከትነው ሁሉ፥ ቸኮል ቁመታም ሲሆን፥ መኵሪያ አጭርና ወፍራም ነበረ። ሰውነቱም እንደ ጠገበ ስልቻ ጥቅጥቅ ስለነበረ ጓደኞቹ «ዱባ» ብለው የቅጥል ስም አውጥተውለት፥ ይህንን ስሙን ግን በጣም አይወደውም ነበረና ሲጠሩት ከትልቁም ከትንሹም ጋር ይኳረፍ ነበረ። የሠፈሩ ሕፃናት ሳይቀሩ እንኳ ይህን ስሙን አጥንተውት መኵሪያ በሚያልፍበት ጊዜ አፈር መፍጨታቸውን አቋርጠው ራቅ ሲልላቸው «ዱባ መሬት ቀዶ ገባ» ብለው ሲሾፉት ደስ አይለውም ነበረ። እግሮቹን ፈርከክ አድርጎ ይቆምና «እስቲ ማ ወንድ ነው የሚይዘኝ?» ብሎ ሲፎክር፥ ያም ያም እየመጣ የሚቻለውን ያህል ከንዱን ጥብቅ አድርጎ ቢይዘው እንኳ፥ መኵሪያ ሆየ ሁሉንም ምንጭቅ አድርጎ እያንገዳገደ ያሽቀነጥራቸዋል። የመኵሪያ አባት ዛሬ በዳር አገር አንድ አውራጃ የሚገዙት ስመ ጥሩው ደጃዝማች በላይ ናቸው።

የአንደኛው ጓድ አባሎች ደግሞ ብርሃኑና ዓለሙ ናቸው። ብርሃኑ እንኳ እህል በልቶ የሚያውቅና ከሐኪም ቤት በቅርብ ቀን የወጣ ገመምተኛ የሚመስል ሰውነተ መጣጣ ልጅ ነበረ። ይኸው ክሳቱም ቅላቱ ላይ መገርጣትን ጨምሮበት ፤ ጓደኞቹ ከስሙ ይልቅ «ዓረብ» ብለው ይጠሩታል። ልብሱም አይቀበለው የተውሶ የለበሰ ያስመስለዋል እንጂ። የብርሃኑ አባት አቶ አባይ ከኢትዮጵያ ከሰሜን አውራጃዎች ከአንዱ የመጡ ዕድሜአቸውን በሙሉው በኪራይ ቤት የኖሩ የማተሚያ ቤት ሠራተኛ ናቸው። ከብርሃኑ በቀር ብዙዎቹ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወልደዋል። የመንፈሳቸው ዝንባሌና የሥራቸው ዓይነት መጻሕፍት የማንበብ ፍቅር ስለ አሳደረባቸውም፥ በአዋቂነታቸውና የአገራቸውን ታሪክ መመርመር የሚወዱ በመሆናቸው፥ በእኩያዎቻቸው ዘንድ የታፈሩ ሰው ነበሩ።

አገረ ስላም ከተማ ነዋሪ የሆነ ሰው የዓለሙን አባት ከበርቴው ነጋዴ አቶ ሰብስቤን የማያውቅ አይገኝም። አንድ ቀን የገንዘባቸውን ልክ ለማወቅ ፈልገው ብራቸን መቁጠር ጀመሩና አሥራ አምስት ቀን ሙሉ ቆጥረው ቢደክማቸው ጊዜ ሳይጨርሱ ተዉት እየተባለ አንድ ሰሞን በመንደሩ ይወራ ነበረ። ዓለሙም ካንዲት እህቱ ጋር ብቻ የዚህ ሁሉ ሲሳይ ወራሽ ነው።

* * *

ልጆቹ በጥዱ ጥላ ሥር ሁነው ሲያጠኑ መሸና ራታቸውን ሊበሉ ወደ መብል ቤት ተነሥተው ሄዱ። ከራት በኋላም በቤተ መጻሕፍቱ ሲያጠኑ አመሹና እንደ ልማዳቸው በምኝታ ቤታቸው በረንዳ ሸማቸውን ተከናንበው ተጠጋግተው ተቀምጠው «ተረት፥ ተረት ፤ የላም በረት» እያሉ ይጫወቱ ጀመሩ። ተረቱም አስፈሪ በሆነው መጠን ይመሠገን ስለ ነበረ ባለተራው የሚያሰማው ተረት ከቀድሞዎቹ በልጦ ጠጉር የሚያስቆም እንዲሆንለት የተቻለውን ያህል ይጣጣር ስለ ነበረ፥ አብዛኛውን ጊዜ ሙከራው ይከናውን ነበረ። ታዲያ ጨለማው ሲደፋፈንና የማናቸውም ነገር ጥላና ጉቶው ያደፈጠ ጠላት በሚመስልበት ሰዓት እኒህ ዕድሜአቸው ከአሥርና ከአሥራ ሁለት ዓመት የማይበልጥ ልጆች በለጋው አእምሮአቸው የእነ አባ ድቡልቡሌን የእነ አያ ጅቦ ሰው በላን፥ የቡዳ፥ የጭራቅና እነዚህን የመሳሰሉ የሚዘገንኑ ተረቶች ሰንቀው ወደ አልጋቸው ሲሄዱ፥ ምን ዓይነት እንቅልፍ እንደሚተኙ የታወቀ ነው። ሌሊቱን ሲባንኑ የሚያድሩት ልጆች ብዛት ስፍር ቍጥር የለውም። ይልቁንም ብርሃኑ አእምሮው ንቁ ስለ ነበረ፥ ማታ የሰማው ሁሉ በሕልሙ እየመጣበት «በላኝ በላኝ» እያለ ቤቱ እስኪነቃነቅ ድረስ በመንፈቀ ሌሊት እየጮኸ፥ በክፍሉ የተኙትን የእርሱ ብጤዎች እየቀሰቀሰ ሞግዚቱ መልሰው ሲያስተኙት አሣር መከራቸውን ሲያዩ ያድሩ ነበረ። አንድ ሌሊት እንደዚሁ ከወትሮው የባሰ ሲባንን አደረና፥ እንደማይነጋ የለም፥ ጥዋት ሞግዚቱ ጠርተው ሲመረምሩት ጊዜ በዋዜማው ማታ ብዙ ተረት ሲያዳምጥ እንዳመሸ ነገራቸው። ከተረቶቹ አንዱን እንዲያሰማቸው ብለውት፥ ብርሃኑ እንደደገመው ተረቱ ይህ ነው፡-

«አንድ ቀን ሊመስ ሲል አንድ ጭራቅ ወደ አንድ መንደር መጥቶ፥ ብዙዎች ልጆች ወዳሉአት አንዲት ሴትዮ ቤት ሰተት ብሎ ገባና «በሩቅ አገር የምቀመጥ አጎትሽ ነኝ» ብሎ አሞኛት። የሴትዮዋ ባል ወደ ሩቅ መንደር ለንግድ ሄዶ ነበረ። ጭራቁም፥ ማን እንደነገረው እንጃ፥ ይህን ያውቃል። የማጅራቱ ዓይኖች እንዳይታዩበት ራሱን በሻድሽ ግጥም አድርጎ አሥሮት ቄስ ይመስላል። ሴትዮዋም የእውነት አጎትዋ መስሎአት በደስታ ተቀበለችውና ጥሩ እራት አብልታ ጐዝጉዛ አንጥፋ አስተኛችው እርሱም ልጆቹ ናፍቀውኛልና ከኔ ጋር ይተኙ አላት። እርስዋም ሞኝዋ፥ ልጅጆቹን ሁሉ ከእርሱ ጋር አስተኛቻቸው። ሌሊት እንዳይርበኝ ጥቂት ጥሬ ባቄላ ከራስጌዬ አኑሪልኝ አላትና አደረገችለት። ጭራቅ ሆዬ መንፈቀ ሌሊት ሲሆን እንቅልፍ ሲወስዳቸውና ቀስ ብሎ አንድ በአንድ ቅርጭም አያደረገ ይበላቸው ጀመራ! አጥንታቸውን እየቆረጣጠመ ሲያላምጥ ሰምታ ሴትዮዋ «አጎቴ ምን ይበላሉ?» ብላ ስትጠይቀው «ያን ያቀረብሽልኝን ባቄላ ነው ልጄ» እያለ ልጆቹን ሁሉ ጭርስ አድርጎ በላና ሌሊት ሰው ሳያየው ተነሥቶ እብስ አለ! ሴትዮዋ ጥዋት ተነሥታ ብታይ አጎትዋ የለም ልጆቹ የሉም። በመሶበ ወርቁ ያቀረበችለት ባቄላ ጨርሶ አልተነካም። የልጆቹ ልብስ ብቻ አውልቀው ካስቀመጡበት ነበረ። ቁርበቱም በደም ተጨማልቆ ተበላሽቶአል።»

ብርሃኑ ይህን ተረት ሲተርት ዓይኖቹ ተጕልጉግለው ጅማቶቹ ተገትረው ትንፋሹን ቁርጥ ቁርጥ እያደረገ ነበረና ተረቱ በሕፃን አእምሮ ላይ ምን ስሜት ቀርጾ እንደ ነበረ

ለመገመት አዳጋች አልነበረም። ሞግዚቱም ተረቱን አዳምጠው እንዳበቁ «አይ የልጅ ነገር ምነው ለጥናቱ ጊዜ እንዲህ አትበረቱ! ለመሆኑ ማን አህያው ነው ይህን ተረት የነገረህ? ለእርሱሳ ማን አህያዩቱ እናት ወይም ሞግዚት ነግራው ይሆን? ጥንትስ ይህን ተረት የፈለሰፈው ማን ይሆን የተሻለ ተረት ጠፍቶ ነውን?» ካሉ በኋላ አጥፊው ተጠራና ለወደፊት የዚህ መሳይ ተረት ቢናገር ብርቱ ቅጣት የሚደርስበት መሆኑን በቁጣ ቃል ነግረው ጭራቅ የሚባል ነገር አለመኖሩን የሚገልጽ ትንሽ ዲስኩር መሳይ አደረጉና ልጅጆቹን አሰናበቱ።

## ምዕራፍ አራት።

# መበታተን።

ክረምት ከገባ ሰንብቶአል ፤ ዝናሙም ቲፍ እያለ ሲወርድ ለመቸም የሚያባራ አይመስልም። አንዳንድ ጊዜም በዝናሙ ፈንታ ለለውጥ እያለ ነፋስ፥ ዝናምና በረዶ ተቀይጦ ነጐድጓዱ እያጎራ፥ መብረቁ ሰማዩን እየሰነጠቀ ውሽንፍሩ ሲወርድ፥ የባሕር ዛፎች ቅጠላቸውን እያረገፉ፥ መሸሸጊያ አጥተው ባሉበት ሁነው በፍርሃት የሚርበደበዱ ይመላሉ። ብርዱ ከቤት ቀርቶ እንዲያውም ከአልጋ ሙቀት ውጣ አያሰኝም ከሰው አፍ የሚወጣው ትንፋሽ ጢስ ይመስላል። የድሮ ሰው «እግዜር የተቆጣው በዝናም መጣው» ብሎ የተረተው ይህን በመሰለ ቀን ሳይሆን አይቀርም። ወሩ ሐምሌ ነው። የሚቻል በሆነ፥ ሁሉ የብርድ ልብሱን ተከናንቦ በቤቱ ቢውል ባልጠላ፥ ነገር ግን ተኝቶ መብላት በሕይወት ሕግ መጽሐፍ ውስጥ የማይገኝ አንቀጽ በመሆኑ፥ ዝናሙ ፋታ ሲሰጠው ትልቁም ትንሹም ያለውን ልብስ ደረብረብ አድርጎ ከወትሮው ትንሽ ወፈር ብሎ እየታየ፥ አቀርቅሮ ወደ እየፊናው ውር ውር ሲል ይታያል። ቆፈን ያልያዘው ሰው የት ተገኝቶ! በዚህ ወራት ተማሪም ቢሆን ከብርዱ አያመልጥም። ደግነቱ ትምህርት ቤት መዘጊያው ተቃርቦአል። ደብተርና መጽሐፍ በተቀመጠበት ተረስቶ ለጥቂት ወራት የአቧራና የሸረሪት ጓደኛ መሆኑ ላይቀርለት ነው። እስከ መጭው ሞቃቱ የመስከረም ወር ድረስም ተማሪ ሁሉ በየቤቱ ሆኖ ከብርዱ ለማምለጥ ተስፋ አለው። ከእውጪ አገር ወደዚህ ከተማ የመጡት ልጆችም ወደሚናፍቁአቸው ዘመዶቻቸው የሚሄዱበትን ጊዜ ተስፋ ፍጻሜ በመጠባበቅ ልባቸውን ደስታ ሞልቶታል።

ጊዜው እንደሚያልፍ ነገር ሳይታወቃቸው የዓመቱ ትምህርት ተፈጽሞአል። የንጋቱ ኮከብ ትምህርት ቤት ልጆችም ሰሞኑን ሲፈተኑ ሰንብተው፥ እንግዴህ ትምህርት ቤታቸው መዘጋቱ ነው። ቀዳሚነት ያገኙት ዕድለኞች ልጆችም ለድካማቸው የሚገባቸውን ወረታ ሽልማት ሲወስዱ ብርሃኑም በክፍሉ በላጭነት ስላገኘ ከሚሸለሙት ልጆች መካከል ነበረ። ይልቁንም ሽልማቱን የሚቀበሉት ከገናናው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እጅ ስለ ሆነ ፤ ደስታው ዕጥፍ ነበረ። የስምንት ዓመት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተፈጸመ። ባለፈውና በቀደሞዎቹ ሰባት ዓመታት ውስጥ ከተማሪዎቻችን እያንዳንዱ የሠራው ሥራ ውጤት ታየ። ወደ ሁለትኛ ደረጃ ወይም ወደ ልዩ ትምህርት ቤቶች መሻገር ወይም ወደ ኋላ መቅረት

የሚለይበት የፍርድ ጊዜ ደረሰ። ትምህርታቸውን በትጋት ሲከታተሉ የነበሩት ጎበዞቹ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርትና ወደ ዩኒቨርስቲዎች ገብተው ጥናታቸውን ለማዝለቅ፥ ወደ ማዕርግና ትልቅ እንጀራ የሚያደርሳቸውን ትምህርት መርጠው ለመማር ተስፋ ሲኖራቸው፥ እነዚያ ወላጆቻቸውን እያሞኙ ትምህርት ቤት የሄዱ አስመስለው ቀኑን ሙሉ ኳስ እና ብይ እየተጫወቱ፥ ወይም ጥርስ ነክሶ ጨክኖ በማጥናት ፈንታ ተመልሶ የማይመጣውን ውድ ጊዜአቸውን በዋዛና በፈዛዛ፥ በቀልድና በቧልት ሲያሳልፉት የነበሩት መጋጣዎች ለዘላለም ወደ ኋላ መቅረታቸው ነው። ጓደኞች በነበሩት መካከል የማያገናኝ መለያ ግንብ ተፈጥሮ ፤ ምንም አብሮ አደግ ቢሆኑ እንኳ ሊረሳሱ ነው። ቸኰልም ጨዋታ ወዳድ ስለ ነበረ፥ ዕጣው ወደ ኋላ ከሚቀሩት ልጆች ጋራ እንዳይሆን ያሰጋዋል።

ተማሪዎቻችን ፈተናቸውን እንዳጠናቀቁ ከሰኞ ጀምረው የሰውነት ጥንካሬና ቅልጥፍና የሚያሳይ ልዩ ልዩ ጅምናስቲክ ሲያሳዩ ሰነበቱ። በትምህርት ቤቶች መካከል በሚደረገው ዓመታዊ የእግር ኳስ ውድድርም ሁለተኛነትን የማግኘት ዕድል ገጠማቸው። ዛሬ ጥዋት የምስክር ወረቀት የመስጠት ሥነ ሥርዓት ሲፈጸም አረፈደና የመጨረሻው ክፍል ተማሪዎች የስምንት ዓመት ሥራ ፍሬ የሚታይበትና የሚለያዩበት የመጨረሻው ትምህርት ቤት ቀን ስለ ሆነ ፤ በልጆቹ ግንባር ላይ ትርጉም ይህ ነው ለማለቱ የሚያዳግት የፍርሃት፥ የደስታና የኃዘን መልክ አንድ ላይ ሁኖ ተሥሎ ይታይ ነበረ። ከሰዓት በኋላም የአማርኛ አስተማሪው አለቃ ገብረ ሥላሴ ያሰናዱትን ትያትር ለማሳየት ብዙዎች ተማሪዎች ለዚሁ ሲዘጋጁ ሽር ጉድ ይሉ ነበር።

ትያትሩ በዘጠኝ ተጀመረ። ትርኢቱን ለማየት የተማሪዎቹ ወላጆችና ቤተ ዘመድ፥ የአገር ጨዋና ወይዛዝርት የክት ሸማቸውን ለብሰው መጥተው የስብሰባውን አዳራሽ ጢቅ እስኪል ድረስ ሞልተውታል። የትያትሩ አርእስት «የወጣት የወደፊት እርምጃ» የሚል ሆኖ በወደፊት ሕይወቱ ተማሪን የሚጠብቀው ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነበረ። የትርኢቱ ፍሬ ነገርና የተማሪዎቹ ቀልጣፋ አሠራር ተመልካቾቹን ማስደሰቱም መጋረጃው በተጋረደ ቍጥር ያስተጋባ የነበረው ጭብጨባ መሰከረለት። ትያትሩ ለራሱ አንድ መጽሐፍ ያህል ነበረና በዝርዝር ለመግለጽ ብዙ ጊዜ ስለሚፈጅ አንባቢዎች በዚሁ ብቻ እንዳይደከሙ እያለፍነው፥ ትርኢቱ እንደ ተፈጸመና የመጨረሻው ጭብጨባ አስተጋብቶ እንደ በረዶ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር አቶ መልአኩ ለተማሪዎቹና ለተሰበሰበው ሕዝብ ያሰሙትን ልብ የሚነካ ንግግር ከዚህ በታች አቅርበነዋል።

የአቶ መልአኩ ንግግር።

«እዚህ የተሰበሰባችሁት ሁላችሁ ትልቁም ትንሹም ጥሪአችንን አክብራችሁ ስለ መጣችሁ፥ በትምህርት ቤቱና በራሴ ስም ሁኜ ጥልቅ ምሥጋናዬን አቀርብላችሁአለሁ። ባለፉት ስምንት ዓመቶች አብረን የኖራችሁት ተማሪዎችም ይህንን ትምህርት ቤት ትታችሁ ወደ እየፊናችሁ ስትሰራጩ የመጨረሻ የመታሰቢያ የምክር ቃላት ባጭሩ ልሰንቅላችሁ ስላሰብኩ ታግሣችሁ እንድታደምጡኝ እለምናችሁአለሁ። ላሳስባችሁ የምፈልገውም፥ እያንዳንዱ ወጣት በአምስት የበላዮች ተጠያቂ መሆኑንና ለነዚህ ሁሉ

መልስ መስጠት እንዳለበት ነው። አምስቱ ጠያቂዎቹም ወላጅጆቹ አስተማሪዎቹ፥ የገዛ ራሱ፥ መንግሥቱና ፈጣሪው ናቸው።

አንደኛው ተጠያቂነቱ በወላጆቹ ለተባለው፥ እኛ እያንዳንዳችን ተወልዶልናል በወላጆቻችን የተደረገልንን ሁሉ አንድ ሁለት ብለን ሳንቆጥር አሳምረን እናውቃለን። ወላጆቻችን በሕፃንነታችን ወራት ተጠንቅቀው ባያሳድጉን፥ የሚያስፈልገንን ምግብ ባይሰጡን፥ ልብስ ባያለብሱን፥ ስንታመም ባያስታምሙንና ጊዜው ሲደርስም ወደ ትምህርት ቤት ባይልኩን፥ በጠቅላላው ባያስቡልን ኑሮ ዛሬ ከዚህ ቦታ እንገኝ ነበረ ወይ? የወላጆች ተስፋ የሥጋቸው ቁራጭ፥ የአጥንታቸው ፍላጭ በሆኑ በልጆቻቸው ላይ ነው ፤ የወላጆች ዓለም ልጆቻቸው ናቸው። የልጆቻቸው ደስታ ደስታቸው፥ የልጆቻቸው ሐዘን ደግሞ ሐዘናቸው ነው። ልጆቻቸው ሲታመሙ አብረው ይታመማሉ። ሲወድቁና ሲነሡ ታግሠው፥ ሲያሳዝኑአቸውም ይቅርታ አድርገው ፤ ከፈጣሪ በታች ሁነው ከሰውነት ላደረሱአቸው ወላጆቻቸው ምን ያህል ዕዳና ከባድ አላፊነት እንዳለባቸው ግልጽ ነው። ከዚህም በኋላ በእግራቸው ተተክተው የቤተሰብን አርማ ይዘው በሕይወት ጐዳና የሚቀጥሉ ልጆች ናቸው የምናደርገው ጥቃቅኑ ነገርና የምንናገረው አጫጭሩ ቃል ቤተ ሰባችንን ሊያስከብር ወይም ሊያዋርድ ይችላል። እንግዲህ ለወላጆቻችሁ ያለባችሁን አላፊነት ተገንዝባችሁ መቸም ቢሆን አትርሱት። ፈጣሪም «አባትህንና እናትህን አክብር» ብሎ አዝዞናል።

ለልጅ የሥጋ ወላጆች እንዳሉት፥ እንዲሁም የመንፈስ ወላጆች ደግሞ አሉት። እነዚህም በአእምሮ እንደወለዱት ለመባል የሚቻሉት አስተማሪዎቹ ናቸው። በትምህርት ቤት በሚሆንበት ጊዜ በአባቱና በእናቱ ምትክ ሁነው የዕውቀት ምግብ እንዳይጐድለው እያሰቡ፥ እርሱም አድጎ በተራው አዋቂ ሁኖ ራሱን ለመቻልና ሌሎችን ለመምከር እስኪበቃ ድረስ ከቀን ወደ ቀን፥ ከሳምንት ወደ ሳምንት፥ ከወር ወደ ወርና ከዓመት ወደ ዓመት ባለመሰልቸት ያስተማሩትንና በዓለም ላይ ሊኖሩት የተፈቀደላቸውን ጊዜ የሰጡት እምነታቸውንም የጣሉበት ስለሆነ የድካማቸውን ፍሬ እንዲያሳያቸው ይገባዋል። ነገሩን በምሳሌ ልግለጽላችሁ። ከአናንት አንዱ በቤቱ ጓሮ አንድ የኮክ ዛፍ ይትከል። ከችግኝነቱ ጊዜ አንሥቶ ሦስት ዓመት ሙሉ ውሀ እያጠጣና እየኰተኰተ ያሳድገው ፤ ከብት እንዳይረግጠውም አጥር ይጠረው። ጊዜው ሲደርስ ኮኩ ፍሬ ሳይሰጥ መክኖ ቢቀር ምን ስሜት ይሰማዋል? ዓመታቱን ሁሉ ለደከመውና ላሰበው ወረታ ሳያገኝ ሲቀር ምንኛ ይመርረው! አስተማሪዎችም እንደዚሁ የሰው አእምሮ አትክልተኞኖች ናቸውና ተስፋቸው ያ የወር ደሞዛቸው ብቻ አይደለም።

ሦስተኛው ተጠያቂነቱ ለገዛ ራሱ ነው ብለናል። ተግቶ ባለመሥራቱ፥ ምክር ባለመቀበሉና ትምህርትና ሥራን እንደ መውደድ ጨዋታን፥ ቀልድ ልፍያንና ቧልትን በመውደዱ የሥጋውን ምኞት አፍቅሮ ተግባሩን ችላ በማለቱ፥ መልካሙን ትቶ ክፉውን በማሰቡና በመከተሉ፥ ጓደኞቹ ከክፍል ወደ ክፍል እየተሻገሩ ሽቅብ ሲወጡ እርሱ የልጅነቱን ጊዜ በቸልታ አሳልፎ ወደ ኋላ ሲቀር ማንን ጐዳ? አብሮ አደጎቹ ትምህርታቸውን አከናውነው አገራቸውን የሚጠቅምና ወገናቸውን የሚያከብር የአላፊነት ሥራ ይዘው መሪዎች ሲሆኑ፥ እርሱ ለገዛ ራሱ ማስተዳደሪያ እንኳ ሊያስገኘው የሚችል

ጥበብ ሳይይዝ ቀርቶ ድሀ ሲሆን ማንን ሊወቅስ ነው? እንዲህ ያለው ልጅ ፍጥረቱን አባክነው ሰው መሆኑ ቀርቶ ወደ እንስሳት ደረጃ ወረደ። ውሎ አድሮም ወንጀለኛ ወይም ለማኝ እንዳይሆን ያሰጋዋል። ዕድሜ ቢያገኝና በስተ እርጅናው ያለፈውን ዘመኑን መለስ ብሎ ቢያይ በገዛ እጁ ከሰው በታች ሁኖ ስለቀረ ራሱን ምንኛ ይወቅስና ይጠላ! እንግዲህ ይህ ሁኔታ በእናንተ እንዳይደርስ ብትፈልጉ በርትታችሁ የምትታገሉበት ወቅት ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። ሳይዘራ አይታጨድም።

መንግሥት ምን ማለት ነው? ለአገሩ ተወላጅሳ ምን ያደርግለታል? ለዚህ ሁለት ጥያቄዎች በዝርዝር ለመመለስ ረጅም ጊዜ ስለሚያሽ ከረጅሙ ባጭሩ ከብዙው በጥቂቱ መንግሥት ለእናንተ ተማሪዎች ያደረገላችሁንና የሚደረግላችሁን ብቻ እናስብ።

ሀ) ይህን ትምህርት ቤት ያሠራላችሁ መንግሥት ነው።

ለ) የሚአስፈልጉአችሁን መጻሕፍት፥ ደብተርና ሌላም መሣሪያ በነፃ የሚሰጣችሁ መንግሥት ነው።

ሐ) የአስተማሪዎቻችሁን ደሞዝ የሚከፍላችሁ መንግሥት ነው።

መ) ችሎታችሁ በሚፈቅድላችሁ መጠን ከፍተኛ ትምህርት እከታገኙ ድረስ አስፈላጊ ሲሆንም ውጭ አገር ድረስ ልኮ በራሱ ወጭ የሚያስተምራችሁ መንግሥት ነው። ከዚህ አዳራሽ ወጥታችሁ ወደ እየቤታችሁ ስትሄዱ ጨለማ እንዳይሆንባችሁ የኤሌክትሪክ መብራት ፤ ጭቃ እንዳይሆንባችሁ ባለ ቅጥራን የባቡር መንገድ ፤ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ደግሞ ፖሊሶችን ያቆመላችሁ መንግሥት ነው። መንግሥት ማለት ሕግና ፤ ሥርዓት፥ ነፃነትና እኩልነት ማለት ነው። የራስ መንግሥት ምን ማለት እንደሆነ በሰፊው ለመረዳት ብትፈልጉም፥ አንፃሩን የፋሺስትን ቀንበር የቀመሱትን ዘመዶቻችሁን ጠይቁአቸው። እንግዴህ መንግሥት ይህን የዘረዘርኩትን ሁሉ መልካም ነገር አድርጎልን እኛሳ ውለታውን እንዴት አድርገን እንመልሳለን?

ሰው የተፈጠረው በሥላሴዎች ምሳሌ ነው። ከሌላው ፍጡር ሁሉ የተለየ የሚያደርገውም ይኸው ነው። ወደ ፊት የሚመጣበትን አስቦ ለመራመድ፥ የሚጐዳውን ትቶ የሚበጀውን እንዲያደርግ፥ ክፉውን ትቶ ደጉን ወይም ደጉን ትቶ ክፉውን እንዲያደርግ ሙሉ መብት አለው። ትክክለኛውንና የተሳሳተውን ሊለይበት የሚችል ፈራጅ ሕሊና ተሰጥቶታል። የፈጣሪው ፈቃድም በአሠርቱ ትእዛዛት ተጠቃልሎታል። ፈጣሪ ለሰው ልጅ የሚያደርግለት መልካም ነገር ተቆጥሮ አያልቅም። ምግብ ልብስ፥ ጎጆንና ጓደኛን ለፍጡራን ሁሉ ቢሰጥ እንኳ፥ ሰውን በተለየ የቀረው ፍጡር ሁሉ የበላይና አዛዥ አድርጎታል። ሰው የምድር ፍጥረት ሁሉ ጌታ ነው! ሆኖም፥ ይህን ሁሉ ያደረገልን ፈጣሪ አንድ ቀን ሳይቆጣጠረን አይቀርም። ተጠያቂነታችንም በተቀበልነው መጠን መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው። እንግዴህ ለዚያን ጊዜ የምንሰጠውን መልስ የምናዘጋጅበት ጊዜው አሁን ነው። ለዚሁም እግዚአብሔር ይርዳን። ንግግሬን ጨርሻለሁ። እናንተ ልጆች የመከርኩአችሁን እንዳትረሱና በሄዳችሁበት ስፍራ ሁሉ መልካም ዕድል እንዲገጥማችሁ እመኝላችሁአለሁ። ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።»

አቶ መልአኩ ንግግራቸውን እንደ ጨረሱና ጭብጨባው ዳር እስከ ዳር አስተጋብቶ እንደ በረደ፥ ከተማሪዎቹ አንዱ ብርሃኑ አባይ ተነሣና በጓደኞች ሁሉ ስም ሆኖ ይህን አጭር የምስጋና ቃል አነበበ።

«እዚህ ትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ ስምንት ዓመት ሙሉ ታግሣችሁ ስላስተማራችሁን ከልባችን የፈለቀ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። አሁንም ተወዳጁ የትምህርት ቤታችን አለቃ አባታችን አቶ መልአኩ የሰጡንን የምክር ቃላት ከኛ እንደማንለያቸውና ሳንታክት ልንፈጽማቸው እንደምንጣጣር በአክብሮት እንገልጻለን። በወላጆቻችንና በአስተማሪዎቻችን፥ በመንግሥታችንና በፈጣሪአችን የተጣለብንን አደራ ለመፈጸም በርትተን እንሞክራለን።»

ተማሪዎቹ የመሰነባበቻ ልዩ ልዩ መዝሙሮች ካዜሙ በኋላ፥ ስብሰባው ተፈጸመና አቶ መልአኩ እንግዶቻቸውን ሸኝተው ሲያበቁ ወደ ጽሕፈት ቤታቸው አመሩ። በጽሕፈት ቤታቸው ገብተው እንደ ተቀመጡም መዝጊያው ተንኳኳና ገና «እፍወይ» ሳይሉ «ግባ» እንዳሉ ቸኰል ከበደ የተባለው ተማሪ ገባ።

«ቸኰል፥ ምን ጉዳይ ኑሮሃል?» አሉ አቶ መልአኩ። «እባክዎን ትምህርት ለመተውና ሥራ ለመግባት ስላሰብኩ ላማክርዎ መጥቼ ነበር» ብሎ መለሰ ቸኰል።

አቶ መልአኩ ድንግጥ አሉና «ምነው፥ ትምህርት የሚያስተው ምን ችግር ገጠመህ? በርትተህ ብታጠና እንኳ ትምህርት የሚያውክህ ልጅ አልነበርክም» አሉት። «ዘመዶቼ ዳር አገር ናቸው፥ እኔም ችግሩ ጠናብኝ፥ ልብሴም አልቆአል። ትምህርቴን ትቼ ሥራ ከመግባትና በማታ ትምህርት ቤት ከመቀጠል በቀር ሌላ መንገድ አይታየኝም» አለ ቸኰል። እንዴ! አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጨርሰሃል ፤ የመጀመሪያውን ኬላ አልፈሀል፥ ከእንግዴህ ወዲያ ብትፈልግ ወደ - አንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፥ በተቀረ ደግሞ ወደ ንግድ፥ ወይም ቴክኒክ ትምህርት ቤቶች አማርጠህ ካሰኘህ ለመግባት ትችላለህ እኮ። ለወደፊት የሚያለብስህና የሚያበላህ መንግሥት ነው፥ የሚያስፈልግህን ሌላ ነገር ሁሉም ይሰጥሀል። አንተም አሁን ሥራ ሐሳብ ውስጥ ከመግባት ይልቅ አርፈህ ብትማር አይሻልም እንዴ! ሥራ ከመግባት ይልቅ አርፈህ ብትማር አይሻልም እንዴ! ሥራ እደ ሆነ መቼም አያመልጥህም ትደርስበታለህ። ጥቃቅኑን ችግር ጋራ ማሳከልህን ትተህ ለረብህ የሚሆነውን ትልቁን ግብ አስብ» አሉ አቶ መልአኩ።

«ትምርህቴን እኮ በማታ ትምህርት ቤት፥ እቀጥላለሁ» አለ ቸኰል።

«ወየ ጉድ! የቀኑን ትተህ የማታውን የትኛው ይቀርብና። ጐጆ ወጥተህ፥ ቀን ስትሠራ ውለህ ለዚሁም ለማጅ ማታ ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት። እባክህን የማይመስል ነገር ነው። «ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው ይልቁን የኔን ምክር ብትሰማ፥ የሚያዛልቅህ ትምርህትን መቀጠል ብቻ ነው። ሌላው ሐሳብ ሁሉ ቢቆይልህ ይሻላል። ጥቂት ትምህርት አደገኛ ነው የሚለውን ምሳሌ ረሳህ እንዴ? ለመሆኑ እውነተኛው ችግርህ ምንድር ነው?» አሉ አቶ መልአኩ

«ልብሴም አልቆብኛል፥ ጫማ መግዣም የለኝም ፤ ደግሞ ለጠጉር ማስተካከያና ለጥቃቅኑ ወጭ የሚሆነኝን የኪስ ገንዘብ ማን ይሰጠኛል?» አለ ቸኰል።

«ሐር ካላማረህ በቀር» አሉ አቶ መልአኩ።

«የመንግሥቱ ልብስ በጣም ጥሩ ነው። ለጫማው እንደ ሆነ ገና ተማሪ ነህ፥ ማን እንዳይሰድብህ ፈርተህ ነው? ትምህርትህን እስከትፈጽም ድረስ እስካሁን እንዳለኸው ብትቀጥል አትችልም ወይ? ጠጉርህንም እንደሆነ በምላጭ ብትላጨው አያስነውርህም ፤ ለመቆረጡ እንደሆነ መልሶ ያድግልሀልና ትደርስበታለህ። «ሁለት ፈላጊ እስከነ አንዱ ያጣል» ተብሎአል። አንተም አርፈህ ብትማር ይሻልሀል።

አቶ መልአኩ ሐሳቡን ሳላልደገፉለት ቸኰል በጣም ከፍቶት እያጕተመተመ ከጽሕፈት ቤታቸው ወጣ። አይቸኰል! እውነትም ቸኰል። በትምህርት ቤት አብረውት ይማሩ የነበሩትን አንዳንድ የከበርቴዎች ልጆች እያየ ካሁኑ ጀምሮ እንደ እነርሱ መንቀባረር ፈለገ። ለጌጡም ለሌላውም ዝግ ብሎ ይደርስበት አልነበረም ወይ? የሥጋን ተድላ ፤ የዓለምን ደስታ ካሁኑ መቅመስ ፈለገ። ይኸውም እሳት ውስጥ እንደ ወደቀ ሥጋ አኰማትሮ የሚያስቀረው መሆኑን ግን አላሰበም። የሚቆጣ ዘመድ እንዳይኖረውም «የኔን ያህል ፤ ትምህርት የሌላቸው ባላገሮች ናቸው» እያለ ዘመዶቹን ሁሉ በንቀት ዓይን እየተመለከተ ምክራቸውን አልፈልግም፥ እንዲያውም አይጠጋቸውም። «ሰፊው ዓለም እያለ እኔ ምን በወጣኝ እጣበባለሁ» እያለ ያቀደውን የተሳሳተ እርምጃ ያጸድቃል። መሰንበት መልካም ነው፥ እስቲ ሥራ ገብቶ የሚሆነውን ለማየት እንበቃ ይሆናል!

## ምዕራፍ አምስት።

# የጽሕፈት ሥራ።

ብርሃኑ፥ ዓለሙና መኰሪያ ሦስቱም አብረው ወደ ነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲዛወሩ ፤ ቸኰል ከበደ ተነጥሎ ቀረ። አፍራሹ ብዙ ምክር ቢሰጠው እንኳ ትምህርቱን አቋርጦ ሥራ ለመግባት የወጠነውን ሐሳብ ሊለወጥ አልፈለገምና ሰሞኑን የሥራ ጥያቄ ማመልከቻዎች በአያሌው ጻፈና ቴምብር እየለጠፈ ለብዙ መሥሪያ ቤቶች ሲናኝ ሰንብቶ፥ ባንዱ ይዞለት ተቀጠረ። በዚህ በተቀጠረበት ጽሕፈት ቤት የሕይወት ታርኩ መስተዋት ከዚህ በታች የተመለከተው ፤ በከፊል ይታይበታል።

| | |
|---|---|
| ስም፡ - | ቸኰል ከበደ፤ |
| ዕድሜ፡ - | ፲፰ ዓመት፤ |
| የሥራ ክፍል፡ - | መዝገብ ፤ ቤት |
| ሥራ፡ - | ረዳት፤ |
| የወር ደሞዝ፡ - | $65 |

ማመልከቻውን ተቀብለው ያነጋገሩት የመሥሪያ ቤቱ የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሹም ደግ ሰው ስለ ነበሩ፥ ልጅነቱን አይተው ደግሞ ይህ ኑሮን ያልሞከረ የዓለምን ጠባይ የማያውቅ ጮርቃ ልጅ አለ ሥራ የትም ሲዋልል ከክፉ ላይ ይወድቃል ብለው አዝነውለት፥ ስለ ሥራ ችሎታው የተሰጠውን ፈተና ካለፈ በኋላ ወዲያው በመዝገብ ቤት ረዳት ሁኖ እንዲቀጠር አደረጉ። ከመዝገብ ቤቱ ሹም ጋርም አገጣጠሙትና ቸኰል በማግሥቱ ሥራ ጀመረ።

መዝገብ ቤቱ በመሥሪያ ቤቱ ሕፃን በምድር ቤት የሚገኝ ባለ ሁለት ትንንሽ መስኮት አንድ አነስተኛ ክፍል ነበረ። ቀድሞ በነበሩት የጽሕፈት ጠረጴዛዎች ላይ የቸኰል ተጨምሮ ስድስት ሆኑና ባለጉዳይ በገባ ጊዜም ከክፍሉ ጥበት የተነሣ መዘዋወሪያ የሚቸግርበት ሰዓት አልታጣም። መስኮቶቹም አብዛኛውን ጊዜ ዝግ ስለ ነበሩ የወረቀቱ ሽታ እያየለ፥ ሳት እያለም የትምባሆና የኃይለኛ ትንፋሽ ሽታ ሲጨመርበት የጽሕፈት ቤቱ ነፋስ፥ ቃናው ከትምህርት ክፍል ጠረን በጣም የተለየ ነበረ። ቸኰል ግን ከዚያ ከነፋሻው የትምህርት ቤቱ ክፍል ይልቅ ይህን ወደደው። ምክንያቱም በመሥሪያ ቤት ሲሆን ነፍስ ያወቀ፥ ሠራተኛው ሁሉ እና ባለ ጉዳዩ እንደ እኵያው ይመለከተውና አንዳንዴ የአቶ ማዕረግ ይስጠው ስለ ነበረ፥ በልጅ አእምሮው የትልቅ ሰውነት ስሜት ይሰማው ስለ ነበረ ነው። ከዚህም በቀር በሥራ ቦታ ፈተና፥ የቃል ጥናት እና በቸኰል አስተያየት ተማሪዎችን አሳር መከራ ለማሳየት ከወላጆችና ካስተማሪዎች የተዶለተ ይህን የመሳሰለ አበሳጭ የትምህርት ቤት ግዴታ ስላልነበረ በጣም ደስ አለው።

እንግዳ በመሆኑ ሥራውን አሳምሮ እስኪለምድ ድረስ ቸኰል ለብዙ ቀን የተወሰነ አላፊነት ሳይሰጠው ፤ በሥራ ክፍሉ በመዝገብ ቤት የሚፈጸመውን ልዩ ልዩ ተግባር ሲመለከት ብቻ ቆየ። ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላም የሥራ ጓደኞቹ ልጅነቱንና አዲስ መጭነቱን እያዩ ትዕግሥት በማድረግ የእርሱንም ፈንታ አንዳንዴ ይሠሩለት ስለ ነበረ፥ ቸኰል ጥቂት ሞልቀቅ እያለ፥ ከጽሕፈት ሥራ የከበረ ሌላ እንደ ሌለ እና ከጸሐፊ ሕይወት የጣፈጠ ሌላ ኑሮ በዓለም ውስጥ እንደማይገኝ ሊያስብና ሊያምን ጀመረ። በዚህ በአዲሱ ሁኔታው ይሰማው የነበረውም ሐሳቡ የሞላለት፥ አንጀቱ የራሰለት ሰው ደስታ ነበረ። ነበረም ጢሱ ባፍንጫዎቹ ቡልቅ ሲል ክብር እንደሚጨምርለት ሙሉ እምነት ስለ ነበረው ፤ ትምባሆን ሱስ ወዲያው አበጀ። ከአዲሶቹ ጓደኞች መካከል እነዚያ ስጃራ የሚያጤሱትም፥ ለዚህ ጥበብ ጀማሪ ደቀ መዝሙር የሆነው ትኩስ ማኅበረተኛ ቤተኛ እስኪሆን ድረስ በፈገግታ እየተመለከቱ ይጋብዙት ነበረ። እንዴ! ነፍስ ያወቀ ሰው መጠጣት አለበት ፤ እንጂ እንዲያውም «አትክልት ዓሣና የሰው ልጅ ከወደ ውሀው» ተብሎአል። ይኸውም ልጅ እንዳያስመስለው፥ ከለስላሳው ይልቅ ኰስተር መረር ያለውን የአልኮል መጠጥን ይመርጥ ነበረ፥ ለጊዜውም አገር የሚያስለምድ ጋባዥ ስላላጣ ቸኰል ወጭ አልበዛበትምና፥ በስጃራና በመጠጥ አክሳሪነት ሲማረሩ የሚሰማቸውን ብዙዎች ሰዎች ንግግር ለማመን አዳጋች ሆነበት።

ቸኰል በዚህ መሥሪያ ቤት ሁለት ወር ያህል እንደ ቆየ፥ የሥራ ጓደኞቹ የዕቁብ ማኅበራቸውን የሚያድሱበት ጊዜ ሆነና እርሱም ዕቁብ ገባ። የመጀመሪያውን ዕቁብ እንዲሸጡለት ችግሩን እያጋነነ አስተዛዝኖ በለመናቸውም ሆነለትና ዋሱን ጠርቶ $ 2፼0

ወስዶ በወሩ ማለቂያ ከደሞዝ ጋር $ 355 በእጁ ገባ። ይህ ከዚህ ቀደም ከሳንቲሞችና አንዳንዴ በዕንቁጣጣሽ ዕለት ብቻ ስዕል እየሠራ ከአንድ ወይም ሁለት ብር ያለፈ አይቶ የማያውቀው ልጅ በመቶ የሚቆጠር ሀብት በአንዴ ፈስሶበት በድንገት በመከበሩ የተሰማውን ደስታ ለመገመት ይቻል ይሆናል። ወዲያው ሰማያዊ ሱፍ ኮትና ሱሬ ያሰፋና አዲስ ጫማ ፤ ባርኔጣና ሌላ የልብስ ዓይነት ገዝቶ የድሮ ልብሱን ወዲያ አሽቅነጠረው። የሚያብለጨልጭ ሰዓት ገዝቶ በሚያብለጨልጭ ማሠሪያ በክንዱ ግጥም አደረገ። ከዚያ ከሎጋ ሰውነቱ ጋር በረዶ በመሰለው ሸሚዝ ላይ ቀስተ ደመና የመሰለ ክራቫት እያሠረ ልጁ ያንጸባርቅ ጀመረ። የውበት ማጐልመሻ በመሆኑ እርግጠኛ ስለ ነበረም መነጽር መሳይ ባይኖቹ ሰካ። ደረቱ ገተር እርምጃውም አውቆ ጀነን አለ። ሕይወት በእውነቱ ጣፋጭ ናት!

አንድ ቅዳሜ ዕለት በዚህ ባዲሱ ሙሉ ትጥቅ ተሸልሞ - ሊያይ ይሁን ሊታይ ፈጣሪ ብቻ የሆዱን ይወቀው - ወደ ነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዱሮ ጓደኞቹን ሊጎበኝ ሄደ። ልጆቹ ወደ ሚገኙበት ቤተ መጻሕፍት አመራና በክፍሉ ውስጥ ገባ ብሎ ቢቆም ጊዜ ተማሪዎቹ ሁሉም ዓይናቸውን ከመጻሕታቸው እያነሡ ቀና ብለው ይመለከቱና ከመ ቅጽበት ወደ ንባባቸው ይመለሳሉ።

ከአስተማሪዎች አንዱ እንጂ ቸኮል ከበደ ይሆናል ብሎ ማን ደፍሮ ጠርጥሮ! እንደ ወትሮው ግልጽ እንዳይሆንም ችግራቸው ላይ ችግር ለመጨመር፥ ዓይኖቹ በፀሐይ መነጽር ተሸፍነዋል። «ሀሎ፥ መኲሪያ» ብሎ በተጣራ ጊዜ ብቻ በድምፁ አወቁት። ወዲያውም መነጥሩን አወለቀና ጥርጣሪአቸውን ጨርሶ አስወገደላቸው። ይህን ጊዜ ልጆቹ የገረማቸውን ልክ ምን እንበል - መብረቅ እንደ መታው ሰው በእያሉበት ክው ብለው፥ አፋቸውን እንደ ከፈቱ ቀሩ። አድናቆቱ ፋታ እንደ ሰጣቸውም መጻሕፍታቸውን እንደተገለጠ በጠረጴዛው ላይ ትተው ቸኮልን ክብብ አደረጉት። የተለወጠባቸውም አለባበሱ ብቻ ሳይሆን አካሄዱ፥ አቋቋሙ፥ አነጋገሩና እጁን እንዲያውም ሰውነቱን ሁሉ እንደሚሠራው ነገር ነበረ። የ «ምን አለብኝ» ስሜት የሞላውን የአራዳ ልጅ መራራቅ፥ ከትምህርት ቤት ከወጣ በዚህ ባጭሩ ጊዜ ውስጥ ሌላ ሥራ የሌላቸው ይመስል እርሱን እርሱን ሲያስተውሉ ፈዝዘው ቀሩ። ምስኪኖቹ የድሮ ጓደኞቹ ልብሱን በውጭ ብቻ ሳይሆን ገብሩንም እያገላበጡ ተመልከተው፥ ክራቫቱንም መላልሰው በእጃችው ዳስሰው፥ የባርኔጣውንና የጫማውን የንግድ ምልክት አጠናቅቀው ካነበቡ በኋላ ባርኔጣውን በእየተራ አጥልቀው ሲያበቁ አድናቆቱ በረድ ብሎ አንደበታቸው ሊከፈት ጀመረ። እንዲህ ያማረበትን መኰንን እንደ እኩያቸው አድርገው ሲዘነጥሉት ከድፍረት እንዳይቆጠርባቸው በመስጋትም ወዲያውኑ የ «ጋሼ ማዕረግ ሰጡት።

«ጋሼ ቸኮል፥» አለ ዓለሙ «ምንድር ነው፥ አዲሱ ሕይወትህሳ ምን ምን ይጥማል?»

«ጽሕፈት ነዋ» አለ ቸኮል።

«እባክህን ጋሼ ቸኮል የጸሐፊ ሥራና ኑሮ እንዴት እንደሆነ ንገረን» አለ ብርሃኑ።

ቸኰል ባርኔጣውን ወደ ማጅራቱ ደፋ ያደርግና እጁን በጐን ኪሱ ከትቶ ደረቱን ገተር አድርጎ፡ -

«ምን፥ ሰውነቴ አትገምቱትም እንዴ? የጸሐፊን የሚተካከል ሌላ ምን ሕይወት አለ ብላችሁ ነው። የጽሕፈት ሥራ እንደሆነ አያደክም ፤ ፈተና፥ ጥናት የሚባል ጭቅጭቅ የለብን ፤ ሰላም ነው። ከሰዓት በኋላና እሑድ ሥራ የለም ፤ ደግሞ ዓውደ ዓመቱ እንደ አፈር ነው።» ቸኰል ይህን ብሎ ሲያበቃ ስጃራውን መዘዞ ያቀጣጥልና ማጤስ ይጀምራል። ከጢሱ ጋርም፥ በቅርብ ቀን ያጠናውን አንድ አዲስ ዘፈን በፉጨት ያዜማል።


«እረ መብልሳ ምን ትበላለህ» አለ መኰሪያ።

«በዘነበ ሲሳይ ሆቴል ደንበኛ ነኝ» አለ ቸኰል። «ቢሻኝ ጥብስ ቢሻኝ ዶሮ፥ ቢሻኝ እንጀራ በወጥ፥ መካሮኒ ያሰኘን በልቼ፥ ደግሞ የተመገብሁትን እንዲያንሸራሽርልኝ አንድ ብርጭቆ ቢራ ወይም የወይን ጠጅ እኸል እብልቶ ውሀ ያሻዋል። በመጨረሻ አፌን በሻይ ወይም በቡና አብሳለሁ።»

ልጆቹ ተያዩና «እንዴት ታድሎአል!» እያሉ ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

«የማታ ትምህርት ቤትስ ገብተህ ትቀጥላለህ ወይ? ያኔ ዱሮ ከትምህርት ቤት ስትወጣ እኮ ገብቼ እማራለሁ ብለኸን ነበረ» አለ ብርሃኑ።

«አድያ፥ ወደፊት እዚያው ቢሮ መጽሐፍ እመለከታለሁ እንጂ የማታ ትምህርት ቤት ደሞ ለምን ይረባል። ደግሞ ቀን ስደክም ውዬ ማታ ከሥራ ጓደኞቼ ከእነ አደፍርስና ከእነ አብጤ ጋር ሆነን ወደ ዕድሜ ቀጥል ወይም ጆሮ ጠምዝ መጠጥ ቤት ሄደን ስንጫወት እናመሻለን። የሙዚቃው፥ የወጉ መጣፈጥ፥ የቤቶቹ ጽዳት መቸስ ግሩም ነው። የነዚህ ቤቶች ያሉት አስተናጋጆችም ሰው አፍቃሪዎችና የደስ ደስ ያላቸው ናቸው ፤ እኔንም ሁሉ ይፈቅዱኛል። ደግሞ ሰው ቀን ሲለፋ ውሎ በዕረፍቱ ጊዜ ሰውነቱን ማስደሰት ይገባዋል። ስለዚህ የዳንስ ጥበብ እስከነ ልዩ ልዩው ስልቱ አሳምሬ ለምጅውአለሁ። ካርታ በደንብ እጫውታለሁ። ገንዘብ ሲያጣጥረኝም ጓደኞቼ በደስታ ያበድሩኛል። ማታ እንደ ልባችን ስንጫወት አምሽተን ወደ እኩለ ሌሊቱ ገደማ ሲሆን በጊዜ ወደ ቤታችን እንገባለን» አለ ቸኰል። «ደግሞ ሥራ ደጉ እያለ ተማሪ ቤት ብሎ ቁም ነገር፥ አዬ! ይብላኝ ለናንተ ፤ ለኔስ እንደሆነ አልፎልኛል። በኋላ ራሳችሁ ትሞክሩታላችሁ እንጂ - ባይመሽብኝ ኑሮ የሥራን ጥሩነት በሰፊው እገልጽላችሁ ነበረ።» በእውነትም ጊዜው መሽቶ ነበረና ትምህርት ቤቱ ከከተማ ራቅ ያለ በመሆኑ፥ አውቶብስ እንዳያመልጠው ቸኰል እስኪጠግቡ ድረስ ሳያጫውታቸው ተሰናብቶ ሄደ።



## በገጽ ፴ ሕይወት በእውነቱ ጣፋጭ ናት ! .........

ብዙዎች ደቂቃዎች የቸኰልን ነገር በሐሳባቸው ሲያጣጥሙ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ፥ ልጆቹ የእርሱን ነገር እየተጨዋወቱ ወደ ግብር አዳራሹ ሊሄዱ ተነሡ። ተማሪዎችም ቢሆኑ ሥጋ የለበሱ ናቸውና ፤ ቸኰል ያ ትላንት አብሮአቸው እርግጫና ሾኬ፥ ኳስ ዓበደች ሲጫወት የነበረው ልጅ እንዲህ ባንዴ ባለፈለትና መኰንን በመሰለው ሳይቀኑበት አልቀሩም። ይህ ስሜትም በተለየ በዓለሙ ላይ በረታና እንዲህ ብሎ ያንጐራጕር ጀመር - «የእኛም ኑሮ እኮ ከኑሮ ጋር ይቆጠር ይሆናል ዓይናችን እስኪፈርጥ ፤ ወገባችን እስኪጐብጥ ድረስ እዚህ የማይረባ መጻሕፍት ላይ ተደፍተን እንውላለን። የልጅነታችንን ጊዜ ሳንጫወትበት እዚሁ ፈጀነው። እኔ እንደሆንኩ ከእንግዴህ ወዲያስ አልሞኝም ፤ አባቴ ይሙት ፤ እዚህ ትምህርት ቤት አልከርምም ወደ ተግባረ ጽሕፈት ትምህርት ቤት እሄድና - ትምህርቱም በሁለት ዓመት ያልቅልኛል ሥራ እገባና እንደልቤ እደሰታለሁ። የሕይወትን ጣዕም ካሁኑ መቅመስ እፈልጋለሁ። ኑ እባካችሁን ሁላችን በተግባረ ጽሕፈት ትምህርት ቤት እንግባ።»

«ታዲያ ቸኰል ሱፍ ቢለብስና ሰዓት ቢያሥር በምን ይበልጠናል መሰለህ?» አለ ብርሃኑ። «ይልቁን ወደፊት ትምህርታችንን ስንጨርስ እኛ እንበልጠዋለን እንጂ። እሱ እንደሆነ ደድቦ መቅረቱ ነው። የማታ ትምህርት ቤትም አልገባ። ትዕግሥት ያሻልና እንጂ እባክህን ቀስ ብለን የምንበለው እኛ ነን።»

«ገና ለገና ተምረን ነው እኮ» አለ ዓለሙ። «ላም አለችኝ በሰማይ ወተትዋን የማላይ። » ደግሞ በእውነቱ ካላችሁስ ሰው እንደ ዕድሉ ነው እንጂ እንደ ትምህርቱ አይደለም። ተምሮ ስላ ድሀ ሆኖ የቀረ ስንትና ስንት ነው! አንድ ቀን ስንኳ ትምህርት ቤት ሂዶ የማያውቅ ፤ ስሙን እንኳ መጻፍ የማይችል፥ ከተማሩት የበለጠ ሀብትና ማዕረግ ያገኘ ደምጎ ሞልቶአል። ይልቁን የምንሞትበትን ጊዜ አናውቀውምና፥ ልጅነት እስካለን ድረስ ቶሎ ቶሎ እንደሰት። እኔ እንደ ሆንኩ ዝም ብዬ ወደ ተግባረ ጽሕፈት ትምህርት ቤት መግባቴ ነው ይብላኝ ለእናንተ፤

ልጆች በሉ በሉ እንጫወት በጣም

እንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም።

የሚለውን ዘፈን ረሳችሁ እንዴ? እውነት ነው እኮ ደግሞ ትምህርት ለመቀጠል የሚፈልግ ችኮ ቢኖር በማታ ትምህርት ቤት መግባት ይችላል።»

ልጆቹ መንገድ ለመንገድ ይህን ንግግራቸውን እየተጫወቱ ሲያዘግሙ የራት ደወል ተደወለና ወደ ግብር አዳራሽ ተፋጠኑ።

* * *

ተማሪዎቻችን የተለመደውን የትምህርትን ቤት ሕይወታቸውን ሲቀጥሉ፥ ቸኰል በአዲሱ ኑሮው ተደስቶ ጥቂቶች ወሮች ተቀመጠ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ጤናው ትንሽ በትንሽ እየተቀነሰ መሔዱ ይሰማው ጀመረ። ለሕመሙ ምክንያት የሆነው ዋናው ሳንከም ለጤና የሚያስፈልገውን ያህል ዕንቅልፍ ባለማግኘቱ ነበረ። አእምሮው በመፈንጠዝ ታውሮ ስለ ነበረ ግን ይህን አስቦ ለመረዳት ጊዜ አላገኘም። በፊት እንደ ጉንፋን አድርጎ ጀመረውና ሲል ሲል ክፉኛ ያስለው ጀመረ። በዚሁ በተጐሳቈለ ጤናው ምክንያትም ሥራውን አሳምሮ ሊፈጽም አልቻለም፥ አንዳንዴም ወደ መሥሪያ ቤቱ መሄድ እየተሳነው በቤቱ ስለሚቀር ውሎ አድሮ ከአለቃው ወቀሳና ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው አልቀረም። ደመወዙም ለዚህ ለችግሩ ጊዜ እንዳይሆነው የበላውን ዕቁብ እየከፈለበት ከዚያችው ከአቅምዋ ግማሽዋ ትሔድ ነበረና ምኑ ተርፎ መድኃኒት መግዣ! ያኔ ዕቁብ ሲደርሰውም «ለክፉ ቀን ይሆነኛል» ብሎ ያስቀመጠው አንድ ሳንቲም እንኳ አልነበረውም። ታዲያ ምን በጀው? እንደምን አድርጎ እንደሚከፍለው ሳያስብ ዝም ብሎ ብድር ይገባ ጀመር። አንዱ አበዳሪ ሲያስቸግረው፥ ከሌላው ተበድሮ ይከፍላል። ደግሞ በጽሑፍ ለማስፈሩ በሚያዳግት ሌላ ልዩ ልዩ ዝቅተኛ ዘዴ ገንዘብ እያገኘ ቀን ይገፋ ነበረ። ይህ ሁሉ ግን በጉዳት ላይ ጉዳት ጨምሮ በሽታውን አባሰበት እንጂ ምንም አልረዳውም። ያ ሎጋ ሰውነቱ ይጠወልግ ጀመረ። ዱሮ የወይን ጠጅ ይመስል የነበረው ጠይምነቱ ወደ አመዳም ጥቁረት ተለወጠ። ከቀን ወደ ቀን ይሻለኝ። ይሆናል ብሎ ቢታገስ ቅሉ፥ ቸኰል ምንም ተስፋ አላገኘም። አንድ ጓደኛው ሕመሙ «የሰው ዓይን ሳይሆን አይቀርም» ብሎ ጥርጣሬውን በገለጸለት ጊዜ እርሱም በሐሳቡ ተስማምቶ ፈውስ ሊሻ ወደ አንዲት «አዋቂ» ዘንድ አንድ ቀን በሌሊት ሄደ። ከሐኪምም ይልቅ ይህችን ያስመረጠው አንድ ምክንያት

«አንዳንድ ጊዜ ሐኪም መርምሮ በሽታውን ቢያውቅ እንኳ፥ መርፌ ይወጋና በሽታውን ሰውነቱ ውስጥ ቀብሮ ያስቀረዋል» የሚል የሞኞችን ተረት በማመን፥ ነበረ። ቸኮል የደንቡን ገጸ በረከት ዕጣን ምናምን ካቀረበ በኋላ የበሽታውን ዓይነትና መድኃኒቱን ነግራው፥ በቶሎ እንደሚድን ባረጋገጠችለት ተደስቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። በማግሥቱም ተበድሮ አንድ ቀይ ሙክት ገዛና የደስ ደስ ወሰደላት። በታዘዘለት መድኃኒት መካከልም ጥቁር ዶሮ የነጭ ድመት ጅራት....... እና ይህን የመሳሰለ ነበረበት። ቸኮል የታዘዘውን ሁሉ ሳያዛንፍ ፈጸመ ነገር ግን ጓጓው በጎ መሆኑ ቀርቶ በሽታው ይልቁን ይብስበት ጀመረ። ዘንግቶ ጅረት መሳይ ተሻግሮ፥ ወይስ የተወሰነው ጊዜ ሳይጨረስ በሐሙስ ቀን ከቤት ወጥቶ ይሆን? በመጨረሻም በጣም ጠንቶበት እኽል ውሃ አላስቀምስ፥ አላስችል ባለው ጊዜ፥ ለመመርመር ወደ ሐኪም ዘንድ መሄድ ግድ ሆነበት።

አንድ ቀን በጥዋት ተነሣና ወደ ሐኪም፥ ዮሐንስ እስክንድር ክሊኒክ ሄደ። በእንግዳ ማረፊያው ጥቂት ጊዜ ዐረፍ ብሎ ቆየና ተራው ሲደርስ ገባ። ሐኪም ዮሐንስም በቃል በሰፊው ጠይቆ ሲያበቃ ልብሱን አወለቀና አገላብጦ ሰውነቱን ሁሉ ሩብ ሰዓት ያህል ከመረመረ በኋላ እንዲህ ሲል ተናገረው፡ -

«አቶ ቸኮል፥ ከምርመራው አሁን እንደ ተረዳሁት፥ ሕመምዎ በእግዚአብሔር በኩል የመጣ ፍጥረታዊ በሽታ ሳይሆን በገዛ እጅዎ ያመጡት መሆኑ በግልጽ ይታያል። ከሰውነትዎ በተለይ ሕመም የሚታይባቸው ሳንባዎ፥ ጉበትዎና ልብዎ ናቸው። ለዚህም ሰበቡ ብዙ ሲሆን ዋናዎቹ እኒህ ናቸው፡-

መጠጥ አለመጠን ያዘወትራሉ።

ለገላዎ የሚያስፈልገውን ያህል አይተኙም።

ሞቃት ልብስ ሳይለብሱ በቅዝቃዜ ሰዓት ሲዘዋወሩ ባሰውነትዎ ውስጥ ብርድ አስገብተዋል።

የሚያጤሱት ትምባሆ ሰውነትዎን በተለየም ሳንባዎን መርዞታል።

በጠቅላላው ደንብ የሌለው ኑሮ የልብ ድካም ፈጥሮብዎታል።

በቀረው ሰውነትዎ ላይ የሚታየው የመጻውለግ ሁኔታም ጠንቁ ይኸው ነው። ለሳንባዎና ለጉበትዎ ፔኒሲሊና ሌላ መርፌ በየቀኑ ጥዋት እዚህ እየመጡ ይወጉ። ለልብዎ የሚያስፈገውን መድኃኒት ደግሞ ከፋርማሲ እንዲገዙ ፤ ወረቀት እሰጥዎታለሁ። ሆኖም፥ በእውነቱ የሚያድንዎ ይህ መድኃኒት አይደለም። ነገሩን በምሳሌ ላስረዳዎ። አንድ መኪና በደንብ እንዲላወስ በየጊዜው ማጠብ ቅባት መቀባት፣ የላላውን ብሎን ማጥበቅ ያስፈልገዋል። የጐደለውን እየሞሉ የተሰበረውን እየጠገኑ ካላጠበቁት በቀር ፤ መኪናው ተበላሽቶ ሊንቀሳቀስ እንደ ማይችል ያውቁታል። ከውስጡ አንዲት ቅንጣት ነገር እንኳ ብትበላሽ መኪናው ወዲያው ይቆማል። በዚሁ አምሳያ የሰው አካላት ከሰው ሥራሽ መኪና ይልቅ ምን ያህል ረቂቅ እንደ ሆነ እና በዚሁ በረቂቅነቱ መጠን በሥርዓት መጠበቅ እንደሚገባው ሊረዱት ይችላሉ። የሰው ገላ ግን እስኪብስበትና መልሶ መነሻውን

እስኪያጣ ድረስ ይታገሣልና ሞኙ ሰው የገዛ ሰውነቱን ገደል ይገፈትረዋል። ስለዚህ የሰውነቱ መኪና አንዳች መሰናክል እንዳያገኘው በንቃት መጠባበቅ የእንዳንዱ አስተዋይ ሰው ተግባር ነው። እይተደላደለ ጤና እንዲኖረው ሰው ከኻያ - አራቱ ሰዓት ውስጥ ስምንቱን እንዲሠራበት ፤ ስምንቱን እንዲያርፍበት ስምንቱን ደግሞ እንዲያንቀላፋበት አስፈላፊው መሆኑን ሥነ ጥበብ ገልጾልናል።

ስለዚህ ፤ የተጐዳው ሰውነትዎን የሚጠግኑት ጥሩ ጥሩ ምግብ ፤ ወተት፣ እንቁላል፣ ቅቤ፣ አትክልት ፤ ፍራ - ፍሬና ይህን የመሳሰለውን በመመገብ ብዙ ዕረፍትና አጥጋቢ እንቅልፍና ንጹሕ ንፋስ ሕጋዊ ኑሮ በመኖር ነው እንጂ የሚዋጥ መድኃኒትና መርፌን ብቻ ተስፋ አያደርጉ። ይህን ምክሬን በመፈጸም ብቻ ነው ከሐምምዎ የሚድኑት እንጂ በተቀረ ዕድሜዎ እንዳያጥር ያሰጋዎታል። ምክሬን ሳይሰሙ ቀርተው አደጋ ላይ ቢወድቁ ግን ጥፋቱ የገዛ ራስዎ መሆኑን ይገንዘቡት።

ቸኰል ይህን በሰማ ጊዜ ክፉኛ ደነገጠ። ከዚህ ጉብኝት በኋላም የታዘዘለትን ሕክምና በደንብ እየፈጸመ ፤ ከወትሮ ስድ ልማዱ ተወስኖ፥ እንደ ሐኪም ዮሐንስ ምክር ለመኖር ፈተነ። በጤንነቱ ጊዜ ያዘወትራቸው ከነበሩት የጨዋታ ስፍራዎች ርቆ በጊዜ ከቤቱ እየገባ ጋዜጣና መጽሐፍ ይመለከት ጀመረ። በጎ ሲሆንም ጥንት አስቦት እንደ ነበረ ወደ ማታ ትምህርት ቤት ለመግባት አሰበ። በዕረፍቱ ቀኖች ንጹሕ አየር ወደ ሚያገኝበት ወደ ከተማ ገጠር እየሄደ ይናፈስ ጀመረ። ሕመሙ ሥር ያልሰደደ ስለ ነበረ ፤ እዚሁም ላይ የልጅነት ፤ ሰውነቱ እያገዘው ፤ ሕክምናው መልካም ውጤት አስገኝና ጥቂት በጥቂት በጎ ሆኖ ብዙ ወር ሳያልፍ ጨርሶ ዳነ።

አየ ጉድ፥ መከራን ለመርሳት ምንኛ አጭር ጊዜ ይበቃል! ቸኰል ሙሉ ጤናውን እንዳገኘ ያሳለፈውን መከራ ሁሉ ከመ ቅጽበት ረሳና እንዲህ እያለ ያስብ ጀመረ፡- «በውኑ ሐኪም ዮሐንስ ተሳስቶ ወይም ሊያስፈራራኝ ብሎ ነው እንጂ በሽታ ተሳስቶ ወይም ሊያስፈራራኝ ብሎ ነው እንጂ የለብኝም እኮ መጠጥ አትጠጣ ብሎ ደግሞ ይቀልዳል።

እስቲ አባካችሁ ማን ጠጥቶ ታመመ? ሁሉ ሰው ይጠጣል እኔ ብቻዬን አይደለሁም። ደግሞ ስጃራ ይቅርብህ ይላል። ታድያ ፤ ግሩም! ሊጤስ ካልሆነ ቀድሞውንስ ትንባሆ፥ ለምን ተፈጠረ ይሆን? ሐኪም ዮሐንስ እንኳ የተማረ ሰው ነበረ። ታዲያ ምንኛ ቢታውር ፤ ነው ይህን ለመረዳት የተሣነው ግን የዓዋቂ ስሕተት ጋራ ያህላል ተብሎ በቀድሞ ጊዜ ባባቶቻችን እኮ ተተርቶአል። ደግሞ ሲጃራ የማጤሰው እኔ ብቻ አይደለሁም፥ በዓለም ውስጥ በሚሊዮን የሚቈጠር ወንድና፥ ሴት ያቦነዋል ፤ ገሚሱም ከፍቅሩ ብዛት የተነሣ ያኝከዋል። የሐኪም ዮሐንስ እስክንድር ነገር እኮ እያደር ያስቃል። ጨምሮ ቤትህ በጊዜ እንድትገባ ይለኛል። ምነው እኔ ብቻ እንደ ጋሪ በአሥራ ሁለት ሰዓት ቤቴ መግባቴ ዶሮ ነኝ እንዴ? ሰው ሁሉ በየቡና ቤቱና በመሸታ ቤት እንደ ልቡ እየተጫወተ ተዝናንቶ እየሳቀ ሕይወቱን በማደስ ሲያመሽ ፤ እኔ በምን አበሳዬ ተኮራምቼ አመሻለሁ! ደግሞ እንደ ሐኪም ዮሐንስ እነሂ የንግድ ቤቶች መክሰራቸው አይደለም ወይ? የሚከፈለው የቀረጥ ጥቅምሳ መቅረቱ አይደለም እንዴ? በእነሱ የሚተዳደረው ሕዝብሳ ፤ ምን ይዋጠው ነው - የሚለው የመሸታ ቤቶች ባያስፈልጉ ኖሮ ባለሥልጣኖች ያዘጉዋቸው አልነበረም ወይ? አይ ሐኪም

ዮሐንስ ሞኝ ተላላ አግኝቶ ሲሰብከኝ አያችሁ? ከዓለም ተነጥዬ በብሕትውና መኖር ከከጀለኝማ እዚያው ዋልድባ ሄጄ አላርፈውም።

ቸኮል በዚህና ባምሳያው አሳብ ልቡን አጸና። በመጠጥ ቤት ከጓደኞቹ ከእነ አደፍርስ ጋር ይጫወተው የነበረው ጨዋታ ልዩ ልዩ ሕብር ፤ ተጐናጽፎ ይታየው ጀመረ። የአዝማሪውና የራድዮው ጣፋጭ ዜማ ሥርግ የመሰለው የሰርከ ፈንጠዝያ ፤ ያ ከዓለም ሕይወት አሳብ ነፃ የሆነው ከምታመሙ በፊት የነበረው ኑሮ ፊቱ ላይ መጥቶ ድቅን እያለ ይናፍቀው ጀመረ። ጣፋጭ ጊዜውን በከንቱ በማሳለፉም ይቈረቈር ነበረ። ሕመሙ በጸናበት ጊዜ ሲርቁት የነበሩትና እርሱም ከሐኪሙ ምክር በኋላ ሲሸሻቸው የነበሩትን የቁም ጓደኞቹን ካሉበት እየፈለገ እንደገና ይጠጋቸው ፤ ጀመረ። ድሮ ደንበኛ ወደነበረባቸው ቡና ቤቶች መለስ ቀለስ አበዛ የቡና ቤቶቹ ሥራ እስኪያጆችም «የት ጠፍተህ ከረምክ ጋሼ ቼኮል?» በልው እያግባቡ ሲጠይቁት ታሞ እንደነበረ መናገር ሐፍረት ሆኖ እየተሰማው «ውጭ አገር ሄጄ ነበረ» እያለ አስመስሎ ይመልስላቸዋል።

አስቀድሞ ሎሚናትና ለስላሳ መጠጥ አንጂ ሌላውን ኃይለኛ መጠጥ እንኳ እጅግ አልተዳፈረም። «ግድ የለህም አንድ መለኪያ ምንም አይልህም ፤ እንዲያውም መድኃኒት ነው። ሐኪም ለእንጀራው ብሎ ነው እንጂ ምን ያውቃ ብለህ ነው? ጤናማው ሰው እንኳ ሲሔድ አንድ በሽታ አንሥቶ ይላከክበታል። አታስብ እባክህን ነገ ለራሱ ያስባል። ይልቁን የኛን የወንድሞችህን ምክር ስማ» እያሉ የልብ ጓደኞቹ በተናገሩት ጊዜ ቸኰል ድፍረት ተሰማውና ቀስ በቀስ እዚያው ጥንት ጠጭነቱ ተመለሰ በፊት በመለኪያ በኋላ በብርጭቆ ገባበት። ስንበት ብሎም የራስ ምታት ሽውታ እንኳ ሳይነካው አንዱን ሽጉጥ ብቻውን ሊያጣራ ቻለ። «አይ ሐኪም ዮሐንስ ብትሳሳት ነው እንጂ እኔስ ደህና ነኝ። ደግሞ ፤ በእውነቱ ሰው በልቶ ካልጠጣ እንደምን ይጠግባል? ለእኛ መድኃኒታችን በርበሬና አረቄ ነው» እያለ ከበርበሬው ይልቅ አሬቄውን በርከት እያደረገ የኰመኰም ጀመረ።

አይ የሰው ነገር! እስቲ ከዚያ ከበሽታው ድኖ ከመጠጥ አመሉ ተርፎ ወደ ሰላም ጐዳና ተመልሶ የነበረው ልጅ ከዚያ ከነበረበት ዘብጥ ዳግመኛ ይግባ! ቸኰል በዚህ በኋለኛው ኑሮው በጤና ብዙ ጊዜ ፤ ሊቆይ አልቻለም። ሰውነቱ ወዲያው ሊመነምን ጀመረ። ያ ፈርዛዛነቱ ቀርቶ ከፀሐይ ውስጥ እንደወደቀ አበባ ጠወለገ፥ ድስት ውስጥ እንደገባ ጐመን ሙሽሽ አለ። ያ እንቧይ የመሰለው ዓይኑ ሟሙቶ ተሰረጕደና ወደ ውስጥ ገባ። ድሮ ደረቱን ገትሮ ጋራ ጋራውን እያየ ይሄድ የነበረው ጐበዝ ዛሬ እንደ ዘተና ዓመት ሽማግሌ ጎብጦ ምርኩዝ ይዞ ምድር ምድሩን እያዩ ሆነ። ቀድሞ ይጠብበው የነበረ ልብስ ዛሬ የጎቱን ተውሶ የለበሰ አስመሰለው ሳሉም ተቀሰቀሰበትና ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት ሄደ። ሲል ሲል የቀረው በሽታው ሁሉ አገረሸበትና ከአልጋው መነሣት ተሳነው። እዚያው አብረውት ሲያሸበሽቡ የነበሩት ጓደኞቹም በምር መታመሙን ሲያውቁ ጊዜ እንደ ጢስ በንነው ቀሩ። በዚህ በችግሩ ጊዜ የሚደግፈው ሰው እንዳይኖርም ጥንት ዘመዶቹኑ ዘወር ብሎ አይቶአቸው አያውቅም ፤ እንዲያውም አይፈቅዳቸው። እነርሱም የሚቀመጥበትን ቦታ አያውቁ እንደምን ብለው ይፈልጉት? ሕመሙ ጸንቶበት ፤ እህል ውሀ አልቀምስ ባለ ጊዜም ይተኛበት የነበረ «የዘነበ ሲሳይ» ሆቴል ባለበት ለጽድቅ ይሆነኛል ብለው፥ ደግሞ

የዳነ እንደሆን በዱቤ ተቀልቦት የነበረውን ሂሳብ ምናልባት ቢከፍል ተስፋ በማድረግ በድሆች ሐኪም ቤት አስገብተው አስተኙት።

## ምዕራፍ ስድስት።

# በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት።

ዓለሙ ሰብስቤ ሁለቱ ጓደኞቹ አብረውት እንዲዛወሩ እሺ ለማሰኘት፥ የተቻለውን ያህል ተነጋግሮአቸው፥ እነርሱ ግን ትምህርታቸውን ለማዝለቅ ስለ ቆረጡ ምክሩን ባለመስማታቸው እያዘነ ብቻውን ወደ ተግባረ ጽሕፈት ትምህርት ቤት ተዛወረ። ይህን ትምህርት ቤት ያስመረጠው ምክንያትም ለሚገኘው ትምህርት ዝንባሌው ሳይሆን፥ ትምህርቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ በመሆኑ፥ አፋጥኖ ጨርሶ ሥራ እንዲገባና እንደ ቸኰለ ለባብሶ የዓለምን ፍሬ ቶሎ ለመሳተፍ እንዲመቸው ሲል ነበር። እንግዲህ ቀድሞ አራት የነበሩት ጓደኞች አንድ በአንድ ተበታትነው ብርሃኑና መኩሪያ ብቻ ሳይለያዩ በነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀሩ።

ነቅዓ ጥበብ በአንድ ሜዳ ላይ የተሠራ ስምንት መቶ አዳሪዎችና ተመላላሾች የሚማሩበት ዘመናዊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። አቀማመጡም በደብረ ሰላም ከተማ ገጠር በስተ አዜብ ነው። በሕንፃዎቹ መካከል የአሥር ዓመት ዕድሜ ያለፈው ቤት አይገኝም።

አሠራራቸውም በቅያስ ሁኖ አንዱ ሕንፃ ራሱን ችሎ ለአንድ ጉዳይ የታቀደ በመሆኑ ቅጥልጥል ሳይሉ፥ አንድ አርቲስት ከሰማይ ሁኖ ቁጭ ቁጭ ያደርጋቸው ይመስላሉ። ምድረ ግቢውም ዙሪያውን በኮተቤ ጥርብ ድንጋይ ተከቦአል። እግራችን የቅስቱን ደጀ ሰላም ተሻግሮ ወደ ውስጥ እንደገባንና በግንባር የሚገኙትን የአበባ መደቦች እንዳለፍን፥ ዋናው የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ሕንፃ በፊታችን ተድቅኖ ይገኛል። የቤቱ ማዕዘኖች ፤ ጥርብ ድንጋይ የቀረው ግን ከጡብ የተሠራ፥ ባለ ሁለት ድርብ ሕንፃ ነው። መስኮቶቹም የፎቅና የምድር ቤት ሳይበላለጡ በረድፍ ሆነው ተሠርተዋል። ደረጃውን ወጥተን ዋንውን ደጃፍ አልፈን ጥቂት እርምጃዎች ተራምደን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ስንመለከት ሞላላው መተላለፊያ ይገጥመናል። ክፍሎቹም መዝጊያዎችም ወደዚሁ ይከፈታሉ። በበሮቹ መካከል የሚገኘው ግንብ ልሙጥነቱ ለዓይን አሰልቺ እንዳይሆን ታስቦ፥ የሚያምሩ ሥዕሎች ተሰቅለውበታል። ከበሮቹ አንዱን ከፍተን ራሳችንን ብቻ አግብተን በተመለከትን ጊዜም ክፍሉ አንድ ጽሕፈት ቤት እንደሆነ እናያለን። የተለመደው ጠረጴዛ፥ ወንበሮች ፤ ሰነዶች የሞሉ ቁም ሳጥኖችና መደርደሪያዎች፥ የጽሕፈት መኪና፥ ስልክና ይህን የመሳሰለ ያለበት መሆኑን እንመለከታለን። በግንቡም አንዳንድ ሥዕሎች ይንጠራወዛሉ። በምድር ቤት የሚገኙት ጽሕፈት ቤቶች ሁሉ ሁኔታቸው ይብዛ ይነስ ይኸው ሲሆን፥ በፎቅ የሚገኙት ግን የተለዩ ናቸው። አብዛኛዎቹ የትምህርት ክፍሎች ሲሆኑ፥ አንዳንዶቹ የሥነ ጥበብ መመርመሪያዎች ናቸው። ወንበሮችና ጠረጴዛዎች (ዴስኮች) ፥ ደግሞ ብዙ እንዳገለገለ የሚያስታውቅበት ጥቂት ገብታ፥ ልዩ ልዩ ካርታዎች ሥዕሎችና አንባቢው

የማይስታቸው ሌሎች የትምህርት ክፍል ቈሳቍስ ይታይባቸዋል። ከዋናው ሕንፃ ፈቀቅ ብሎ የሚገኘው የትምህርት ቤቱ የጉባኤ አዳራሽ ነው። ሕንፃው ከውጭ ሲታይ ያን ያህል አይደንቅም እንደቀሩት ቤቶች ከጡብ የተሠራ ነው። ግን ድንቁ የሚጀምረው መድረኩን ከተሻገርን በኋላ ነው። ወደ ግንባር፥ ዓይናችን የሚያርፈው በቀይ ከፈይ መጋረጃ በተጋረደው የተጫዋቾቹ መደብ ላይ ሲሆን፥ በአዳራሹ ግጥም ብለው የሞሉት ወንበሮች ወደዚሁ መደብ እየተመለከቱ ከዚሁ የተፈነጠቁ የፀሐይ ጮራ ይመስላሉ። ግንቡ ለዓይን እንዲያምር በአረንጓዴና ብጫ ቅይጥ ቀለም ተቀብቶአል፥ ጣራውም እንደ አጎበር ሁኖ በልዩ ልዩ አረግ ጌጥ ተሸልሞአል። የትምህርት ቤቱ አደባባይ ይህ ክፍል ነው።

ቀጥሎ የሚገኙት እንደዚሁ በሸክላ የተሠሩ የግብር አዳራሽና የመኝታ ቤት ናቸው። ራቅ ብሎ እንደ እንጉዳይ በለምለሙና በባሕር ዛፉ መካከል ጉች ጉች ብለው የሚታዩት የአስተማሪዎችና የምድረ ግቢው ሠራተኛ መኖሪያ ቤቶች ናቸው። ነገር፥ ግን የእነዚህንም ሁኔታ ስንተነትን ተወዳጅ አንባቢን እንዳናሰለቸው፥ የጨዋታ ሜዳውን እንዳይዘነጋ ብቻ እያሳሰብን ልጆቻችን በዚህ በአምሳለ ገነት አካባቢ የሚኖሩትን ኑሮ ወደ መተረክ እንሻገራለን።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባንድ ፊት የልጅነት ጨዋታ እንደልብ ሲገኝበት፥ ጥናቱም ያን ያህል ጥብቅ ፤ አልነበረም። በሁለተኛው ደረጃ ግን የትምህርቱ መጠን ከፍተኛ ስለነበረ ጥናቱ ሁሉ ከረር ያለ ሁኖ ለጨዋታ እምብዛም ፋታ አይገኝም ነበረ።

እነ ብርሃኑም በዚህ በአዲሱ ቤታቸው ማለዳ ተነሥተው የብርድ ልብሳቸውን ይከናነቡና ሲያጠኑ አርፍደው ፊታቸውን ተጣጥበው ወደ ቁርስ፥ ከዚያም መጻሕፍቶቻቸውንና ደብተሮቻቸውን ይዘው ከክፍል ወደ ክፍል ሲሯሯጡ ይውሉና ከሰዓት በኋላ ከላቦራቶሪ ወደ ስፖርት ሜዳ ተመላልሰው ማሳረጊያው ቤተ መጻሕፍት ነበረ። የርኑሮውን ሸክም ቀለል ያለ በማድረግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ክበቦችና ማኅበሮች ባይኖሩ ኑሮ ይህ የሥርክ ሕይወት በእውነቱ በተሰለቸ ነበረ፥ ነገር ግን ልጆቹ ሳይቦዝኑ የብዙዎች ክበቦች አባሎች ነበሩ። ብርሃኑ ዓባይ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ክበቦች ውስጥ ልዩ ልዩ ተግባር ነበረው። የክርክር ክበብ አባል ፤ የወንዶች ወጣቶች ክርስቲናዊ ማኅበር አባል የማኅሌት ክበብ መሪ ፤ የትያትራዊ ቅኔ ክበብ ጸሓፊ የቴንስ ክበብ አባል የእርሻ ክበብ አባል። ብርሃኑ በነዚህ ክበቦች ሁሉ ደንበኛ ማኅበረተኛ ሲሆን በተለየ በክርክር ክበብ ንግግሮች ውስጥ እስከ አንገቱ ድረስ ተነክሮ ነበረ። ክርክሮች ቅጣቸው ምን እንደ ነበረ ተወዳጁ አንባቢ ለማወቅ ሳይፈልግ አይቀርምና ለዓይነት ያህል አንዱ ይኸውለት፡-

የክርክር ክበብ ሰብሳቢ ክብረት ደስታ።

| | |
|---|---|
| ጸሐፊ | መኩሪያ በላይ። |
| ዳኞች | ፩ መምሕር ጳውሎስ። |
| | ፪ መምሕር ተወልደ ብርሃን። |
| | ፫ አንድ ተማሪ |

ተከራካሪዎች፡ - ይከልከል ባይ ብርሃኑ ዓባይ።

፡ አይከልከል ባይ ዘገየ ግድየለው።

ክርክሩ - መጠጥ ይከልከል ወይስ ነፃ ይሁን? ብርሃኑ - መጠጥ የሰውን የገላና የአእምሮ ጤናን አጉድሎ በሕመም ላይ ይጥልና ውሎ አድሮ ወደ ዕብደትና ወደ ሞት የሚያደርስ አጥፊ መርዝ በመሆኑ በሕግ ሊከለከል ይገባዋል። የጉልበት ሠራተኛው፥ ጸሐፊው፥ ነጋዴው፥ ወታደሩና ሌላውም ሠራተኛ ቀኑን ሙሉ ሲለፋ የዋለበትን ለቤቴ፥ ለልጆቼ፥ ለሰውነቴ የሚያስፈልገውን ምግብ ለመግዣ፥ ለክፉ ቀን ይሆነኛል ሳይል ሌባው እንኳን ነፍሱን ሸጦ ሲሰርቅ ያድርና እነሀ ሁሉ ለፍተው ያገኙትን ገንዘብ ለአልኮል ለውጠው ባዶ እጃቸውን እየተንገዳገዱ ወደ ቤታቸው የሚገቡ ወይም በእየጉድባው ወድቀው የሚያነጉ በመሆናቸው ጥቅማቸውን ከጉዳታቸው ሊለዩ አልቻሉምና መጠጥ በሕግ ሊከለከል ይገባዋል።

ዘገየ፡ - ሰዎች በመጠጥ ምክንያት ጉዳት የሚደርስባቸው መጥነው ሳይጠጡ እየቀሩ ነው እንጂ መጠጥ በልክ ከሆነ ሰውነት የሚበጅ ሕይወትን ለማደስ ደግሞ አስፈላጊ ስለሆነ በሕግ የሚበጅ ሕይወትን ለማደስ ደግሞ አስፈላጊ ስለሆነ በሕግ ሊከለከል አይገባውም። አንተ አሁን የመጠጥን ስም እንዲህ የምታጠፋው ጥቅሙን እያወቅኸው ስታብል ነው።

ብርሃኑ፡ - አልኮል ለሰውነት መልካም ነው ያልከውን እስቲ በኋላ ታስረዳናለህ። በተቀረ በልክ መጠጫ ተብሎ መለኪያ ተሠርቶ ነበረ፥ ብቻ በዚሁ እየተጠጣም ከመስከር አልተተረፈም እና በመለኪያ ተጠጥቶ ከሰከረ በሕግ ሊከለከል ይገባዋል። የአልኮል መጠጥ ደግሞ አንዳች ምግብነት እንደሌለው በሐኪሞች ዘንድ ተረጋግጦ፥ እነርሱም የሚመከሩን እንዳንጠጣ ነው። በኛ በመሐይምኖቹ ዘንድ ቢሆንም፥ አልኮል ምግብ ቢሆን ኑሮ እናቶቻችን ወተቱንና አብሹን ትተው ልጆቻቸውን በዚሁ ያሳዱጉአቸው አለነበረም ወይ፥ ነገር ግን ይህን አጥፊ መጠጥ የምናዘወትረው «ነፍስ አውቆአል» ከተባልን ወዲህ ስለሆነ የዕውርነታችን ነገር ያስገርማል። ሞቅታ ወይም ስካር ማለት የዕለት ዕብደት ነው እንጂ ሌላ አይደለምና መጠጥ በሕግ ሊከለከል ይገባዋል።

ዘገየ፡ - ስሙን በከንቱ ታጠፋዋለህ እንጂ ሰው እንደሆነ የመጠጥን ጥቅም ከተገነዘበ ሰንብቶአል። እስቲ በዓለም ውስጥ መጠጥ የማይጠጣበት አገር እንዳለ ንገረኝ?» እስላሞቹ ልትለኝ ነው? «እኛ ክርስቲያኖቹ በጌሾ ቋንቋ ስንሰክር እነርሱ፥ ደግሞ በጫት ብሩንዶ ይሰክራሉ። ደግሞ መጠጥ በሰው አፍ ይቅርና በመጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ጠቃሚነቱ ተመስክሮለታል ሽማግሌው ኖህ እንኳ ወይን ጠጁን እያስጣለ ይመገምግ ነበር። ቅዱስ ዳዊትም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፡ - የወይን ጠጅም የሰው ልብ ደስ እንዲያሰኝ። ፊቱ በዘይት እንዲበራ እንጀራም የሰው ልብ እንዲያጸና» ሊቁ ንጉሥ ሰሎሞንም እንዲህ ሲል ጽፎአል። ለጥፋት ስለሚቀርብ ሰው ጻጅም ስጡ ወይንም ሰውነታቸው ለተከዘ ይጠጣ ዘንድ መከራውንም ይረሳ ዘንድ ድካሙንም ከዚያ በኋላ እንዳያስብ ጌታ በቃና ዘገሊላ ውሀውን ወደ ጠጅ እንደ ለወጠ የሚነግረውን ታሪክ ሳታነበው አልቀረህም። ቅዱስ ጳውሎስም ጢሞቴዎስን «ደግሞ ውኃ አትጠጣ ጥቂት ጻጅ ጠጣ እንጂ ስለ ሆድህ ስለ

ደቄህም ብዛት» ብሎ ፤ መክሮታል። ታዲያ፥ አቶ ብርሃኑ ሆይ፥ ይህን ሁሉ ስታውቅ እንደምን ደፍረህ መጠጥ በሕግ ይከልከል ትላለህ?

ብርሃኑ፡ - መጽሐፍ ቅዱስን ከጠቀስክ፥ ኖህ ከጠጣ በኋላ የሆነውን ንገረን እንጂ ለምን ሽፋፍነህ ታልፈዋለህ። ነፍሱን አጥቶ ዕርቃነ ሥጋውን እንደ ግንድ ተዘርሮ፥ የገዛ ልጁን ከምን «ሳቅህብኝ» ብሎ ረገመ እንጂ፥ ሌላ ምን ፋይደ አገኘ? ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የተፈቀደው የቦካው አስካሪው መጠጥ ሳይሆን ጫፋጩ የፍሬው ጭማቂ እንደሆነ ብለው የሚከራከሩ የሃይማኖት ክፍሎች መኖራቸውን ታውቃለህ ወይ? ይልቁን፥ ያውልህ፥ ስካር ከትልልቆቹ ኃጢአቶች አንዱ መሆኑ በመጽሕፍ ቅዱስ ተደጋግሞ ተነግሮአል፡ - ሰሎሞን እንዲህ አለ፡ - «ወይታ ለማን ነው። ኃዘን ለማን ነው። ፀብ ለማን ነው ጩኸት ለማን ነው። ያለ ምክንያት መቁሰል ለማን ነው። የዓይን ቅላት ለማን ነው። ጸጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን። የወይን ጸጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚሰበሰቡ። ወደ ፀጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ መልኩም በብርሌ ፤ ባንጸባረቀ ጊዜ እያጻፈጠም ይገባል። ከጠጡት በኋላ እንደ እባብ ይነድፋልና እንደ ጉበናም መርዙን ይፈስሳል። ዓይኖችህ አመንዝሮች ያያሉ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል። በባሕር ውስጥም እንደተኛ ትሆናለህ እንዳንቀላፉም በምሰሶ ላይ ትላለኸም መቱኝ ያውም አልተሰማኝም ጐተቱኝ አላወቅሁምም። መቼ እነሣለሁ ደግሞ አብዝቼ እሻታለሁ። ጌታ ከተናገረው ጥቂቱ ያውልህ - በነፍሳችሁ ግን ተጠንቀቁ ልባችሁ በሥሥት በስካርም እንዳይደነድን..... ያም ቀን በድንገት እንዳይደርስባችሁ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎአል - የሥጋም ሥራ የተገለጠች ናት.... ምንዝር.....(ዝሙት) ...... ስካርም መሶልሶልም ይህንንም ሁሉ የሚመስል። እንደዚች ያለችውን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ጨምሮ ደግሞ - በቀኑም እንሂድ ቦቅን ነገር። በዘፈን በስካር አይደለም ፤ በዝሙት አይደለም በሴሰኝነትም በፀብም በቅናትም ብሎአል። ለሰካራም፥ በመንግሥተ ሰማያት ቀርቶ በዚች ዓለምም ተስፋ የለውም። «የመሸታ ነጋዴ ሰካራምን ይፈቅደዋል ፤ ልጁን ግን አይድርለትም፣» እያሉ ፅርዓውያን ይተርታሉ። ባንዳድን ሃይማኖቶች ደግሞ መጠጥ ጨርሶ የተከለከለ መሆኑን አሳምረህ ታውቃለህ። ለማንኛውም ዓይነት ሥራ በታማኝነት የሚፈለገው ጭምቱ ነው እንጂ ሰካራምን ማን ያምነዋል?

ዘየገ፡ - አየ ጉድ ፤ በእብለት ልታሳምነን፥ ትጣጣረለህ። አሁን ላንተ እንደ መሰለህ ሁሉ በብዙዎች መንግሥታት ዘንድ ፤ በተለየም በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት አገር ያንተ ብጤዎች ሰዉን በውሀ ጥም ሊፈጁ ተነሥተው «የመከልከል (PROHIBITION) የሚባለውኝ ሕግ አውጥተው ሳይከናወንላቸው ቀርቶ መተረቻ ሆነዋል። መጠጥ ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ መሆኑ ያኔ ተረጋገጠ። ከዚህ ከተባለው በላይም በአልኮል የሚተዳደረውን ሕዝብ ምን ይዋጠው ነው የምትለው እባክህን?

ብርሃኑ በተባበሩት የአሜሪካ፥ መንግሥታት አገር ቢሆንም «የመከልከል» ሕግ ባይጸና እንኳ አልኮል ስድ እንዳልሆነ ታውቃለህ? በሌሎች አገሮች በብዙዎቹ ዘንድም መንግሥት በቅርብ የሚቆጣጠረውና ዕድሜው ኻያ አንድ ዓመት ያልሞላው ሰው በመሸታ ቤት እንዳይገባ በሕግ ክልክል መሆኑን ታውቃለህ ወይ? አንተ እንደምትለውም ሞክረው፥ ካቃታቸው እኛ ሳንሞክረው እንዳንቀር ማለትህ እነሱ ገደል ከገቡ እኛም እንግባ ማለትህ

አይደለም ወይ? ባይሆንም ሞክረን ይቀራል እንጂ። ስድ ይሁን ማለት በአእምሮ የተነገረ፥ አይመስለኝም። በአልኮል ጠንቅ የሚደርሰውውን ጉዳትና በዚሁ ሳቢያ የሚያልቀውን ሕዝብ ብታስብ ኑሮ እንዲህ ብለህ አትናገርም ነበረ። አብሮ አደጋችን ቸኰል ከበደ እንኳ ከመጠጥ የተነሣ ታሞ፥ ሐኪም ቤት መሆኑን ሰምቼአለሁ መጠጥ የሕዝብ ግብረ ገብነት ጠር መሆኑ፥ ደግሞ ለይምሰል እሱን እንነግዳለን ብለው መርበባቸውን እየዘረጉ ወጣቶችን ሰንክለው የሚያስቀሩትን ብታስብ ኑሮ የተናገርከው ቃል፥ ከአፍህ አይወጣም ነበረ። ይህ ሁኔታ ዛሬ የገነነው ደግሞ ትምህርት ቤቶች በአያሌው ተከፍተው ዕውቀት በመስፋፋቱ ጭምቶች ልንሆን በሚገባ ጊዜ መሆኑ በጣም ያሳዝናል። በመጠጥ ቤት ተወልደው ያሚያድጉት ምስኪኖቹ ሕፃናት ና በነዚህ ቤቶች የሚያገለግሉት ደመወዝተኞች ሁሉ ምን ሞያ እያጠኑ እንደሚያድጉና በኋላ ለማኅበሩ፥ ምን ዓይነት ሕዝብ እንደሚጨምሩለት እስቲ አስብ። የእነዚህ የመጠጥ ቤቶች ሥራ አስኪያጆች ለቀሩት ልጃገረዶች ምን ዓይነት አርአያ ናቸው? በአልኮል ጠንቅ የጠፉትን አገሮች በታሪክ ውስጥ ብትፈልግ ታገኛለህ። በምን ይስተዳደሩ ላልከው ደግሞ ፤ ለሴቶች ልጆች ከአረቄ ንግድ በቀር ሌላ ሥራ የለም እንደማለትህ ይመስላል። ይህን ማለትህም ወንድ የሚሠራውን ማናቸውንም ተግባር ሴት ልትሠራ የምትችል መሆንዋን ባለማወቅህ ነው። ብበዙ አገር ሴቶች በየፋብሪካው ከወንድ እኩል ሠርተው ራሳቸውን ችለው መኖራቸውን እወቅ። ሌላ ቀርቶ የሴት ወታደር እንኳ አለ። በትምህርት ረገድም ሴት የወንድ ተወዳዳሪ መሆንዋ የታወቀ ነው። ደግሞ ሚስቱና ልጆቹ ካሁን ካሁን ይመጣል ሲሉ እንቅልፉ እያሸነፋቸው በየተቀመጡበት ተደፍተው ኮሽ ባለ ቁጥር ብንን እያሉ ሲጠብቁት፥ በመንገድ ምን ክፉ ነገር ያገኘው ይሆን ብለው ነጋ ጠባ ሲሰጉለት እርሱ በዓለም ውስጥ አንዳች ግዳጅ እንደ ሌለበት እያፈራረቀ መለኪያዎቹን ሲገለብጥ፥ ብርሌዎቹን ሲያንደቀድቅና አዝማሪን ሲያስገጥም አምሽቶ ዶሮ ጩኸት ላይ በየመንገዱ እየተንገዳገደና እየተለፋደደ፥ አንዳንዴም እንደከብት በአራት እግሩ የሚያስኼደው፥ በኋላም ከቤቱ ገብቶ የፈረደበትን ቤተ ሰብ ሲያንጫጫ የሚያሳድረው የዚህ ግፍ ሁሉ መነሻው ዙሮ ዙሮ ያ አንተ ያመሰገንኸው መጠጥ አይደለም ወይ? ሰውን ካበለዘ በኋላ ማኅበራዊ ኑሮን የሚያጠፋና ከዚህ የባሰ ተከታይ እንዳያመጣ የሚሰጋው በምር ሊታሰብበት የሚገባው መርዝ መጠጥ ነው። ስለዚህ በሕግ ሊከለከል ይገባዋል»።

ይህን ጊዜ የተወሰነው ሰዓት ደረሰና ደወሉ ተደውሎ ክርክሩ ቆመ። ከዳኞቹ ሁለቱ ለብርሃኑ ሲፈርዱ አንዱ ለዘገየ ፈረደና በድምጽ ብልጫ ብርሃኑ ረትቶ ተጨብጭቦለት ጉባዔው ተበተነ።»

*    *    *

የነቅዓ ጥበብ ትምህርት ቤት ከዚህ በላይ ባመለከትነው ክርክር መሳይና በልዩ ልዩ ስፖርት እየተቀለመ መሽቶ እየነጋ ሕይወት ይቀጥል ነበረ። እነ ብርሃኑም ትምህርቱ ተሳክቶላቸው፥ ሦስት ክፍሎች ፈጽመው አሁን በመጨረሻው ክፍል ውስጥ ናቸው። መኰሪያ እና ብርሃኑም ሳይበላለጡ ከክፍል ወደ ክፍል አብረው እየተሸጋገሩ ዛሬ

የሁለተኛው ደረጃ ትምህርት ፍጻሜ ፈተና ስለ ደረሰባቸው ቀን እስከ ሌሊት በርትተው በማጥናት ላይ ይገኛሉ።

## ምዕራፍ ሰባት።

# የአዲሱ ሕይወት ጣዕም።

ዓለሙ ሰብስቤ ትምህርቱን በተግባረ ጽሕፈት ትምህርት ቤት ለማከናወንና ሥራ ለመግባት እጅግ አላዳገተውም። ከትምህርት ቤት በመጠኑ ተመርቆ እንደወጣም በአንድ የንግድ ቤት ጠቀም ያለ ደመወዝ የሚገኝበት የሂሳብ ሥራ ወዲያው አገኘና ገባ። የቤት ኪራይና የቀለብ ሐሳብ እንዳይኖርበት ኑሮው በአባቱ ቤት ሁኖ፥ ደመወዙን እንደመሰለው ወጭ ለማድረግ ተፋላሚ የሌለበት መብት ነበረው። ሐሳብን ሁሉ በወላጆች ላይ ጥሎ የእናትን ፍትፍት እየጐረሱ መቀመጥ፥ ከዚህ የተሻለ የሚያስመኝ ምን ኑሮ አለ?

ባለፈው ሰሞን ጉንፋን መሳይ ያዘውና ዓለሙ ተኝቶ እንዲሰንብት የሐኪም ትእዛዝ ሆነበት። በአልጋው ላይ እየተገላበጠ ጋዜጣዎች ማንበብና ራድዮኑን ማዳመጥ ሲሰለቸው፥ እነዚህን ችላ ብሎ ሐሳቡ እንደ ፈቀደው እንዲዋልል፥ በተወው ጊዜም ከጥቂት ዓመታት በፊት አብሮአቸው ሲላፋ የነበሩትን ዛሬ ሁሉም አድገው ለሰውነት የደረሱት የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ትውስ አሉት። በተለይም ጓዴው የነበረው ብርሃኑ አባይን ናፈቀና መጥቶ እንዲያጫውተው ስልክ ደወለለት። ትምህርት ቤቱ ተዘግቶ ብርሃኑ በዕረፍት ላይ ነው። በንግግራቸውና ስለ ኑሮ ባላቸው አስተያየት እንደ ሰማይና ምድር ቢራራቁ እንኳ፥ ትርጉሙን ለመረዳት የሚያዳግት ፍቅር በዓለሙና በብርሃኑ መካከል ነበረ።

ሊመሽ ሲል ብርሃኑ እንደ ጥሪው ወደ አቶ ሰብስቤ ግቢ መጥቶ በሩን ባንኳኳ ጊዜ አሽከር ከፈተለትና ወደ ዓለሙ ክፍል መራው። ብርሃኑና ዓለሙ እንደ ተያዩና ሰላምታ እንደተሰጣጡም ሐሳባቸው እንደ በምክር ከመቅጽበት ወደ ንጋት ኮከብ ትምህርት ቤት ቀኖቻቸው ተመለሰና ያ ትናንት ሲላፉትና ሲነጋገሩት፥ በቀን ሲቃኙትና አስተማሪዎቻቸውን ለማናደድ ሲያደርጉት የነበረው ሁሉ ትዝ እያላቸው ዝም ብሎ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቆዩ ፤ በግንባራቸው አንዳንዴ የትካዜ፥ አብዛአውን ጊዜ ግን የፈገግታ መልክ ይታይ ነበረ። ከዚህ ሰመመን ነቅተው አፋቸውን እንደከፈቱ፥ እኩል ሰዓት ያህል ከልጅነታቸው ጊዜ ነገሮች እንደገጠማቸው እያነሡ ሲጨዋወቱና ሲስቁ ከቆዩ በኋላ ፤ አሽከሩ ሻይ አመጣላቸውና ጠጡ።

«እህ ዓለሙ» ብርሃኑ «ያማረ ክፍልና ምቹ አልጋ አለህ እንግዲህ እዚሁ ታረጀዋለህ እንጂ ምን አግዶህ ሚስት ታገባለህ።»

«ሰማህ ወዳጄ ብርሃኑ» አለ ዓለሙ «በእውነቱ የቤቴና የኑሮዬ ምቾት አባብሎኝ ሳይሆን ሚስት ጨርሼ እንደማላገባ እልሃለሁ። ምክንያቱም ሚስት ማግባት የሚያስፈልግ ሁኖ ስላልታየኝ ነው።»

«ዓለሙ» አለ ብርሃኑ «ሁሉም እንዳንተ ወንደላጤ ቢሆን ኑሮ ዓለም ባዶዋን ትቀር ነበረ። ለሁሉም ነገር ንግግራችንን ከመቀጠላችን በፊት ትዳር አስፈላጊ ሁኖ ያላገኘህበትን ምክንያት እስቲ አስረዳኝ እባክህን። በቂ ምክንያት ከሰጠኸኝ ምናልባት ደቀ መዝሙርህ እሆን ይሆናል።»

«መቸ አታኸውና ፤ ከሁሉ በፊት ለሥርጉ ድግስ ያለብህ ጣጣ በርበሬንና ጌሾህን ሽምተህ ስታስወቅጥ ፤ ብቅል ጥንስስ፥ መግላሊት ስትል ፤ እንጀራ ስታስጋግር ፤ የእርድ ከብት ስትገዛ ፤ ድንኳን፥ ዋንጫ ፈልጉ ስትል ፤ ይህን ሁሉ አድርገህ ደግሞ ሐሜት ላይቀርልህ መቸም የምታውቀውን ሰው ሁሉ መጥራት አትችልም። እስቲ ልብ በለው ፤ አንድ ወጣት ለዚያች ለአንዲት ቀን ድግስ የሚለፋው ልፋት ጐጆውን ለመሥራት ወይም ለሌላ ጉዳይ ቢያውለው ኑሮ ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ የሚደግፈውን ነገር ሊያቋቁምበት ይችል ነበረ። ይህንንም ሁሉ እንለፈው። ሥርጉን እንደምንም ብለህ አልፈህ እንደገና እፎይ ሳትል ወዲያው ልጅ ከተፍ ይላል። ከእንግዲህ የሰው ልጅ አሳድረህ ፤ ልጆቹ ባስነጠሳቸው ቊጥር ወደ ሐኪም ቤት ሩጠህ ፤ ከፍ እንዳሉ ደግሞ ወደ፥ ትምህርት ቤት መላክ። ከሚስትህ ጋር ደግሞ ይህ ጐደለ ፤ ይህ አለቀ፥ ባለች ቊጥር እየባነንክ ንዝንዙ መከራ። እንዳንዴም ፍች አይጠፋ። ደግሞ መጨረሻው ይህ መሰለህ እንዴ ጉዱ ገና ነው እኮ! ልጆች ሲጐለምሱ ደግሞ ማሳጨት ፤ መዳር ፤ ማፋታት ፤ አማት ፤ ምራት ፤ ተወኝ እባክህን ጣጣው ፈንጣጣው ተቆጥሮ አይዘለቅም። ከዚህ ሁሉ ጭቅጭቅ ምነው ሳያገቡ ቢቀሩ ፤ ሰው የተፈጠረው አንድ ራሱን ሲሆን እዚህ ማጥ ውስጥ ማን ግባ አለው? ለዚህ ለአላፊው ሕይወቱ ራሱን ችሎ ፤ ሥጋውን አስደስቶ ከኖረ መቼ አነሰው? አለ ዓለሙ።

«ትዳር ሞክረህ እንዲህ ብታማርር እንኳ ባማረብህ ነበረ»አለ ብርሃኑ። «በተቀረ ከሩቁ ምን አንገፈገፈህ እባክህን?፥ አንተ በተለይ የፈረኸው ልጅ ወልደው ሲያሳድጉ የሚገጥመውን ድካም ይመስለኛል። እነዚያ መካኖች በመሆናቸው ፤ ልጅ ያልወለዱት ደግሞ ውሻና ፤ ድመት ሲያሳድጉና ለልጅ የነበረውን የወላጅ ፍቅር ለነዚህ አራዊቶች ሲለግሡት የሚኖሩ መሆናቸውን ዘንግተሃል መሰለኝ። ከነዚህ ልጅ ቢሶች ዕድለኞች የሆኑት ደግሞ የሰው ልጅ ያሳድጋሉ። ይህን አድርገው የሆኑት ደግሞ የሰው ልጅ ያሳድጋሉ። ይህን አድርገውም ልባቸው አይደሰት ፤ እስከነ ምሳሌው «ያልወለድኩት ልጅ አባ አባ ሲለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ» ይባላል። አየህ፥ ጠለቅ አድርገህ ብታስብ ፤ የትዳር ሸክም የወንዱ ብቻ አይደለም ፤ ሚስቱ ረዳት አለችው። ልጆች ሲያሳድግ ስለሚደርስበት ድካም ላልከው ፤ ቡሽላ ከማሳደግ የራስን ልጅ ማሳደግ ይሻላል። ደግሞ ከካሻው ሰውዬው ባረጀ ሰዓት የሚተኩት ልጆች አሉት። አንተ የተመለከትኸው የድካሙን ብቻ ነው። እረ ይህን ሁሉ ሐተታ እንተውና ሚስት ማግባትና ዘር መተው ፍጡር የተባለ ሁሉ ዓይነተኛ ተግባር ሲሆን ሰው ከዚህ እንዴት አድርጎ ለማምለጥ የሚችል ይመስልሃል? የሚያስፈራራህ የሥርጉ ድግስ እንደሆነ፥ አንተ እንኳ ዕድሜ ለወላጆችህ ፤ ሐሳብ የለብህም ፤ ሌላ ዓቅም የሚያጥረው ደግሞ እንደ ችሎታው ይደግስ እንጂ ማን ተንጠራራ አለው? ደግሞ ዕድመኞቹ ለትዳር ጀማሪዎቹ የሚያደርጉላቸውን እርዳታ ምነው ዘነጋኸው?»

«እባክህን ሆቴል ነጋዴ ይመስል ይህ ዳስ ደጃፍ የጠረጴዛ ኬሳ ገትሮ መቀበልን አታንሣብኝ» አለ ዓለሙ።

«ይልቁን ስማ ልንገርህ» አለ ብርሃኑ «ትዳር ያለው ሰው ሥራው ውሎ ቤቱ ሲመለስ አባባ፥ አባባ እያሉ የሚቀበሉት ልጆች ፤ የሚፈቅደውን የምታውቅና የምታዘጋጅለት ሚስት፥ በብሩህ ገጽ የምትቀየው ባለቤት ያለችበት የራሱ ቤት ይጠብቀዋል። የቤተ ሰብእ አሳዳሪ በመሆኑ በተሸከመው አላፊነት መጠን ክብሩና ግርማው ያን ያህል ከፍተኛ እንደሚሆን አምናለሁ። ወንደላጤ ግን እንደልቡ ነፃ ነኝ ብሎ ቢፎክርም፥ ዙረቱ ሲደከመው ሹክክ ብሎ ምኝታ ቤቱ ገብቶ ፤ በአልጋው ላይ እንደ ውሻ ጥቅልል ጭብጥ ብሎ ከመተኛት በቀር ምን ኑሮ አለው ብለህ ነው? ሽል ማለቱሳ። ትዳር ለእለቱ እንዲህ ቢያስፈራህ እንኳ ያን ያህል ክፉ አይምሰልህ ፤ ደግሞ ውሎ አድሮ አይቀርልህም። አንድ ሊቅ እንዲህ ሲል የተናገረው አሁን ትዝ አለኝ ፤ ካላችሁበት ነበርኩ ፤ ወዳለሁእብት ትመጣላችሁ።» ታዲያ የማይቀርልህን ነገር ቶሎ ብታደርገው አይሻልም ወይ?»

ብርሃኑ ይህንን ተናግሮ ሲያበቃ ሰዓቱን ቢመለከት እርሱም በጣም መሽቶአል።

«በል መሽ ልሂድልህ ፤ እስቲ ሰሞኑን ደግሞ ብቅ ብዬ ጨዋታችንን እንቀልጥልና የተረታው ሚስት ያገባል» ይልና፥ ስቀው፥ ተሰናብቶ ወደ ቤቱ አመራ።

አቶ ሰብስቤ ልጃቸው ዓለሙ ትዳር እንዲይዝላቸው ምኞታቸው መሆኑኑን ነጋ ጠባ ለባለ ጉዳዩ ከመግለጽና ከመሞታቸው በፊት «አበባውን» እንዲያዩ መናፈቃቸውን ከማስረዳት አልቦዘኑም። ዓለሙ ግን ይህን ሲያነሡበት አባቱን እንደገደሉበትና እርሱንም ሊገድሉ እንደመጡ ያህል ሆኖ እየከፋው አቀርቅሮ በመስማትና እንደ ድዳ ዝም በማለት ይመልስላቸው ነበረ። ደንፍተው ሲበቃቸው ቀስ ብሎ ተነሥቶ መሄድ ልማዱ ሲሆን አንዳንዴ ብቻ ንዴታቸው በዝቶ ወላፈኑ እንዳይደርስበት ሲያሰጋው «እሺ ታገሡኝ» በሚል መልስ ፤ ይሸኛቸው ስለ ነበረ እናቱ እምብዛም ተስፋ አልቆረጡም። አንድ፥ ማታም ሊነጋጋ እስኪል ድረስ እንደዚሁ ሲጨቃጨቁ አመሹና ዓለሙ ሊሄድ ቆረጠ። በማግሥቱም ቤቱን ትቶ በከተማው ወደ ሚገኝኝ ወደ አንድ ሆቴል ገባና ኑሮውን እዚያው ለማድረግ ተመዘገበ

«ሰማሽ ወይዘሮ ይታከቱ» አሉ አቶ ሰብስቤ በሣልስቱ ማታ ቤታቸው በረንዳ ተቀምጠው ከባለቤታቸው ጋር ሲወያዩ «እኔ ሕይወቴን ሙሉ ቀን እስከ ሌሊት የምለፋው ለእርሱ ቅርስ ጉርስ አበጃለሁ ብየ ነበረ። (እህቱ እንደሆች ወደ ባል ቤት መሄድዋ ነውና ስለርስዋ ማሰቡ የባልዋ እንጂ የኛ ጉዳይ አይደለም) እርሱ እንደሆነ ይግረማችሁ ብሎ ጥሎልን ነጐደ። አይ የኛ አበሳ፥ «ስላጐረስኩ እጄን ተነከስኩ፥» አሳድገን እንዲህ መካን ሁነን እንቅር እንዴ። ይህን የመሰለው ልጅ ምነው ሳይወለድ በቀረ!»

ወይዘሮ ይታከቱ እንዲህ ብለው ይመልሳሉ ፤ «አይዞሁ ትዕግሥት ያድርጉ የዓለሙ አባት እስቲ የውጩን ጥቂት ይሞክረውና ተመልሶ መምጣቱ አይቀርም። እንዲህ ሂዶ በዚያው ለመቅረት የሚያደርሰውን አላሰቀየምነውም፥ የሚጨክንብን አይመስለኝም» ይሉና ዕንባቸውን ርግፍ ርግፍ ያደርጋሉ።

«አይሄሄ!» አሉ አቶ ሰብስቤ ፤ እኩያዎቹ እኮ ሦስትና አራት ወልድዋል። የእግዜር ነገር አይታወቅም እንጂ ከእንግዲህ ወዲያ ሰው ይሆናል ብለሽ ነው? እርሱን ተስፋ ማድረግ

ንፋስን መከተል ያህል ነው። ይልቁን ብርድ ተነሥቶአልና ቤት እንግባ» ብለው ወደ ቤት ገብተው ሌላ ተግባር በማሰብ የዓለሙን ነገር ለመርሳት ይጣጣራሉ።

* * *

የዓለሙ አዲሱ ቤት በከተማው መካከል በአራዳ የሚገኝ የተዋበ ሕንፃ ነበረ። የተመደበለት ክፍል ጽዳትም በአባቱ ቤት ከነበረው የምኝታ ክፍል ጋር ይወዳደራል እንጂ አያንስም። በዚህ በአዲሱ አካባቢውና በወላጆቹ ቤት መካከል የነበረው ልዩነት ግን በሆቴሉ የሚወጣበት እና የሚገባበትን ሰዓት የሚታዘበው ነዝናዛ ፍጡር አለመኖሩ ነው። አምሽቶ በገባ ቍጥር ይወቅሱት የነበረውና ያ የማያስፈልገው መቆጣጠር ቀርቶለት ስድ በመሆኑ ለሰው ልጅ የሚገባውን መብት እንዳገኘ ሆኖ ተሰማው። አይ ሆቴል መመቸቱ! በበዓል ቀን እስካሰኘው ሰዓት ድረስ እንዳይተኛ ቤቶቹ «ቤተ ክርስቲያን እንሂድ» እያሉ ሲያበሳጩት የነበረው አሁን ቀርቶአል። በእውነት የገዛ ራሱ ጌታ የሆነው ዛሬ ነው፡ የሆቴሉ ኑሮ አሰልቺ እንዳይሆንበትም አብረውት የሰፈሩት አንዳንድ የእርሱ መሳይ እንግዶች አልታጡም። በበረሃ የሚጓዙ መንገደኞች ለጋራ ጥቅማቸው ሲሉ እንደሚቀራረቡ ሁሉ፥ ዓለሙም ከመሰሎቹ የሆቴል እንግዶች ጋር ተዋወቀና መድረሻው ተመሳሳይ ሁኖ በሐሳብ በመግባባታቸው የመንፈስ ወንድማችነታቸው ከመ ቅጽበት ተወልዶ ወዲያ ወዲያው ሥር ሰደደ።

ሆቴል ለአገሩ እንግዳ ፤ ለሰዉ ባዳ ለሆነ ሰውና ለጨዋ ልጅ መኖሪያ በመሆኑ በዓለሙ ልብ ውስጥ የቅርታ ፤ ሽውታ ስሜት ያሳደረው የወጭው ጉዳይ ነበረ እንጂ ከልዩ ልዩ ዓይነት ሰው ጋር በመተዋወቅና ከወጉ ከንግግሩ ይሸመት የነበረው ፍልስፍና ፤ ሰው ከሰው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ማኅበራዊ ግንኙነት ስልቱን በመረዳት በሌላ አኳኋን ሊገኝ የማይቻለውን ጥበብ ያገኝ እንደ ነበረ ሆኖ ተሰማው። ግንኙነቱም ቢሆን የበላይና የበታች ሳይኖርበት እኩያ ለእኩያ ነው። «ገንዘቡ እንደሆነ ደግሞ ምን አለበት። በእጅ ካለ ይከፈላል ፤ ለዕለቱ ከሌለ ደግሞ ተበድሮም ቢሆን ይከፈላል ፤ ሰው ሁኖ የማይቸገርና የማይበደር የለም» እያለ ዓለሙ ራሱን ያጽናና ነበረ።

ዓውደ ዓመት እና የዕረፍት ቀን ሁኖ ወደ ሥራው በማይሄድበት ጊዜአትም ዓለሙ ከጓደኝኖቹና የደስታው ተሳታፊዎች ከሆኑ ሌሎች እንግዶች ጋር ሲቀናው በመኪና በተቀረ በአውቶብስ ተሳፍረው ወደከተማው ገጠር እያመሩ መዝናናትና ንጹሕ አየር በጠርሙሶች ከሰነሰቁት የጉሮሮ ማራሻ ፤ የሕይወት ማደሻ ጋር እያስማሙ መመገብ የሰርክ ተግባሩ ነበረ። ከዚያ ምላሽም ድካም ባልተሰማው ጊዜ ሲኒማ መግባት ፤ ካሰኘውም ለማዕረጉ ተገቢ በሆነ ቡና ቤት እየሄደ በመደነስና አእምሮን የሚያበራ ወግ በማውጋት ጊዜውን ያሳልፋል። ይህን የመስለ ከሃሳብ ነፃ የሆነ ሕይወት እያለ ወላጆቹ ሚስት እያገባ ይወተውቱት የነበረው ሁሉ ለረቡ እንዳለነበረ አሁን ጉልህ የሆነለት መሰለው። ደግሞ በታሪክ ውስጥ በመካከላቸው እነ ቅዱስ ጳውሎስን፥ ሾፐንሀወርንና ኒቸ ኤፒክዩርስን የመሳሰሉት ሊቃውንት የሚገኙባቸውን እየጠቀሰ እርሱም ከፍጹም ልቡ ደቀ መዝሙራቸው መሆኑን አረጋገጠ። በተለይም ቅዱስ ጳውሎስ «ከመግባት አለመግባት ይሻላል» ባለው በጣም ያስብ ነበረ።

ልጅነት ሠርከ አይገኝም፥ ጤንነት ዘወትር የለም ፤ የወጣትነት ጊዜስ እንደምን ይለፍ፥ ሕመም ወይ እርጅና በመጣበት ሰዓትሳ የወንደላጤ ፍጻሜ ምን ይሆን ይሆን?» የሚል ጥያቄ አንዳንዴ ሳይፈልገው በሃሳቡ ውስጥ ጣልቃ ሲገባበት «በመጣ ጊዜ ይታሰብበት» እያለ ሕሊናውን አሳረፈ።

# ምዕራፍ ስምንት።

# የትምህርት ትርጉም።

*ዓመታዊ ፈተና ተፈጽሞአል። ብርሃኑና መኰሪያም ዓመታቱን ተግተው በመማር ይህንን በደኅና ስላለፉት የእነርሱን ያህል ደስ ያለው ሰው ይኖር ይሆን? እንግዲህ ይህን ሁለተኛውን ኬላ ካለፉ ፤ ከባሕር ማዶ ወደ አንዱ አገር ሂደው ትምህርታቸውን የመፈጸም መልካም ዕድል ዕጣቸው እንዲሆን ባለ ሙሉ ተስፋ ናቸው።*

*የነቅዓ ጥበብ ትምህርት ቤት ግቢ ፤ ተዋበች ሙሽራ በሰንደቅ ዓላማዎች ተሸልማ ስነ በዓሉን ለመከፈል የመጡትን እንግዶች ትቀበላለች። ዛሬ መጨረሻው የትምህርት ቤት ቀን ነው። የምስክር ወረቀቶቹን ለመስጠት ገናናው ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት በመካከላቸው በመገኘታቸው ፤ ተማሪዎቹ ወዲህ ስለ ይህ መልካም ዕድላቸው፥ ወዲህም የአያሌ ዓመታት ትምህርታቸውን ስላከናወኑ ደስታቸው ዕጥፍ ነበረ። ዓመታት ትምህርታቸውን ስላከናወኑ ደስታቸው ዕጥፍ ነበረ። በዓሉ የሚፈጸምበት የጉባኤው አዳራሽም በአበባ ፤ በሰንደቅ ዓላማና በሚያምሩ ስዕሎች ተሸልሞ አጊጦአል።*

*እነ ብርሃኑ ብዙ ዓመታት የጣሩበትና በናፍቆት ሲጠብቁት የነበረው የምስክር ወረቀታቸውን ከንጉሥ ነገሥቱ እጅ ለመቀበል ስማቸው እስኪጣራ ድረስ በተቀመጡበት ቦታ ልባቸው ፍርሃት ፍርሃት እያለው ቆይተው ተራቸው ሲደርስ እጅ እየነሡ ዕድለኞቹ፥ ተማሪዎች የምክር ወረቀታቸውን ወሰዱ። ይኸው ወረቀት ለተማሪዎቹ ተሰጥቶ እንደ ተፈጸመም የትምህርት ቤቱ አለቃ ዶክተር ጴጥሮስ አብርሃም አስተዋጽኦውን ከዚህ ቀጥሎ የምናቀርበውን ጠሊቅ የምክር ቃላት ያዘለ ንግግር አደረጉ፡-*

<u>*የዶክተር ጴጥሮስ አብርሃም ንግግር፡-*</u>

*ከዚህ በነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በት ትምህርታችሁን ለፈጸማችሁት ልጆች የምስክር ወረቀት የመስጠትን ስነ ሥርዓት ለማከበር መሰብሰባችን በጣም ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። ይልቁንም ተወዳጅና ገናናው ንጉሥ ነገሥታችን መልካም ፈቃዳቸው ሁኖ በዓሉን ሊካፈሉ በመካከላችን መገኘታቸው ደስታችን ላይ ደስታ ይጨምርልናል። ከእናንተ ተማሪዎች ብዙዎቻችሁ እንግዲህ የትምህርት ቤት ኑሮው በቅቶአቸው ከአስተማሪዎችና ከፈተናዎች ነፃ ልትወጡ ስትሆኑ ፤ ጥቂቶቻችሁ ግን ትምህርታችሁን በከፍተኞች ትምህርት ቤቶች ልትቀጥሉ ናችሁ። ስለዚህ ይህ ቀን ለአብዛኛዎቻችሁ የመጨረሻው የተማሪነት ቀን ይሆን ይሆናል። ከሞግዚቶች መሪነት ወጥታችሁ በገዛ*

ሐሳባችሁ እንደ ፈቃዳችሁ ለመኖር ወደ ሰፊው ዓለም ስትገቡ፥ አብረን የነበርንበት ጊዜ መታሰቢያ እንዲሆናችሁ ጥቂት የምክር ቃላት ላበረክትላችሁ እወዳለሁ ይህ ምክርም፥ ዕድል አግኝተው የእናንተን ያህል የተማሩ ብዙዎች ልጆች እስከ አሁን ድረስ የሉምና «እንበልጣለን» የማለት ሐሳብ በአእምሮአችሁ ውስጥ እንዳታገቡ ፤ ትምህርት የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ምን እንደሆነ ባጭሩ ስገልጽላችሁ ታግሳችሁ እንድትሰሙ እለምናችሁአለሁ።

«በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ» የሚለውን ንግግር ሁላችሁም ታስታውሱታላችሁ። እንግዲህ የትምህርት ቀደምት አገልግሎት አንድ ብልሃት አውቀን በዚሁ እየሠራን ደሞዝ አግኝተን ለሕይወታችን የሚያስፈልገውን ለመግዛት እንዲያስችለን መሆኑን ማንም አይስተውም። በድካም ምግብ ማግኘትን ደግሞ አእምሮ ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን ፤ እስትንፋስ ያለው ፍጡር ሁሉ የሚፈጽመው ተግባር ነው። ወፍም ሆነ ጉንዳን ምግቡን ካለበት ሂዶ ይፈልገዋል እንጂ በአንድ ቦታ ቁጭ ብሎ ምግቡ አይመጣለትም።

ነገር ግን በዓለም ስንኖር ሳለን ከሥራ ችሎታ በቀር ደግሞ ብዙ ሌላ ችሎታ ያሻልና። በሥራ ችሎታቸው ለፍተው ያገኙትን በቂ ገንዘብ በማስተዋል ወጭ ማድረጉ እየተሳናቸው ቁም ነገር ላይ ሳያውሉት በትነውት የሚቀሩ፥ እንዲያውም በገዛ ገንዘባቸው ጤናቸውን አሰናክለው ሕይወታቸውን ባጭሩ የሚያስቀሩ ስንትና ስንት ናቸው? ልዩ ልዩ ሱስ እያበጁ በመጨረሻ የዚህ ሱስ ተገዥዎች ሁነው የቀሩና ያገኙን ገንዘብ ሁሉ የሱስ ማርኪያ፥ የአመል መከሊያ ብቻ በማድረግ ዕድሜአቸውን የፈጁ ሰዎች ብዛታቸው ሊታወቅ ይቻል ይሆን? የሥራ ችሎታ አልጐደላቸውም። ነገር ግን ሕይወታቸውን ወደፊት ለማሻሻል አንድ ግብ ወስነው፥ ከየዕለቱ ልፋታቸው የሚያገኙት ፍሬ ወደዚያ ግብ እንዲያደርሱ እንደሚረዳቸው በማድረግ ፈንታ በአንዲት ጠባብ መንገድ፥ በአንዲት ቀጭን መስመር ብቻ ሲመላለሱ፥ የትም ሳይደርሱ ተቀጭተው የሚቀሩት የሰው ልጆች ልክ የላቸውም። ስለዚህ ትምህርት አግኝቼአለሁ! ብሎ የሚያስበው ሰው የሕይወቱን መምሪያ ቅን ፍልስፍና ለይቶ ያውቀ መሆን አለበት። በልቡ ውስጥ ዕውቀት፥ ንዋይና ደስታ ምን ምን ያህል ስፍራ ሊሰጡ እንደሚገባቸውና ከነዚህ አንዱ ያንዱን ድንበር እንዳያልፍ ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስችለው በቂ ማስተዋል እንዲኖረው ያሻል።

በዓለም ውስጥ ከመሰሉ ጋራ ተስማምቶ ሊቀመጥ ባለመቻሉ ከሁሉም ጋራ ሲነታረክ የሚኖረው ሰው ከዚህ ቀደም ሳይገጥመን አልቀረም። ይህ ሰው በልጅነቱ ከወንድሞቹና ከአብሮ አደጎቹ ጋራ በመጣላት ይጀምርና፥ ሲያድግ ከሥራ አለቆቹ ፤ ከዘመዶቹ ፤ ከሚስቱ ፤ ከአማቶቹ ፤ ከልጆቹ፥ ከጐረቤቶቹ ከጓደኞቹ ባጭሩ ከእነርሱ ጋራ ግንኙእንት ካለው ሰው ሁሉ ጋራ በትንሹም በትልቁም ነገር ሲጨቃጨቅ ይኖራል። ምክንያቱሳ? ለእርሱ እንደሚመስለው እርሱ ብቻ ትክክለኛውን የተከተለ ሲሆን የቀሩት ሁሉ ተሳስተዋል። «እገሌ እኮ እንዲህ አደረገኝ» ብሎ ዛሬ ከበቀለ ጋራ ተነጋግሮ እንደሆነ ፤ ይጫወታል። ይህ ሰው ይክት ተግባሩ ጭቅጭቅ እንደሆነ ለማለት ይቻላል። ለአጥቢያው የፖሊስ ጣቢያ ዘወትር የማይሰለች ደንበኛ ስለሆነ ፖሊሶቹ ሁሉ ያውቁታል። «በጥባጭ ካለ ማ ጥሩ ይጠጣል» ተብሎ የተተረተው በእርሱ ብጤ ሰበብ ሳይሆን ይቀራል

ትላላችሁን? ይህን የመሰለ አመል ያለው ሰው ብዙ ዕውቀት ቢሰበስብ እንኳ በእውነት ተማርኩ ብሎ መናገር አይገባውም።

የተማረ ሰው ካልተማረው የማይለይበት ምክንያቱ ፤ የተማሪው፥ ሰው በፈቃዱ ሕግን ሲያከብር ያልተማረው ሰው ግን የቅጣት ፍራቻ ብቻ አስገድዶት ሕግን በማክበሩ እንደሆነ ይባላል። የተማረ ሰው የውጭ ምልክቱ ፤ ሰውነቱ ልብሱና መርኖሪው ንጹሕ ነው። በአገባብ ስለሚሄድና ስለሚናገር ሁኔታው ትሕትና የተሞላ ነው። ሥራው የታረመ ነው። አእምሮው ለራሱ ምቾትና ድሎት በማሰብ ብቻ የታጠረ ሳይሆን ፤ ለጐረቤቶቹ ፤ ለሰፈሩና በሰፊውም ለአገሩ ማሰብ ተግባሩ መሆኑን በማወቁ ፤ አላፊነቱን ይፈጽማል። በተቻለው መጠን ሌሎችን ለመርዳት ዝግጁ ነው። ይህ ሰው ስስት ፤ ቅናት ፤ የራስ ፍቅር ፤ ስንፍና እና ቁጣ የመሳሰሉትን መጥፎ የባሕሪ ጉድለቶች ሁሉ አርሞ ፤ ከሌላው ፍጡር፥ ሁሉ የበላይ ሆኖ ለተፈጠረባት ደረጃ ተገቢ ሁኖ፥ እንዲገኝ ሁሉ ቀን ሲጣጣር ይኖራል። መንፈሱና ሐሳቡ ንጹሕ እንዲሆን ሳይሰለች ይታገላል።

ከእንግዲህ እናንተ ትምህርት ቤትን ትታችሁ ወደ ሰፊው ዓለም የምትገቡ ወጣቶች ከአባታችሁ ተላልፎ ወደ እናንተ ለደረሰው አገር እና ለዘመናችሁ ማማር ወይም መከፋት የግል አላፊነት እንዳለባችሁና ሌላ አላፊ እንደሌለ ተረድታችሁ የጥሪአችሁን ከፍተኛነት አክብራችሁ እንድትኖሩ፥ በምትሔዱበት ስፍራ ሁሉ ብርታትና መልካም ዕድል እንዲገጥማችሁ እየተመኘሁላችሁ፥ ለአባቶቻችሁ አገር ታማኞች ሁናችሁ እንድትገኙ ያልኩትን ደግሜ እያሳሰብኩ ንግግሬን አቆማለሁ። ለዚሁም እግዚአብሔር ይርዳችሁ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር»

የዶክተር ጴጥሮስ አብርሃም ንግግር እንደ ተፈጸመና ጭብጨባው ዝግ እንዳለ ግርማዊነታቸው ቀጥሎ የተመለከተውን ንግግር አሰሙ።

<u>ግርማዊነታቸው ንግግር።</u>

«.... የሰው የጐልማሳነቱ ወራት በሚቀረው ሕይወቱ የሚደርሰውን ዘመን ፤ የሚጋራበት ጊዜ ስለሆነ፥ ራሱን የሚገዛበት ዓቅም የሚያከማቸው በዚህ ወራት ነው። የሰውም ዕድል በዛሬው ዘመን ከአስተዳደጉና ከትምህርቱ ጋራ የተያያዘ ነው። መልካሙን አስተዳደግ ያለፈው ጐልማሳ ምኞቶች ሁሉ ከፍ ወዳለው ግብ ይንጠራራሉ። ይህም የሚገኘው አሁን እንዳቆምነው ባለ የልጅነት ትምህርት አልፎ ወደ ከፍተኛው ደረጃ በሚደርስበት የጐልማስነት ወራቶች በሚለሰልሱበት ትምህርት ቤት ነው። ለኢትዮጵያ ልጆች የትልቅ የትንሽ ወገን ሳይባባሉ ማን መሆናቸውን ራሳቸው የሚያሳውቁበት ይህን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አቁመንላቸዋል።....»

በዚህ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ጐልማሶች ለሕይወታቸው መሪ የሚሆን ትምህርት ለመስጠት የቀረባችሁ መምህራኖች ሥራችሁ ከባድ መሆኑ የታወቀ ነው። የሱ ሕይወት ወደ በጎ ጐዳና የሚመራበትን መብራት ለእያንዳንዱ ተማሪያቸው እንደ አቅሙና እንደ

ስጦታው በእጁ ማስጨበጥ አለባችሁ። መብራቱንም የሚያውለበልበው ንፋስ ምንም ብርቱ መሆኑ ቢታወቅ ተማሪዎቻችሁ ተግቡን፥ አልፈው በቀን በቀኑ፥ ያለመሰልቸት በምታለሰልሱት አእምሮአቸው እግዚአብሔርንና አገራቸውን ንጉሠ ነገሥታቸውንም ለማገልገል እንዲበቁ ተስፋ እናደርጋለን። ከዚህም ፍጻሜ የበለጠና የተከበረ ነገር አይገኝም።

እናንተ ጐልማሶች ምንም ስጦታችሁ ለየብቻው ቢሆን ተርታ ስጦታ ያለው እንኳ ጠንክሮ በመሥራት ታላቁን አስተዋይነት ለመግዛት የሚችል መሆኑን ዕወቁ። በአናንተም ዘንድ በጎ ባሕርይና ጽኑ ጠባይ ያደረ እንደሆነ ሰው ራሱን ሰው የሚያደርግበትንና ለራሱ ዋጋ የሚሰጥበትን በዚህ ትምህርት ቤት ገንዘባችሁ ታደርጉታላችሁ። የሰው ትልቅነትና ትንሽነት የሚመሰረተው እንደ አስተዋይነቱ መጠንና በበጎ ባሕርይ በጽኑ ጠባይ ነው። በመካከላችሁም በዕድሜ የምትቀዳደሙ ብትኖሩ ሁላችሁም ዛሬ በዚህ ትምርህት ቤት ደጃፍ ወደ ሕይወት መለቂያ በር ደርሳችኋል። ጊዜያችሁን ሁሉ አስተዋይነትን ለመግዛት፥ በበጎ ባሕርይ የሚፈጸሙትን ለመልመድ፥ ጽኑ ጠባይን ለማግኘት በሥራ አሳልፉ። አእምሮአችሁንም በአስተማሪዎቻችሁ ሞግዚትነት በዚህ ትምህርት ቤት አሳድጉ። ለወገኖቻችሁና ላገራችሁ ክብር ለእኛም ደስታ የምትሆኑበት ቀን በቅርብ ጊዜ ይደርሳል። የእኛንም ውለታ የምትመልሱት እንዲህ በማድረግ ነው።... በአእምሮ ጠንክሩ፥ በሥራ ጠንክሩ፥ በሃይማኖት ጠንክሩ፥ በተስፋ ጠንክሩ፥ የመጨረሻውን ዕድልና የድል አክሊል ትወርሳላችሁ።... ኢትዮጵያ እናንተንና እናንተን የመሰሉትን የልጆችዋን አገልግሎት ትጠብቃለች።»

የግርማዊነታቸው ንግግር እንደ ተፈጸመ የተማሪዎቹና የተሰበሰበው ሕዝብ ጭብጨባ አዳራሹን ሦስቴ ሞላው። ዶክተር ጴጥሮስም በራሳቸውና በተማሪዎቹ ስም ሁነው ስለ አባታዊው ጥበብ የተሞላ ንጉሣዊ ምክር ግርማዊነታቸውን አመስግነው ሲያበቁ የተሰበሰበውን ሕዝብ ቁሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘመረና የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ።

# ጉዞ ወደ ፈረንጅ አገር።

ብርሃኑና መኰሪያ በትምህርት ሚኒስቴር እንዲገኙ የሚል የስልክ መልእክት መቀበላቸውን የትምህርት ቤቱ አለቃ ለልጆቹ ነገሩአቸው። ልጆቹ ወደ ትምህርት



ገጽ ፳፯። የኢትዮጵያ ስም እምዲልቅ....

ሚኒስቴር እንደ ደረሱም ወደ ዋናው ዲሬክተር ወዲያው ቀረቡና ከእኒሁ ባለሥልጣን አንደበት እነዚህን ቃላት ሰሙ «.... ዛሬ ወደዚህ የጠራሁአችሁ፥ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ስም ሆኜ፥ ትምህርታችሁን በውጭ አገር እንድትቀጥሉ የተመረጣችሁ መሆናችሁን እንድነግራችሁ ነው። ይህ ድንቅ ዕድል የሚገጥመው ከተማሪዎች መካከል ከስንቱ ለአንዱ መሆኑን አሳምራችሁ ታውቃላችሁ። በመግንሥት ትምህርት ቤት ከገባችሁበት ቀን አንሥቶ ፈረንጅ አገር ከርማችሁ እስክትመለሱ ድረስ ለእያንዳንዳችሁ ከ፺ ሺሕ ብር የሚበልጥ ወጭ የሚደረግ መሆኑን አትዘንጉ። በግብርና በቀረጥ ከገበሬው ከነጋደውና ከማናቸውም ዓይነት ሠራተኛ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ድሀ ወይም ሀብታም ሳይባል ተጠራቅሞ ይህን ያህል ወጭ ሲደረላችሁ፥ እናንተም ለውዲቱ አገራችሁ የግል ጥቅም የሌለበት ቅን አገልግሎታችሁን በማበርከት ውለታዋን እንድትመልሱ መትጋት እንደአለባችሁ ለዚሁ እግዚአብሔር እንዲያበቃችሁ እየተመኘሁላችሁ ነው። ሐሙስ በሦስት ሰዓት እዚህ ተገኙና ግርማዊነታቸውን ልትሰናበቱ ወደ ቤተ መንግሥት እወስዳችሁአለሁ። ለልብሳችሁና ለመንገድ መሰናዶ የሚያስገልጋችሁን ገንዘብ ተዘጋጅቶላችሁአል ፤ አሁን ሂዱና ከሂሳብ ክፍል ተቀበሉ።...»

ልጆቹ ይህን በሰሙ ጊዜ፥ አቤት፥ የተሰማቸው ደስታ! አንዳንዱ ሳቁ፥ አንዳንዱም ዝለሉ ዝለሉ አሰኛቸው። የምሥራቹን ለዘመድ ወዳጅ ለመንገር የቤታቸውን መንገድ እርዝማኔ የመንፈቅ ጉዞ ሆኖ ተሰማቸው። የዕድላቸውን ነገር እየተጨዋወቱ መንገድ ለመንገድ ሲሄዱም ወጭ ወራጁን ልብ ለማድረግ ዓይናቸው በደስታ ታውሮ ከእርሱ በቀር ሌላ ሰው በዓለም ውስጥ ያለ ሆኖ አልታያቸውም። በፊታቸው የቆያቸውን የሚያውቁትን ሰው ግን እንቅ አድርጎ መሳም ብቻ ነው። ምክንያቱን ለመንገር ግን አላገኙም።

ቤተ ዘመድ ይህን ውብ ወሬ በሰማ ጊዜ እግዚአብሔርን ከማመስገንና መንግሥትን ከመመረቅ ሊታገሥ አልቻለም። «ሰማህ ልጄ ብርሃኑ» አሉ አቶ ዓባይ ይህንኑ ጉዳይ ከልጃቸው ጋር ሲጨዋወቱ «ነፃነት ምን ማለት እንደሆነ አሁን ትረዳዋለህ ወይ? ጠላት እንደሆነ ሁለተኛ ደረጃ ይቅርና ፤ ዩኒቨርሲቲማ አይታለምም፥ ዱሮ ተቋቁመው የነበሩትን ትምህርት ቤቶች ሁሉ ድፍን አድርጎ ዘግቶ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ከብት ሆኖ እንዲቀርብለት ቀን እስከ ሌሊት ይደክም ነበረ። ነገር ግን ለሥላሴዎች ምሥጋናው ይግባ፥ ሰንደቅ ዓላማችን ትለምልም፥ ንጉሠ ነገሥታችን ውለው ይግቡ ፤ አሁን ከናንተ ካልጐደለ በቀር ሰው በዓለም ሲኖር ሊገጥመው የሚችል ትልቁ ዕድል እንግዲህ ይኸው ደረሳችሁ። እኛ ዘመዶቻችሁም ከዚህ ወዲያ ደስ የሚል የምንመኘው ነገር የለንም። በል እስቲ በርታና ፍሬህን አሳይ!»

«እናንተ ወጣቶች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ስትሄዱና ከተማራችሁ በኋላ ስለሚገጥማችሁ መልካም ዕድል ስታስቡ፥ በበቂ ደመወዝ፥ ሹመት፥ ነጭ እንጀራና ገንዘብ ሊያመጣው በሚችል ደስታ ብቻ ትወሰናላችሁ። ሳይማሩ እነዚህን ነገሮች ለማግኘት የታደሉ ሰዎች አይታጡምና ለእነርሱ የሚጐድላቸው ምን እንደ ሆነ፥ ወይም ከፍተኛ ትምህርት ሊያስገኘው የሚችል ከዚህ ከተባለው የበለጠ ሀብት ምን እንደ ሆነ ለማሰብ ጊዜ ያገኛችሁ አይመስለኝም። ያልተማረው ሰው ወደ ስነ ጥበብ ፤ ወደ ፍልስፍና፥ ወደ ታሪክና

ወደ ሌላው ወሰን ማለቂያ ወደ ሌለበት ንጹሕ የዕውቀት ዓለም ውስጥ እንዳይገባ በድንቁርናው ወህኒ ውስጥ ተግዞ ከሚኖረው ነፃ መሆናችሁን አእምሮአችሁና ብርታታችሁ እስከሚፈቅደው ድረስ በዕውቀት ጐዳና ልትጓዙ የምትችሉ መሆናችሁን ከሀብት አትቄጥሩትም። የዚህ የሰፊው መንግሥት ባለ ሙሉ መብት ዜጋዎች እንድትሆኑ የሚፈቅድላችሁን የትምህርት የይለፍ ወረቀት እንደሚገባው መጠን ዋጋ አትሰጡትም። ግን ጥንትም አባቶቻችን በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል...ብለው ተርተዋል።

«የሥጋ ባርነት የመንፈስ ባርነት እንደሚያስከትል የሥጋ ነፃነትም የመንፈስ ነፃነትን ያመጣልና ዕድላችሁ ምንኛ ትልቅ እንደሆነ ዕወቁ።

«ደግሞ በሌላው በኩል ሰፊውን ዓለም ስታዩ አገራችን የዓለም እንብርት ናት ከሚለው ጠባብ አስተያየት የምትፈወሱ መሆናችሁን አትዘንጉ።»

*   *   *

ብርሃኑና መኩሪያ ለቤተ መንግሥቱ ግቢ እንግዶች አልነበሩም። በዓመት በዓመት ለክብረ ባአላትና ሽልማት ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ለመቀበል እየገቡ በጣም የሚያውቁት ቢሆን እንኳ ፤ ይህ አምሳለ ኤደን ገነት የሆነ ግቢ ለተመልካቹ ዓይን ዘወትር አዲስ፥ ግርማማ፥ ውበቱ ታይቶ የማይጠገብ፥ የአትክልቱና የአበባው መዓዛ የጣፈጠ ነበረ። ይልቁንም የነፃነቱ ምልክት የሆኑት ተወዳጆቹ ሦስት ቀለሞች በዚህ ዓጸድ ማከከል ጫፉ ሰማይ በሚደርሰው ምሰሶ ላይ ሲወለበለብ የሚመለከተው ኢትዮጵያዊ ልቡን ደስታና ኩራት እንደምን ሳይሞላው ይቀራል!

ዕድሞች ልጆች እንደ ቀድሞው ሳይሆን ዛሬ አመጣጣቸው ልዩ ነው። በእልፍኝ አስከልካዩ ተመርተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን አዳራሽ ገቡ። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለጥ ብለው እጅ እንደ ነሡ፥ ወደ ጌቶቹ ዙፋን ጠጋ እንዲሉ ተነግረው ለቀረቡላቸው አባታዊ ጥያቄዎች መልስ ከሰጡ በኋላ ከገናናው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የተሰጣቸውን ንጉሣዊ የምክር ቃል ከዚህ ቀጥሎ አትመነዋል።

«የሚበቃ ዕውቀት እንድታገኙ ብትተጉ ብትጣጣሩና ብትማሩ የሚንቁዋችሁ ያከብሩዋችኋል፥ የሚጠሉዋችሁ ይዋዱዋችኋል።

«እግዚአብሔር እኛን ለኻያ ሚሊዮን ሕዝብ ጠባቂ እንድንሆን ሲመርጠን ፤ የምንኮራባችሁ ከሁሉ ይልቅ በትምህርት ቤት ባላችሁት ነው። እንደዚህም ሲባል የቀሩት ትምህርት ስለጐደላቸው ነው እንጂ የማንኮራባቸውና የነቀፍናቸው ሆኖ አይደለም። ስለዚህ...ፍሬያችሁን እንድታሳዩ ምኞታችን ነው። ከዛሬ ቀደምም ከብዙዎቹ ፍሬ አግኝተንባቸዋል። እግዚአብሔር በምትሄዱበት አገር ትምህርታችሁ እንዲከናወንላችሁ ረድቶ በደህና አገራችሁ ይመልሳችሁ።»

«ግርማዊነታቸው ንግግር በኋላ ከሁለቱ ተማሪዎች አንደኛቸው መኩሪያ በላይ እነዚህን ቃላት ተናገረ፦

## ግርማዊ ጃንሆይ!

«ግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ትምህርታችንን በውጭ አገር እንድንቀጥል ለዚህ ትልቅ ዕድል ያበቃንን ፈጣሪ ከሙል ልባችን እናመሰግናለን። የኢትዮጵያ ስም እንዲልቅ ፤ ለሕዝቡ እድገትና ላገሩ ልማት ግርማዊነትዎን ቀን እስከ ሌሊት የደከምመውንና የሚደክመውን እኛ በዕድሜ አነሥተኞች የሆንነው ዜጎችዎም ሳንቀር በጉልህ የተመለከትነው ነው። እኛም ብውጭ አገር ትምህርት ቀስመን ተመልሰን የግርማዊነትዎ ቅን አገልጋዮች በመሆን በተደረገልን ችሮታ መጠን ውለታ እንድንመለስ ያበቃን ዘንድ አምላክን ዘወትር እንለምነዋለን። ግርማዊነትዎ ሺሕ ዓመት ይንገሥ!»

*   *   *

እነ ብርሃኑ ለጉዞው ሲሰናዱ ሰንብተው ከብዙ ቀን በኋላ ወደሚደረሰው አዲሱ ትምህርት ቤታቸው ለመሳፈር ዛሬ ጠዋት በዘመድ ወዳጅ ታጅበው ወደ አይሮፕላን ጣቢያ ደረሱ። ምንም አካሄዳቸው ለደግ ቢሆን እንኳ ፤ ከሚያፈቅሩት ሰው ቀርቶ ከተለማመዱት ጠላት እንኳ መለያየት አስደሳች አይደለምና የመለያየት ምጥ በሸኚዎችና በተሸኚዎች ግንባር ላይ ተስሎ ይታይ ነበረ።

አይሮፕላኑ መነሻው ሲሆንም ልጆቹ ከዘመዶቻቸው ጋር ሲሳሳሙ ሁለቱም ወገን ዕንባቸውን ሊገቱ አልቻሉም። መሐረሞች ገሚሶቹ ከኪስ ፤ አብዛኛዎቹ ግን ከቦርሳ እየተመዘዙ ሁሉም በይፉ ይጠቀምባቸው ጀመረ። ደግነቱ በራሪው ወዲያው፥ ተነሥቶ ገላገላቸው። ሰማዩን እየቀዘፈ ሲያጓብብ ተጨለጠና ከጥቂት ሴክኮንድ በኋላ ትንኝ ያህል ሆኖ ሲታይ ቆይቶ ለዓይን ጠፋ። ሸኚዎችም መቸስ ምን ይደረግ ወደ እየቤታቸው ተመለሱ።

ልጆቹ በአረግራጊው ወንበር ተቀምጠው ለጥቂቶች ዓመታት የሚለዩትን በዓለም የተፈቀደላቸውን አጭር ዕድሜ እንዲኖርበት ከፈጣሪ የተመደበላቸውን ድርሻ ተናፋቂ አገራቸውን ከአይሮፕላን መስኮት ቁልቍል ይመለከቱ ነበረ። ከሰማይ ሁነው ቁልቁል ሲመለከቱ ግርድፉ ቀርቶ ውብ ውብ ብቻ የሚታየው የሸንተረሩ የወንዙና የእርሻው ማማር የአገራቸውን ፍቅር መልሶ ቀሰቀሰባቸውና ዕንባ እንቅ እንቅ ያደርጋቸው ጀመረ። እንዲህ የሚለውን ድሮ በልጅነታቸው በትምህርት ቤት ይዘምሩት የነበረውን ምዝሙር አስታውሱና ዛሬ ካንጀታቸው ይዘምሩት ጀመረ፡-

መመለሴ አይቀርም አምላክ ቢረዳኝ

ተለየሁሽ አገር ሳለሁ ደኅና ሁኚ

በሰው አገር ሳለሁ እንዳትናፍቂኝ።.....»

ይህን ከዚህ ቀደም እንደዛሬው አምሮ ያልታያቸውን የአበባዎቻቸውን አገር እያደነቁ ከአሞራዎች ጋራ ሲያንጃብበት ምናልባት ተመልሰው የማያዩት የመሆናቸው ጭልምልም ያለ ሐሳብ በልባቸው፥ ውስጥ ስለ ነበረ ፤ ሰፊውን ዓለም የማየትና ትምህርታቸውን

በትልልቆች ትምህርት ቤቶች የመቀጠል የገጠማቸው ትልቅ ዕድል የሚያሰማቸው ደስታ ከሐዘን ጋር የተደባለቀ ሆነ። በአገራቸው ትተዋቸው የሄዱትን ዘመዶቻቸውንና አብሮ አደጎቻቸውን እያስተወሱ ማን በሞት ተለይቶ ማን በሕይወት ይቆየን ይሆን እያሉ ሲያስቡ ፤ አይሮፕላኑ የኢትዮጵያን መሬት ጨርሶ ባሕረ ኤርትራን ላይ ሲበር ውሎ በምድረ ግብፅ ጣቢያ ላይ ሲያርፍ ብቻ ከሐሳብ ሕልማቸው ብንን አሉ። በሕልማቸው መካከልም «አገሬ ስመለስ ይህን እሠራለሁ ይህን እፈጥራለሁ....» የሚል ሐሳብ በብዙው እንደነበረ አይጠረጠርም።

በመርከብ ሊሳፈሩ ወደ እስክንድርያ፥ ከመውርዳቸው በፊት ከካይሮ ከተማ የሚውሉበት የሁለት ቀን ጊዜ ነበራቸው። ብርሃኑም ጊዜ ያገኘ እንደሆነ በምድረ ግብፅ ሊያያቸው ሲመኝ የነበረው ታሪካዊ ትእይንቶች ሁሉ ዝርዝር ገና አዲስ አበባ ሳለ አዘጋጅቶ ኑሮ ወዲያውኑ እነሱን ለማየት ከተማውና ገጠሩን ሲዞሩ ዋሉ። በዝና በጣም የታወቁትን ድንቅ የሆኑትን ፒራሚዶችን፥ ስፊንክስ የተባለውን በሰው ምስል የተቀረጸውን ጋራ፥ ከሦስት ሺህ ዓመት ይበልጥ ሳይፈርስ የተቀመጠውን የሰዎች አስከሬን (ሙሚ) እና ልዩ ልዩ ታሪካዊ ነገር ባለ አደራ የሆኑትን ቤተ መዘክሮች እና የግብፅ እስትንፋስ የሆነውን እዚህ ስሙን ለውጦ «ኒል» የሚባለውን የአባይን ወንዝ እየዞሩ ሲያዩ መሸ። እነዚህን የጥንት ትንግርታዊ ሥራዎች ለማየት ከሁሉም የዓለም ክፍሎች ወደ ምድረ ግብፅ የሚመጣው በብዙ ሽሕ የሚቆጠረው ሕዝብ ለአገሩ ተወላጆች የሚያስገኘውን ጥቅም በተመለከቱ፥ ጊዜ ፤ በአገራቸው ያሉትን የአክሱምን ሐውትና የሮሐ (ላሊበላ) ቤተ ክርስቲያን የመሳሰሉት ታሪካዊ እጅ ሥራዎች የቀረው ዓለም በሰፊው እንዲያውቃቸውና ጐብኚዎች መጥተው እንዲያዩአቸው ቢደረግ ለሕቡና ለመንግሥቱ የሚያስገኘውን መንፈሳዊና ንዋያዊ ብልጽግና እያሰቡ፥ እነዚህ የአገራቸው ትልልቆች ሥፍራዎች የዓለም ጎብኚዎች መነኻርያ ሁነው የሚያዩበትን ጊዜ ይናፍቁ ጀመረ።

* * *

ከካይሮ ከተማ ባብቡር ተሳፍረው በኒል (አባይ) ዳርቻ በመስኖ ውሀ የተዘራውን እርሻ ማዶ እየተመከቱ ሲጓዙ አርፍደው፥ የግብፅ ዋና ወደብ ከተማ ወደ ሆነው ወደ እስክንድርያ ማታ ደረሰኡ። ይህ ከተማም ቢሆን ብዙ ታሪክ ያየ ነው። የቆረቆረውና ስሙን የሰጠው የፅርዕ ንጉሥ ትልቁ እስክንድር ሲሆን፥ ሮማውያን፥ ቱርኮችና ሌሎችም መንግሥታት በእተራ ቅኝ አገር አድርገውት ነበረ። እነ ብርሃኑም የይለፍ ወረቀቶቻቸውን ጉዳይ ካጠናቀቁ በኋላ ታሪካዊ ሥፍራዎችን ሲጐበኙ አምሽተው በማግሥቱ ማለዳ በመርከባቸው ተሳፈሩ። መርከብ ሲያዩና ሲቀመጡ የመጀመሪያ ቀና ነበረ። ይህን ከብረት የተሠራ ተንሳፋፊ ከተማ ሲመለከቱ ጊዜ ፤ ብዙ ብልሃት ያዘለውን ይህን የሰው እጅ ሥራ በጣም አደነቁ ። የመርከብዋን ልዩ ልዩ ደርብ እየዞሩ ሲጐበኙ በገጠማቸው አስደናቂ ትርእይት መካከል የመርከብዋ ሞተር ትልቅነት፥ በየቀኑ የሚመጣው ዜና ዕለት የሚዘጋጅበት ማተሚያ ቤት፥ በሺ የሚቆጠረውን ተሳፋሪና የመርከብዋን ጭፍራበቀን በቀን የሚመግበው እንከን የሌለበት ወጥቤት፥ ሆስፒታሉ፥ ቤተ ክርስቲያን እና

ኦኬስትራው ጐልተው ይታዩ ነበረ። አንስተኛው ነገርማ ተቆጥሮም አይዝለቅም። ነገር ግን የባሕር ባቡር ሥራ ምንም መስተንክር ቢሆን እንኳ ሁለት ፤ ጀንበር ገና ሳትጠልቅ ተሰልቺ መሆን ቅር ይላል።

መንገደኞቹ መድረሻቸው ወደብ እስኪደርሱ ድረስ ጊዜአቸውን ወዲህና ወዲያ ከመንጐራደድ እና በቡና ቤቱ ከመዝናናትና መጻሕፍትና ጋዜጣ ከመመልከት፥ ወይም በሸራ ወንበር ላይ ተዘርሮ አድማሱንና ሰማዩን ከመመልከት፥ አንዳንዴም ለለውጥ ብለው ፀሐይ ከመሞቅና እርስ በእርስ ከመነጋገር በቀር ሌላ ሥራ አልነበራቸውም። ይህ የሰለቸው ደግሞ በመርከብዋ ኋላ ሁኖ ባሕሩን እየሰነጠቀች አለስልሳ ስትገሰግስ ውቅያኖሱን በመመልከትና ከፍላ ያለፈችው ውሀ የቀኙና የግራው እየተንደረደረ ወደ ሥፍራው ሲመለስ መካከል ተገናኝቶ ሲጋጭ የሚያሰማውን እምቦጭና የሚታየውን ኮረብታ የሚያህል ድንገተኛ የውሀ ክምር ፤ እዚያም ዓረፋው ሻሽ መስሎ ባሕሩን ልብስ ሲያደርገው ትርእይቱን በማድነቅ ጊዜውን ያሳልፉ ነበረ። በመርከብ ላይ መወዳጀት ደግሞ የአስተዋዋቂ ስነ ሥርዓትና ሌላ ድካም አያሻውም። መኰሪያ ወደ ካናዳ ከሚመለስ ካንድ ወጣት ጋራ ፤ ወዲያው ተዋውቆ ዘወትር አብረው ሲታዩ፥ ብርሃኑ ደግሞ ዶክተር ክረሽና ከሚባል አንድ ሕንዳዊ ሊቅ ጋር ተዋውቀና ቀኖቹን ሲነጋገሩ ያሳለፉአቸው ነበረ። ዶክተር፥ ክሪስና በአንድ ትልቅ የአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ ለማስተማር የተመረጠ በቦምበይ ዩኒቨርሲቲ የማኅበራዊ ኑሮ ጥበባት ፕሮፌሰር ነበረ። ብርሃኑም የዚህ ጥበብ ደቀ መዝሙር ስለ ነበረ ከዚህ አጋጣሚ ደስ ብሎት የልቡ እስኪደርስለት ድረስ ከመጠይቅ አልቦዘነም። ዶክተር ክሪሽናም ሆነ ብሎ የሚጠይቀውና እርሱም በበኩሉ ሲጠይቀ በቂ ፣መልስ የሚሰጠው አስተዋይ ተማሪ ስላገኘ ደስታው ከብርሃኑው ጋር ይወዳደራል እንጂ አያንስም ነበረ። መርከብዋ ወደ ወደብ ለመድረስ ቀን ሌሊት ሳት ስትገሰግስ ዶክተር ክርሽና እና ብርሃኑ ይጨዋወቱት የነበረውን ከብርሃኑ ዕለታዊ ደብተር እንዳለ ቀድተን ከዚህ ቀጥለን እናቀርበዋለን፦

«ሰኔ ፲፫ ቀን፦ ዛሬ ዶክተር ክሪሽና ከሚባለው ሰው ጋር ተዋወቅሁ። ዕድሜው ወደ ፶፫ ዓመት የሚጠጋ የማኅበራዊ ኑሮ ጥበብ ተመራማሪ የሕንድ ተወላጅ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ከዚህ ቀደም የተከታተሉ መሆኑን አስረዳኝ። ለማነጋግረው ለማንቸውም ጉዳይ አብስሎ ሊመልስልኝ የሚቻልና የሚፈቅድ በመሆኑ በጣም ደስ ብሎኛል። ብዙዎች ጥያቄዎች ኃይለኞች ናቸው። ቋንቋችን እንግሊዝኛ ነው። ከንግግራችን ፍሬ ፍሬው ይኸው፦

ብርሃኑ። ዛሬ ባሕሩ ጸጥ ብሎአልና እዚህ ዓርፈን መቀመጥ የምንችል ይመስለኛል። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የአገርዎ አድናቂ ነኝ። አሁን ስለ አገርዎ አንዳንድ ጥያቄ ብጠይቅዎ ይጠሉብኝ ይሆን?

ዶክተር ክሪሽና። ደስ እያለኝ እነግርዎታለሁ እንጂ ለምን ቅር ይለኛል?

ብርሃኑ። እንግዲያስ ስለ አገርዎ ሁኔታ ዋና ዋናውን ጉዳይ ያጫውቱኝ እባክዎን።

<u>ዶክተር ክሪሽና፡፡</u> ጉዳዩ ባሕር ነውና በተለየ ለማወቅ የሚፈልጉትን ነገር ቢገልጹልኝ ለመመለስ በጣም ይረዳኛል፡፡ በተቀረ አንድ ዓመት ሙሉ ብተርክልዎ እንኳ አጋመስሁት ለማየት ያዳግተኛል፡፡

<u>ብርሃኑ፡፡</u> እንግዲያው ይሁን፡፡ አገርዎ (ሕንድ) ለእድገትዋ ስለምታደርገው ጥረት ይንገሩኝ፡፡

ዶክተር ክሪሽና፡፡ ሕንድ ነፃነትዋን ያገኘችው ከጥቂት ዓመታት በፊት ስለሆነ ቁጠባዋንና የሕዝብዋን ማኅበራዊ ኑሮ በማሻሻል ላይ ነች፡፡ ደግሞ በሚሊዮን የሚቈጠሩትን ንባብና ጽሕፈት የማያውቁትን ልጆችዋን በማስተማር፥ የሰው ልጅ ላይ ሊደርስ የሚችለው የከፋ ሁሉ ምንጭ የሆነውን ድንቁርናን ለማሸነፍ በብርቱ ትታገላለች፡፡ በውጭ ፖለቲካዋም ቢሆን ስለ ሰው ፤ ልጅ ሙብት እና ሰለ ዓለም ሰላም ቀን እስከ ሌሊት ትደክማለች፡፡

<u>ብርሃኑ፡፡</u> ቁጠባዋን ለማዳበር የምታደርገው ጥረት ምን መልክ አለው? ብዙ ሚሊዮን መሀይምኖቹን ለማስተማርሳ ምን ተገለጸላችሁ?

<u>ዶክተር ክሪሽና፡፡</u> አገሬ ቁጠባዋን መመሥረት የጀመረችው ትልቁ መሪአችን ማህተማ ጋንዲ (ነፍሱን ይማርና) «የአገር ልጅን ሥራ እናክብር ከውጭ አገር የሚመጣውን ዕቃ ሁሉ እናስወግድ» ብሎ ገና የትልቋ ብሪታንያ የቅኝ አገር ሳለን፡፡ አንሥቶ በፈለመ ጊዜ ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ፥ በተለይ ከባዕድ ቀንበር ወጥተን ነፃነታችንን ካገኘን ወዲህ፥ ለሕዝቡ ኑሮ የሚያስፈልገው ዕቃ፥ ልብስ፥ መሣሪያ መጽሐፍና ማናቸውም ሌላ ነገር ሁሉ በአገር ውስጥ በአገር ልጅ በመሠራቱ ፤ አገራችንን አደህይቶ የባዕድ ሲሳይ የነበረው ጥቅም እዚህ እንዲቀር ፤ ይህ በመደረጉም ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብዋ ሥራ አግኝቶ ራሱን እንዲችል ለማድረግ ትደክማለች፡፡ ውጥንዋም በአያሌ በኩል ተሳክቶላታል፡፡

<u>ብርሃኑ፡፡</u> የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻልሳ ምን ልዩ ጥረት ትፈጽማለች?

<u>ዶክተር ክሪሽና፡፡</u> ዋናው ድካምዋ ፤ ሁሉ ንባብና ጽሕፈት አውቆ ከጨለማ ድንቁርና እንዲወጣ ለማድረግ ነው፡፡ ይህን አቅድ በሥራ ለማዋልም እያንዳንዱ ንባብ የሚያውቀው ሰው አንድ ፊደል የማያቀውን ሌላ ሰው አ-ቡ-ጊ-ዳ እንዲያስቆጥር በማለት ተነስታበታለች፡፡ ማናቸውንም ዘመናዊ ከፍተኛ ጥበብ ለማስማር ሙሉ ትጥቅ ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ከፍታ ወጣቶችዋን ታሠለጥናለ፡፡ በሌላ፥ ወገን ደግሞ ትልልቆች ወንዞችዋን እየገደበች ኢንዱስትሪዋን ለማፋፋት የሚያስፈልገውን የኤሌክትሪክ ኃይል በማስገኘትና ዱሮ ባዶ የነበረው ሰፊ መሬት ከግድቡ ውሀ በመስኖ እየለማ ለልጆችዋ ምግብ እንዲገኝ በማድረግ ትደክማለች፡፡ ይህ ጥረትዋ አፍራሽ አግኝቶት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርም ማኅበራዊ ግብረ ገብነት እንዲጠነክር ፤ ግልሙትናና ስካርን የመሰለው ነቀርሳን ሁልጊዜ በመከላከል ሕዝብ ከመጠን አልፎ መሬት እንዳይጠብበው ቤተ ሰባችን በመመጠን ፤ በጤና አጠባበቅና በሌላ አቅጣጫ የሚያስፈልፈውን እርዳታ በማድረግ ትታገላለች፡፡»

ይህን ጊዜ የምሳ ደወል ተደወለና ምንም ቢጥመን እንኳ ንግግራችንን አቋርጠን ወደ ግብሩ ምንም ቢጥመን ከምሳ በኋላ እንድንቀጥል ወደ ግብሩ አዳራሽ ወረድን።

«ሰኔ ፲፰ ቀን ዛሬ ባሕሩ ታውኮአል ትልልቆች ዓሣዎች ከመርከቡ ዙሪያ ብቅ ጥልቅ እያሉ ሲሾኑን ዋሉ። እንዳንዶችን ዓሣዎች ምናልባት ዘሆን እንጂ ሌላ የምድር ፤ አውሬ የሚተካከላቸው አይመስለኝም። ወደ ቀኝ ሲመለከቱ ወሀ፥ ወደ ግራ ሲመለከቱ ውሀ፥ ፊት ሲመለከቱ ውሀ፥ ወደ ኋላ ሲመለከቱ ውሀ፥ ውሀ፥ ውሀ፥ ከላይ በኩል ሰማዩ እንዳጎበር ሁኖ በረጂም ዘንግ የማደረስ ይመስላል። አድማሱም ደረስብህ ሲሉት እየሸሸ ይሄዳል። ታድያ እዚህ ሁሉ ቁጡ ውሀ መካከል መርከብዋ ደሴት ትመስል እለስጋት ትገሰግሳለች። ይህን ማለቂያ የሌለውን ውሀ ሳስተውል የኖህ መርከብና የጥፋት ውሀ ታወሰኝ። ክሪስቶፎር ኮሎምቦ ይህን ዓይቶት የማያውቀውንና ዜናውን ያልሰማውን ውቅያኖስ እንደ ዛሬዎቹ መርከቦች ምቾትና መሣሪያ በሌላቸው የእንጨት መርከቦች አድርጎ ፤ በሞተር ፈንታ ሸራውን ገትሮ ሲገሥግሥ ምንኛ ልበ ቆራጥ እንደ ነበረ ለመገመት ቻልኩ።

ወደ ማታ ጊዜ ከዶክተር ክሪሽና ጋር ተገናኝተን ጭውውታችንን ቀጠልን። ዛሬ ተጠያቂነቱ ወደ እኔ ዞረ። ንግግራችን እንዲ ነበረ።

<u>ዶክተር ክሪሽና።</u> ያገርዎ ሕዝብ ብዛት ስንት ነው?

<u>ብርሃኑ</u>። ወደ ኻያ ሚሊዮን ይጠጋል።

<u>ዶክተር ክሪሽና።</u> ስለ ሃይማኖት ጉዳይ የሕዝቡ አስተያየት እንዴት ነው?

<u>ብርሃኑ።</u> «ሃይማኖት የግል አገር የጋራ» የሚለው ባህል ባገሬ በጣም የገነነ ነው። ክርስቲያኑም፥ እስላሙም ፤ አረመኔውም ጐን ለጐን በሰላም ይኖራል። ከጥቂት መቶ ዓመታት በፊት ግን አንድ ኃይለኛ አገሩን በሙሉ ለመያዝ ተነሥቶ በእግረ መንገዱም ሕዝቡን ወደ ራሱ እምነት ለመመለስ የወረራ ሐሳቡን በሃይማኖት ላይ አስመርኩዞ ኻያ ዓመት ሙሉ አገሩን አሸበረና ብዙ ሕዝብ አጠፋ። ከርሱ ቀደም ብሎም ሃይማኖትዋ ከሕዝቡ ልዩ የሆነ ንግሥት ተነሥታ እንደዚሁ በሕዝቡ ላይ ብዙ ጉዳት አደረገች። በተቀረ ሕዝቡ ላባቶቹ ባህል ታማኝ ሰላማዊ ሕዝብ ነው።

<u>ብርሃኑ።</u> ዶክተር ክሪሽና ፤ በጥያቄዎ መካከል እባክዎን አንድ ነገር ልጠይቅዎ። ሰውን ከሰው ጋር የሚያጣላው መሠረታዊው ለበብ ምንድር ነው?

<u>ዶክተር ክሪሽና።</u> መልሱ ያን ያህል ያሚያስቸግር አይምሰልዎ አቶ ብርሃኑ የሰው ልጅ ዓለም ሲፈጠር ዘር ሲቈጠር ጀምሮ የተደነገገለትን የፍጥረትን ሕግ ጥሶ እንደ ልቤ እንደ ፈቃዴ ልኑር ሲል ፤ የያዘው መንገድ ከሕግ የወጣ ስለሆነ አስተሳሰቡ ይዛባል። ለርሱ ብቻ እንዲደላው ሲል መንፈግ ግድ ይሆንበታል። ራሱን በጣም መውደዱም ሌሎችን መጥላት ያስከትልና የሚጠላቸውን ሰዎች ይፈራቸዋል። የሌሎች አለኝታ ከእርሱው ጋር እንዲስተካከል ስለ ማይፈልግም ቅናትን የመሰለ ነቀርሳ ያድርበታል። ይህ ሁኔታ ከእየአንዳንዱ ሰው ጀምሮ ከቤተ ሰብ፥ ጎሣ፥ ከአውራጃ፥ ከአገር አልፎ፥ ዓለምን ሁሉ የሚጠቀልል ጉዳይ ይሆናል።

<u>ብርሃኑ።</u> ታድያ ምን ተሻለ? መጥፎ መንፈስ እንደምን አድርጎ ለመለወጥ ይቻል ይሆን?

<u>ዶክተር ክሪሽና።</u> ዞሮ ዞሮ ኰብልሎት ወደ ነበረው ወደ ፍጥረው ሕግ መመለስ ነዋ። ይህ ሕግም የተተባተበ ፤ አስቸጋሪ ሕግ እንዳይሆን በጣም ጉልህ ነው። «ሌሎች ሊያደርጉልህ የምትፈልገውን አንተም ለሌሎች አድርግ።» በሚለው አጭር ንግግር ውስጥ ተጠቃሎአል። የጦርነቶች ምክንያት ምንድር ነው? ዓለም አሁን ካለችበት ዘብጥ ውስጥ የገባችው እንዴት ሁኖ ነው የሰው ልጅ ወንድሙን ለማጥፋት እንደሚተጋውና ይህን እከይ ሐሳቡን ለመፈጸም በሚልያርድ የሚቈጠር ገንዘቡን ወጭ አድርጎ በአእላፋት የሚቆጠረው ሕዝቡን አስከትቶ አለምሕረት ለጦርነት ለሞት አሳልፎ የሚሰጠውን ያህል ለመርዳቱ ጊዜ ቢበረታ ኑሮ የዚች ዓለም መልክ ተለውጦ የምድር ገነት ትሆን ነበረ። ግን እንጃ ፤ ታሪክ ሊመዘገብ ከተጀመረ አንሥቶ የተጻፈውን አንመለከት እና በእድሜአችን ውስጥ የደረሰውንም ስናይ፥ ካሣለፍነው መከራ አንዲት ልቡና ስንኳ የሸመትን አንመልስም። አይ ፤ በጊዜ ልብ መግዛት ይሻላልና፥ በተቀር ጠፍተን እንዳንቀር ያስጋናል። መድኃኒቱ ዞሮ ዞሮ ያው ነው። የፍጥረትን ሕግ ወደ ማክበር መመለስ ነው።»

## ምዕራፍ አሥር።

# በአዲሱ ዓለም

ሆቴል ማጀስቲክ በከተማ ውስጥ በአማካይ ሥፍራ የሚገኝ ያማረ የእንዶች ማረፊያ ነው። እነ ብርሃኑም ፤ መርከባቸው፥ ወደብ የምትደርስባትን ቀን ካወቁ በኋላ በቴሌግራም ስፍራ አስይዘው ኑሮ፥ ከመርከብ እንደወረዱ በታክሲ ሆነው በቀጥታ ወደዚህ ሆቴል ሔዱ። አዚያ እንደ ደረሱ የመጀመሪያው አድናቆታቸው በሕንፃው ማማርና በክፍሎቹ ጽዳት ነበረ። ወደ ጽሕፈት ቤቱ ገብተው ከተመዘገቡ በኋላ በወርቀ ዘቦ ያንቆጠቆጠውን ሰማያዊ ልብስ የለበሰው የእንግዳ ተቀባይ ወደ ክፍላቸው መራቸውና ሻንጣዎቻቸውን አስከተለላቸው።

በዚህ በአዲሱ አገር የመጀመሪያውን ሌሊት በሆቴሉ እንደ አደሩም፥ ትምህርት ቤታቸው ወደ ሚገኝበት ከተማ ጉዞ ከመቀጠላቸው አስቀድሞ የነበራቸውን የቦዘን ሁለት ቀን ይህን ስመ ጥሩ ፊት ከተማ እየዞሩ ለመጐብኘት እንዲያውሉት ቁርጥ ሐሣብ አደረጉ። ከተማው እንኳን ሁለንተናው በሁለት ቀን ታይቶ የሚዘለቅ አልነበረም ፤ ሆኖም ሊጐበኙአቸው የሚፈልጉአቸውን ዋና ዋና ትዕይንቶች ከከተማው መሪ መጽሐፍ ውስጥ መረጡና ሐሳባቸውን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በማለዳ ተነሡ። ቀጥሎ የሚገኘው የጕብኙነታቸው ዜና ከብዙው በጥቂቱ ከረጅሙ ባጭሩ ከብርሃኑ የዕለት መዝገብ ተገልብጦ ቀርቦአል።

<u>ጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም</u> ዛሬ ጥዋት የ-ን ከተማ ልንጐበኝ በጥዋት ከሆቴላችን ተነሣንና በታክሲና በአውቶብስ ፤ ሆነን አስቀድመን በዕርዝማኔው ወደ ታወቀው ሕንፃ

ሄድን ፤ (እዚህ አገር ታክሲው በሔደው ኪሎ ሜትር መጠን ሂሳቡን የሚያመለክት ቆጣሪ ስላለው ተሣፋሪው ይህንኑ አይቶ ይከፍላል እንጂ ከሹፌሩ ጋራ ውጣ ውረድ የለበትም።) ይህ ፎቅ በሊፍት (ፎቅ መውጫ) የማይወጣ ቢሆን ኑሮ ጫፉ ድረስ ደረጃውን ለመውጣት የአንድ ቀን መንገድ በሆነ። በክረምት ወራት ዳመና ጫፉን ይሸፍነዋል አሉን። ከዚህ ፎቅ ጫፍ ሁኖ በተራራ ላይ ሁኖ እንደሚታየው ሁሉ ከተማውና ገጠሩ ወለል ብሎ ይታያል። ቁልቁል ሲመለከቱ ፤ በመንገዶቹ የሚተላለፈው የተሽከርካሪና የእግረኛ ብዛትና ትንሽነት ውር ውር የሚል ገብረ ጉንዳንን ይመስላል።

ጉብኝታችንን በመቀጠል ወደ ሌላ ስፍራ ስንሄድ፥ ይህን ከተማ ገምሶ የሚያልፈውን አንድ ትልቅ ወንዝ በፊት በድልድይ ተሻገርን። ይህ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በጣም ሰፊ ነው። የኤሌክትሪክ ፋኖሶቹ የሚሰጡት ብርሃንም ከፀሐይ ብርሃን አያንስም። ይህን መንገድ ለመሥራት የተደዱበትን ምክንያት ብንጠይቅ ጊዜ፥ ድልድዩ ለተላላፊ ባለመብቃቱ መሆኑን ገለጹልን። የዚህ ድልድይ ሥራ የሰው ልጅ ለሥራ ሲታጠቅ ምን ያህል ትልቅ ነገር ለማበጀት እንደሚችል ይገልጻል።

ምሳችንን በከተማው መካከል በሚገኝ አንድ የመብል ቤት ከተመገብን በኋላ (ዋጋው ተወደደ እንጂ ምግቡስ ጣፋጭ ነበረ) ዝና ገነኑን ቤተ መጻሕፍት ለማየት በባቡር ሄድን። የዚህ ከተማ ባቡር የሚጓዘው በአገራችን እንደለምድነው በመሬት ላይ መሆን ቀርቶ በመሬት ውስጥ ለውስጥ አንድ አይጥ መንገድ ተቆፍሮ ነው። ይህ የተደረገውም፥ የየብስ ጥርጊያ ለባለ መንኰራኲር ተሽከርካሪ፥ እንኳ ስለ ጠበበ የሚወጣውን ሕዝብ በማፋጠን እንዲረዳም ደረጃው ራሱ ተንቀሳቃሽ ነው። ዓይን ስንት ነገር ያያል! ሁሉም ለአስደናቂነቱ መጠን የለውም። ባቡሩ በሰዓት ከአንድ መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ይፈጥናል።

የከተማው ቤተ መጻሕፍት አሥራ ሁለት ሚልዮን መጻሕፍት የያዘ መሆኑን እንግዳ ተቀባይነቱ ገለጸችልንና ከኛ ብጤ ሌሎች ጐብኚዎች ጋራ ልዩ ልዩውን ክፍል እያዞረች አሳየችን። አንባቢዎችን የሚያገለግሉና መጻፍቱን የሚያደራጁ ሠራተኞች ብዛት ከአራት መቶ የሚበልጥ መሆኑንም አስረዳችን። በቀን በቀን አምስት ሺህ አንባቢ የቤተ መጻሕቱን መድረክ ይሻገራል።

ቤቶቹ ሁሉም ረጃጅም ፎቆች በመሆናቸው ፤ ጣራ የሚባል ነገር ተፈልጎ ለዓይን ዓይታይም። በባቡር መንገድ ሲራመዱ በኮረብታዎች መካከል ሸለቆ ለሸለቆ መጓዝን ይመስላል። ቀና ብለው ሲመለከቱ፥ ፎቅ ላይ ፎቅ የተደረቡ ቤቶችና ሰማዩ ብቻ ይታያል።

በቀረው በዚህ ከተማ ካየነው ብዙው እንግዳ ነገር አንዱ አዋቂውም ልጁም አለ ይሉኝታ መንገድ ለመንገድ እየገመጠ መሄዱን ነው። የፀሐይ ምች ወይም የሰው ዓይን አለመፍራታቸው! የተሽከርካሪው ብዛት መቸም መዓት ነው። እግረኛ መንገድ ሲያቋርጥ ቀኝ ግራውን አጥርቶ ካልሆነ፥ ኬት መጣሽ ሳትባል አንዲት መኪና ቀንድባው ያርፈዋል!

ደግሞ ወንዱም ሴቱም ጥልቅ ይሁን ሻንጣ ራሱ ተሸክሞ መሄዱን ተመልክተን ገረመን።»

*  *  *

የእነ ብርሃኑ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው ገባ ብሎ ካሉት አውራጃዎ መካከል ባንዱ ነበረ። ዩኒቨርሲቲው ራሱ አንድ መጠነኛ ከተማ ያክላል። - ሃያ ሺሕ ተማሪዎች ይገኙበታል። ከብዛቱ የተነሣም ተማሪ ለተማሪ አይተዋወቅም። ልጆቻችን ወደ ቤታችን እንደደረሱ የገጠማቸውን ሁኔታ ወትሮ ጥንቁቅ ብርሃኑ በዕለታዊ መዝገቡ ጽፎት ኑሮ ከዚያው እንደገና እንቀዳለን።

«ጥቅምት ፳፪ ቀን ፲፱፻- ዓ.ም በእግዚአብሔር ቸርነት ዛሬ በሰላምና በጤና ወደ ትምህርት ቤታችን ደረስን። ወደ ትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሄድን ጊዜም በደስታ ተቀበሉንና ክፍላችንን የሚያሳምን ሰው ሰጡን። በአሣር በመከራ ወደ መኝታ ክፍላችን አወጣን ፤ እርሱም ለክፋት ብሎት በአምስተኛው ድርብ ነው። አሁን ሰዓቱ ምሽት ቢሆን፥ እንኳ የትምህርት ቤቱ ግቢ የተዋበ መሆኑን ከአትክልቱ፥ ከመንገዶቹና ከመስኮቹ፥ ከቤቶቹም ሊገመት ይቻላል።

ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም ሰሞኑን የትምህርትና የጤና ምርመራ ውርጅብኝ ሰንብቶብን በደኅና አለፍነው እና ትምህርታችንን ዛሬ ጥዋት ጀመርን። ከክፍል ወደ ክፍል ሲርዋርዋጡ ቀኑ ይመሻል። የተዋወቅናቸው አስተማሪዎቻችንና ጓደኞቻችን ተማሪዎች ለሚያቀርቡልን ጥያቄ ማለቂያ የለውም። ስለ አገራችን ስፋት፥ ስለ ሕዝብ ብዛት፥ ስለ ሰብሉ፥ ስለ ኑሮው፥ ምን መሳይ ልብስ እንደምንለብስ እና ምን እንደምንበላ፥ በምን በምን እንደምንጠጣ፥ ምን ላይ እንደምንተኛ፥…ይጠይቁናል። ጥያቄያቸው አንዳንድ ጊዜ የልጅ ይሆንና በጣም ያስቃል። ሆኖም እኛ በዘልማድ የምናደርገው ብዙ ንገር ለእነርሱ እንግዳ መሆኑ፥ የእነርሱም ብዙው ነገር ለእኛ እንደዚሁ መሆኑ አይገርምም። እኛስ ኑሮአቸው ከኛው ልዩ የሆነ እውጭ አገር ዜጋዎች ጋራ በከተማችን ልምምድ ስለ ነበረን የዚህ፥ አገር ሰው ኑሮ እምብዛም እንግዳ አልሆነብንም። እነዚህ ተማሪዎች ግን ያገራችንን ነገር ስንነግራቸው ተረት እንደሚሰማ ሕፃን ዓይናቸውን ጕልጕለው ያስተውሉናል። ወይም እንደ ጋዜጣ አነጋገር ከማርስ እንደመጡ ሰዎች ያህል ይቈጥሩናል። ከአገራቸው ልማድ በቀር ሌላ የሌለ የሚመስላቸው አንዳንድ ንዝኅላሎችም ሳይገጥሙን አልቀሩም። ታድያ ያንዱ አገር ከሌላው አገር ልማድ ጋራ አይስማም። አንዱ ባንድ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ… የምኝታ ክፍል ጓደኞቻችን ያገራቸውን ሲያስጠኑን እኛ ደግሞ ለውጡን ያገራችንን እንነግራቸዋለን።

ጥቅምት ፴ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም በውድም ሆነ በግድ የትምህርት ቤት ኑሮውን መልመዳቸው ነው። የቀረውስ ቢሻው፥ መብሉ እንደሆነ ግን ዘወትር አልጫ፥ ውሀ ውሀ የሚል ነገር፥ ብናኝ በርበሬ እንኳ የለበት ቢፈጽምልን ትምህርታችንን በአራትና በአምስት ዓመት ውስጥ አከናውነን ወደ ውዲቱ ለምለም አገራችን ለመመለስ ተስፋ አለን።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

# የወዲያ ወሬ

ወደ ውጭ አገር የሄዱት ልጆቻቸው አዲሱ አካባቢአቸውን ሲላመዱና ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ፥ በአገር በቀሩት ዘመዶቻቸው ዘንድ ኑሮ እንደወትሮው ይቀጥላል። አቶ አባይ (የብርሃኑ አባት) ሰርክ ጥዋት በሦስት ሰዓት በሥራቸው ቦታ ተገኝተው፥ በሰዓት ለምሳ ወጥተው፥ በዘጠኝ ሰዓት ተመልሰው ሄደው ማታ በአሥራ ሁለት ሰዓት የቀኑን ተግባር ፈጽመው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ በመሆናቸው ኑሮአቸው ፤ ነጋጠባ ይህ ሲሆን፥ የሚለዋወጥ ነገር ባለመኖሩ የሚሰለች ሳይመስለን አይቀርም። ነገር ግን አቶ አባይ በሚቀመጡበት በአገረ ሰላም ከተማም ብዙ ነገር ተለዋውጦ ነበረና እርሳቸው ይህን አዳዲስ ሁኔታ ሳይታዘቡት አልቀሩም። ለምሳሌ ያህል አቶ አባይ ልጅ በነበሩበት ጊዜ አንድ ከበርቴ ወደ አደባባይ ወደ ገበያ ወይም ማኅበራዊ ኑሮ አስገድዶት ሊደርስ ወደሚገባው ጉዳይ ሲሄድ፥ ሰጋር በቅሎውን ያስጭንና በፍጥነት ከበቅሎው ጋራ የሚወዳደረውን ለጓሚ ያስከትል ነበረ። ዛሬ ግን ይህ የጋማ ከብት የከተማ ቦታውን ለአውቶመቢል ለቆ፥ ራቅ ወዳለው ባላገር ሸሽቶ፥ ሠፈር ጨዋው መኪናቸውን ራሳቸው ሽምጥ ይነዳሉ። ደከም ሲላቸውም ፤ ስሙን ለውጦ ዛሬ ሾፌር ተብሎ በጐናቸው ለተቀመጠው ለዱሮ ለጓሚአቸው መሪውን ይለቃሉ። የራሱን መኪና ለመግዛት የማይችለው ተራው ሰው ቢሆን እንኳ በትንሽ ገንዘብ በአውቶብስ ተሳፍሮ ወዳሰኘው ሊደርስ በመቻሉ ከብዙ ልፋት ድኖአል። ስለዚህ የልጅነታቸው ጊዜንና የዛሬውን ሁኔታ ሲያመዛዝኑት ብዙ ነገር ተለውጦና ተሻሽሎ ይታያል። ሴቶችም ቢሆኑ ዛሬ ወደ ገበያ ሲሔዱ መኪና ተሳፍረው ስለሆነ የሸመቱትን አዝላ ወደቤትዋ የምትቻኰል እምብዛም አትታይም።

አቶ አባይ ከዕለታት አንድ እሑድ ቀን ከዕቁብ ማኅበር ስብሰባ አርፍደው ወደቤታቸው ሲመለሱ ይህን ይህን በአእምሮአቸው ሲያወጡና ሲያወርዱ ሳያስቡት ቤታቸው ደረሱና ከልጃቸው ከብርሃኑ ፖስታ መጥቶላቸው ኑሮ ባለቤታቸው ሰጥተዋቸው ሊያነቡ ከፈቱት በውስጡም ቀጥሎ እንደቀዳነው አነበቡ።

## .... ከተማ

## ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻ - ዓ.ም

የተወደድከ አባቴ

ከማፈቅራት አናቴና ከተወዳጆቹ ወንድሞቼና እህቶቼ ጋራ ሁላችሁም እንደምን ከርማችኋል? እኔ ለጤናዩ በጣም ደኅና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን፥ ከናፍቆታችሁ በቀር የሚጐድለኝ ነገር የለም። ባለፈው መጋቢት የጻፍክልኝ ደብዳቤህ ደርሶኝ ደስ ብሎኛል ነገር ግን ሰሞኑን በፈተና ላይ ሰለሰነበትን መልሱን ቶሎ ሳልጽፍ በመቅረቴ ይቅርታ እንድታደርግልኝ እለምንሃለሁ። ዘመዶቻችን ሁሉ ጤና እንዲሆኑ ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

ባለፈው ጊዜ ደብዳቤዬ እንደገለጽኩልህ ሁሉ ትምህርቴን ወደመፈጸሙ ገደማ ተቃርቤአለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ አንድ ዓመት ያህል ቢያስጨምረኝ ነው እንጂ ወደ ውዲቱ አገሬ የምመለስበት ጊዜ በመቃረቡ ለደስታዬ መጠን የለውም። የራስ አገር ጣዕም ካልተለዩት አይታወቅም። አሁን ሩቅ ሁኜ ሳስታውሰው የአገሬ ወንዙ ሸንተረሩ ፤ ሜዳው ተራራው ፤ ጨፌውና ጫካው ፤ ገበሬው ሲያርስ፣ ከብቱ ሲሰማራ ዓይኔ ላይ መጥቶ ድቅን እያለብኝ እዚህ አገር በመጣሁ ጊዜ በአድናቆት እመለከተው የነበረውን ሁሉ ከምናምን አድርጐታል። ዛሬ የዘወትር ሐሳቤም ወደ ውዲቱ አገሬ መቼ ተመልሼ እዚህ ከአስተማሪዎችና ከመጻሕፍት ያገኘሁትን ጥበብ በተግባር በማዋል ለኔ የተገለጸልኝን ብርሃን ለአገሬ ሰዎች መቸ አካፍየ ፤ በሐሳቤም ሆነ በጉልበቴ እስከ መጨረሻይቱ የላቤ ጠብታ ድረስ ሀገሬን አገልግየ ነው።

እዚህ አገር ስለ ተመለከትኩትና ስለ ሰማሁት በአያሌው እጽፍልህ ነበረ። ነገር ግን አሁን በወረቀት ጨርሼው ባፌ የማወራውን እንዳላጣ ብየ በተመለስኩ፥ ጊዜ በቃሌ እንድ ነግራችሁ አቆይቸውአለሁና ደብዳቤዬ በማጠሩ እንዳታዝኑብኝ ተስፋ አደርግሁ የናፍቆት ሰላምታዬን እልካለሁ።

የሚወድህ ልጅህ ብርሃኑ።»

## ምዕራፍ ፲፪።

# ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም።

ብርሃኑ እና ዓለሙ ቸኰልን ጠይቀው ሲመለሱ በሆስፒታሉ ደጅ አቅራቢያ ቁመው ይጠብቁ ነበረ። ብርሃኑ ከውጭ አገር ከተመለሰ ሦስት ወር ሁኖታል። ጋሪው ሲዘገይባቸው ጊዜም በባቡር መንገድ ዳርቻ ሸቅብ ቁልቁል በመንሸራሸር ማስታገሻ ሲያበጁ ፤ አንድ በባለጸግነቱ የታወቀ ሰው «ሸንጡ ሰላሣ ክንድ በሚያህል» መኪና መጥተው ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ገቡ።

«እኒህ ሰው ታመዋል መሰለኝ ፤ ሐኪም ፍለጋ ነው የመጡት» አለ ብርሃኑ።

«አይ ሞኙ!» ብሎ መለሰ ዓለሙ «ሰው ሁሉ እንዳንተ መናጢ ድኃ ነው የሚመስልህ። ርሳቸው ሐኪም ሲፈልጉ እስካሉበት ድረስ እያለኸለኸ ይመጣላቸዋል እንጂ እዚህ ድረስ ማን ልፉ አላቸው?»

«እረ አዎን ጃል እውነትህን ነው እኮ። እኔ የተናገርኩት ሳወጣና ሳላወርድ አስቀድሞ በሐሳቤ ውስጥ ጥልቅ ያለውን ነው።» ብርሃኑ ይህን ተናግሮ ጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ይቆይና እንዲህ ብሎ ይቀጥላል «ዓለሙ ፤ አሁን አንድ ነገር» ትውስ አለኝ። እኒህ ሰውዬና ብዙዎች የእርሳቸው መሰል ከበርቴዎች ሐኪምና ሌላ ነገር ሲፈልጉ እቤታቸው ድረስ ይጣላቸዋል። የሥራ ሰዓት እንዳይረፍድባቸው አይሰጉም ፤ ከሥራ ሲቀሩም የበላይን ተግሳፅና የደሞዝ

ቁርጥን አይፈሩም። የተመኙትን ነገር ደግሞ ሁሉን ባይሆን እንኳ አብዛኛውን ያገኛሉ። ልክ እንደ «አላዲን ፋኑስ» ጫር ጫር አድርገህ ያሰኘህን ማስመጣት ነው። ታዲያ አጥብቀህ ብታስብበት እኮ እንዲህ ያለው ኑሮ ምኑ ደስ ይል ይመስልሃል? ሰው መቼም የተፈጠረው ሊወርድና ሊወጣ ፤ ሊያገኝና ሊያጣ ፤ ሊበርደው ፤ ሊስቅና ፤ ሊያለቅስ ሊለብስና ሊታረዝ ፤ ተስፋ ሊያደርግና ተስፋ እንዲቆርጥ ፤ እንዲደክምና እንዲያርፍ ነው። በወፉ ፤ በአውሬውና በሌላው ሕያው፥ ፍጡር ላይ ስንመለከተው ፤ ሁሉም ተግቶ ለኑሮው የሚያስፈልገውን ሲሻ እንደሚገሠግሥ ነው። ከዚህ ሁኔታም ፤ ይህ የፍጥረት ሕግ መሆኑን ለመረዳት ሳንችል አንቀርም ይመስለኛል። ታዲያ ከሕግ ውጭ የሆነ ማናቸውም ንገር ከዜማ የወጣ ሰልፍ አበላሺ ነውና ለኔ እንደሚመስለኝ የጌታ ልጅ ሁኖ ተወልዶ በተድላና በቅምጥል ውስጥ ተውጦ ከመቅረት ይልቅ በድህነት ተወልዶ ጥሮ ግሮ በማደግ የሕይወትን ጣዕም በይበልጥ ለመቅመስ ሳይሻል እንደማይቀር ነው። ይህን የሚያደርገው፥ ማለት በጥረቱ የማይኖር ሰው ለተፈጠረበት ዓላማ በውነት ኖረ፥ ለማለት የማይኖር ሰው ለተፈጠረበት ዓላማ በውነት ኖረ ለማለት የማኖር ሰው ለተፈጠረበት ዓላማ በውነት ኖረ ለማለት የማይቻል ይምሰለኛል። በዚህ ዓለም ላይ የሕይወት መልእክቱን ሊፈጽም የተላከው እያንዳንዱ ሰው የመኖርን ተግባር ካልፈጸመ በቀር በቁመናው ሳለ የሞተ እንደሆነ ሊባል ይቻላል። «እገሌ የሞተ ሬሳ ነው «ስንል ገና በቁመናው ሳለ ነው እኮ።»

«እባክህን ተወኝ፥ እኔስ ለኑሮዬ የሚያሻኝን ሳልወጣና ሳልወርድ ካገኘሁት ማን ልፋ አለኝ?» ብሎ ዓለሙ ሲናገር መኩሪያ ወዲያው በመኪናው ሆኖ ባጠገባቸው ሲያልፍ እጁን ለሰላምታ አወዛወዘላቸው።

«እንዴ መኩሪያ አይደለም እንዴ? ከውጭ አገር መቸ ተመለሰ እባክህን?» አለ ዓለሙ።

«አላውቅህም ኑሮአል እንዴ?» አለ ብርሃኑ «ሰንብቶአል እኮ አሁንስ ወደ ስድስቱ ወር ሳይጠጋው አይቀርም። በቅርብ ቀን ውስጥ ወይዘሪት ጥሩ ወርቅን ሊያገባልህ ነው። ጥሩ ወርቅ ታውቃት የለም!»

«ከመጣ ተገናኝታችሁአል ወይ?» አለ አለሙ።

«እንዴታ፥ ካንተ ጋራ አልተገናኛችሁም መሰለኝ» አለ ብርሃኑ።

«ያውልህ እንግዴህ የኛ ነገር» አለ ዓለሙ «ከተለያየን ዘመኑ ልክ የለውም፥ ምነው የእግዜርን ሰላምታ እንኳ ነፈገኝ ፤ ከሩብ ሰዓት በፊት ተገናኝተን የነበረ ይመስል እጁን አወዛውዞ ብቻ ዝም ወየ ጉድ!»

«ቢቸኩል ይሆናል እባክህን፤» አለ ብርሃኑ። «ይልቁን ይህ ጋሪ ደግሞ ሳይሄድብን እንሳፈር።» ይህንን ይባባሉና ሁለቱ ወጣቶች ጋሪያቸው ላይ ጉብ ብለው የከተማውን ነፋስ እየተመገቡ ወደ ዓለሙ ቤት አመሩ።

ከፍ ብሎ ከሁለቱ ሰዎች ንግግር እንደ ተረዳነው መኰሪያ ትምህርቱን በውጭ አገር አከናውኖ ከተመለሰ መንፈቅ ያህል ሆኖታል። የተከታተለው ትምህርትም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረስ የመጣውንና አባቱም ከሕፃንነቱ አንተው በአእምሮው ውስጥ ቀርጸውት የነበረውን የቤተ ሰቡን ማዕርግ ከፍ የሚያደርግ ዓይነት ትምህርት ነበረ። ወደ ትውልድ አገሩ እንደ ተመለሰም ወዲያው ደህና ደሞዝ የሚገኝበት ሥራ አገኘ። ክብር ሀብትና ማዕርግ፥ በጠቅላላው ዓለም ልታቀርበው የምትችል ብዕል ይህን የታደለ ልጅ ይጠብቀው ነበረ። ከሁሉ ይልቅ ደስታ ላይ ደስታ የሆነው ግን የወላጆቹ የኑሮ ጓደኛ የምትሆነውን አስበው ጨርሰውለት ስለ ነበረ ከትምህርት ቤት እንደ ተመለሰ ወዲያው አቶ ጥቂት ቆየት እንዳለ ደግሰው በዳሩት ጊዜ ነው።

የሠርጉን ታሪክ በወሬ እንደሰማነው ለትንግርት ነበረ። ሆኖም የአፍ ታሪክ ከሰው ወደ ሰው ሲቀባበል መራባቱ አይቀርምና ፤ እውነተኛውን ታሪክ ካንድ ጋዜጣ ላይ እንዳለ ቀድተነው ይኸውና፡-

## የከተማ ወሬ።

### ሠርግ

ትላንት እሑድ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻- ዓ.ም የልጅ መኩሪያ በላይና የወይዘሪት ጥሩ ወርቅ ደምሴ የሠርግ በዓል ተከብሮ ፤ ውላእ። እድለኞቹ ሙሽሮች ብዛታቸው ከሁለት መቶ በማያንስ መኪናዎች ታጅበው ከሙሽራይቱ ቤት ወደ ወንዱ ቤት በመጡ ጊዜ እልልታውና ሆታው ጆሮ የሚያደነቁር ነበረ። የሰነበቱበት በመሆናቸው ተዳክመው የነበሩት ልጅ አገረዶችም የሙሽሮቹን መምጣት ድምጽ እንዳገኙ ዘፈኑን እያቀለጡ ከበሮውን እስኪተረተር ይመቱና ግጥሙን ያጐርፉ ጀመሩ። በደጃዝማች በላይ ግቢ ሙሽሮቹን ይጠብቃቸው የነበረውን ዳስም በትልቅነትና በማማር የሚያስተካከለውን ዳስ ከዚህ ቀደም ያየ ሽማግሌ ባገር ሊገኝ አልተቻለም። በአነስተኛ ግምት ባንድ ጊዜ ሁለት ሺ ሰው ሊያበላ የሚችል ሆኖ ፤ የስፋቱ መጠን በአንዱ ጫፍ ሆኖ የሚጣራውን በወዲያኛው ጫፍ ያለ ሰው ሊሰማው እንደማይችል ታውቆአል። ይህ አስደናቂ የሆነ አዳራሽ የድንኳንና የዳስ ቅልቅል ሁኖ ግንቦቹና ምሰሶዎቹ ውበታቸው ባማረ መአዛቸው በጣፈጠ አበባዎችና በሰንደቅ ዓላማዎች ተሸልመው የሰማይን ከዋክብት የመሰሉ የኤሌክትሪክ ፋናዎች ብርሃናቸውን እንደ ፀሐይ ያጐርፉበት ነበረ። በወለሉም መለስለሱ ወፍራም ስጋጃን የሚወዳደር ለምለም ቀጤማ ተነስንሶበታል።

ሙሽራይቱ ተኩላ ተሸልማ፥ በረዶ የመሰለ ነጭ ሀር ለብሳ፥ መልአክ የመሳሰሉት ደንገጥሮችዋ በእጃቸው እረጃጅም ሻማ ይዘው እያጅቡአት፥ ሙሽራውም ከሚዜዎቹ ጋር እንደ ንጋት ኮከብ ደምቆ አምሮበት የዳሱት መድረክ በግርማ እንደ ተሻገሩ እድመኞቹ ብድግ ብድግ አሉና በጭብጨባው ዳር እስከ ዳር አስተጋባ። ይህ

ትንግርታዊ ትርእይት ለዘላለም ተመዝግቦ እንዲቆይ በማለትም ፎቶ ግራፍ አንሽዎች ተግተው ተግባራቸውን ይፈጽሙ ነበረ።

ለገበታዎቹ እስኪከብድ ድረስ የተትረፈረፈው ሲሳይና ይጐርፍ የነበረው ልዩ ልዩ የአገርና የባሕር መጠጥ ዓይነት ሠርገኞቹን አስደስቶ ይመግብ ነበረ። ስፍር ቁጥር የሌለውን ሠርገኛ ሲያገለገሉ የነበሩትን አሳላፊዎችም ቅልትፍናቸው የተመልካችን ሆድና ዓይን ሳያስደስት አልቀረም። ሳሕንና ቢላዋ እየተጋጨ፥ የበላተኛው ድምፅ እንደ ሠራዊት ወይም እንደ ገበያ ሕዝብ ድምፅ ሲተም ይህን ጊዜ አዝማሪዎች ለዛው በጣፈጠ ምትና ባማረ ጉሮሮ ልዩ ልዩ የሆኑ የአገር ዜማዎችን ሲያሰሙ እንግዶቹ በቀረው የምድር ፍሬ እየተመገቡ ለመንፈሳቸው ደግሞ ይህን የተዋበ ዜማ ሲሰሙ፥ የአባቶችን ታሪክ እያስታወሰ ፊቱ በርቶ ዓይኑ እሳት ነበልባል መስሎ ወኔው ያልተቀሰቀሰበት አንድ ስንኳ በመካከላቸው አይገኝም ነበረ። ይልቁንም አዝማሪዎቹ የደጃዝማች በላይን ስም እያነሡ ክብራቸውን ሲያሞግሱ በተሰማ ጊዜ፥ ልቡ በእነዚህ መኳንንት ፍቅር ያልተነካ ሰው ከወዴት ይምጣ!

በውነቱ ይህ ሠርግ አንዳች ጉድለት የማይገኝበት ነበረ። ዳሱ የተሠራበት የልዩ ልዩ ዓይነት ዛፍ ቅጠልና የአበባው፥ የቈጠማውና የሙብሉ የበየዓይነቱ መጠጥና የልዩ ልዩውን ሽቶ መዓዛ አንድ ላይ የሰነፈጠው አፍንጫ፥ ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ገጸ በረከት ያቀረበችለትን ሽቶ ግምት ሳያስገኝ አልቀረም።

የልጅ መኰሪያ በላይ ሠርግ እንዲህ ባለ አስደሳች ስነ ሥርዓት ተፈጸመ።

ከሠርገኞቹ አንዱ።

መኰሪያ የዕድሉ! ሁኖ በቆየው ሀብት ላይ ከፍተኛ ትምህርቱ በሚፈቅድለት መደብ ሥራ ተሰጥቶት በቂ ደሞዝ በማግኘቱ በገንዘብ ማጠር ሳንክ የጐጆ ወጮችን ታንኳ ከሚያውክ ሞገድ ነፃ ሆኖ ትዳሩን በሚያስደስት ሁኔታ ጀመረ። የሳምንት ተግባሩ ጣልቃ ከሚገባው በቀርም፥ በዝምድና በወዳጅ ቤት ግብዣ መሳተፍና ሙሽራውን እየያዘ ንፋስ ለመቀበል በአዲሱ መኪናው ሽርሽር መሄድ አልተለየውም። በተቀረ፥ ሲኒማንና ትያትርን የመሳሰሉት ትዕይንቶች የስፖርትና የመደሰቻ ቦታዎች በደፈናው ታማኝ ደንበኛ በመሆኑ መንፈሱን ከማደስ አልቦዘነም ነበረና የትዳር ሸክም ቀለል ያለ ስለሆነለት በዚሁ ሸክም ክብደት ሲማረሩ የሚሰማቸውን ሰዎች ንግግር ለመቀበል በጣም አዳጋች ይሆንበት ነበረ። ደግሞ እነርሱ እንደሚሉት አስቸጋሪ ቢሆንባቸው እንኳ፥ «ሰው የተጻለትን የአርባ ቀን ዕድሉን ተመስገን ብሎ መቀበል አለበት» እያለ እርሱ እንደሆነ የዕድሉን እያመሠገነ ይኖር ነበረ።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት።

# በፍቅር መነደፍ

ዓለሙ ሰብስቤ በሆቴል ኑሮው ተደስቶ ረጅም ጊዜ ሊኖር አልቻለም። ላዲሱ መኖሪያው የነበረው የወረት ወላፈን እንደቀዘቀዘና አዲሱ ሕይወቱ የማያዘልቀው፥ በተለይም በውጭው በኩል የሚከብደው መሆኑን እንደ ሞከረ ፤ ወደ ወላጆቹ ቤት መመለስ ከሁሉ የተሻለ መሆኑን ተረዳ። ይህንኑ ሐሳብ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በመዶለት የሚረዱትም እናቱ ወይዘሮ ይታከቱን የመሰለ መካሪ አገኘና ውሎ አድሮ ትቶት ሄዶ ወደ ነበረ ቤት ተመለሰ። ይህን በማድረጉም ደስታው የብዙዎች ሲሆን ከነዚህ አንዱ ጓደኛው ብርሃኑ ነበረ። በዚህ ሰሞንም ጓደኛነታቸው ከወትሮው ይልቅ ጋል አለና ብርሃኑ ወደ ማታ ጊዜ በዕረፍቱ ሰዓት ከዓለሙ ጋር ለማውጋት ወደ አቶ ሰብስቤ ቤት ይመጣጣ ነበረ።

የአቶ ሰብስቤ ቤት ዙሪያውን ረጅም ግንብ ደብቆት አንዳንዴ የብረቱ በር ሲከፈት ብቻ ጨረፍታውን ካልሆነ በቀር ሕንፃውን በሞላው ለማየት የማይቻል ነበረ። ከውጭ ከሩቅ ሲመለከቱ ፤ ጣራና በግቢው ውስጥ ከሚገኙ አንዳንድ ዛፎች ጫፍ በቀር ሌላ አይታይም በሩን ዘልቀን ስንገባ ግን መሬቱን ባነጠፈው ሣርና በውቦቹ የአበባ መደቦች መካከል ከጡብ የተሠራው አራት ማዕዘን ቤት በግርማ ቁብ ብሎ እናያለን። የቤቱን አሠራር ስንመረምርም የጥንቱንና የአዲሱን ዘመን ቅያስ ያጣመረ በመሆኑ መሐንዲሱ የዱሮ ሰው መሆኑን ያሳስበናል።

ብርሃኑ እንደ ልማዱ አንድ ምሽት ወደ ዓለሙ ዘንድ መጣና ዛሬ በቤት ቆይቶ የተቀበለው ያው ጓደኛው ሳይሆን እኅቱ ተዋበች ነበረች። ወላጆችዋ ዘመድ ሊጠይቁ ወደ ከተማው ገጠር ሂደው ስለነበረ፥ እስኪመለሱ ድረስ የቤቱ አላፊነት የብቻዋ ነበረ። ብርሃኑም በሩን ባንኳኳ ጊዜ የከፈተችለት እርስዋ ነበረችና የደንቡን ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ የወንድምዋን መኖር አለመኖር ሁኔታ አስረድታ፥ በቶሎ የሚመለስ መሆኑን ገልጻ በቤት ገብቶ እንዲጠብቀው አለችው።

«ግባና ጋዜጣ ስትመለከት ቆየው፥ እርሱ እንደሆነ አሁን ይመጣልሀል» አለች ተዋበች ዓይንዋን ሰበር አድርጋ «ጋዜታው ሲሰለችህ ደግሞ ሻይ አመጣልሀለሁ።»

ብርሃኑ ፤ ይህን የመሰለ ጥሪ መልኳና ስምዋ ውብ ከሆነ አስተናጋጅ አግኝቶ ይቅርና በዜሮም ቢሆን ለመጠበቅ ዝግጁ ስለ ነበረ ጥሪውን በደስታ ተቀብሎ ወደ እንግዳ ማረፊያ ክፍል መራችውና ባረግራጊው ወንበር ውስጥ ስጥም አለ። ባጠገቡ ከነበረው ጠረጴዛ አንድ ጋዜጣ ሳብ ያደርግና ማንበብ ይጀመራል። ወትሮ እንኳ ትጉ አንባቢ ነበረ ምነው ዛሬ ሐሳቡ እየኮበለለ አልሰበሰብልህ አለው? ብርሃኑ በንጋት ኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማር በነበረበት ጊዜ ተዋበች አብራው ትማር ስለ ነበረ ፤ ዕውቂያቸው የከረመ ነበረ ፤ በትንሽነትዋ ጊዜም ይህችን ዓቅመ ቢስ ንፋስ ሽው ሲል ገፍትሮ እንዳይጥላት የምታሰጋ ልጅ ማናቸውም ጉዳት እንዳይደርስባት ልዩ ተባቂዋ እርሱ እንደሆነ ይመስለው ነበረ። ዛሬ

ግን ተውበች ቁመትዋ ዘለግ ያለ ሰውነተ ፍርጥም ልጃገረድ ሁናለች። ፈገግ ያለው ጠይም መልክዋ የአደይ አበባን መስሎ በሚያብብበት የወጣትነት ዘመን ውስጥ በመሆኑ የደም ግባትዋ እንደ ምንጭ ውሀ ኩል መስሎ ጠርቶ ይታይ ነበረ። የጥቁር ሀር ነዶ የመሰለው ጠጉርዋ በራስዋ ላይ እንደ አክሊል ተደፍቶ፥ እንደ አልማዝ የጠሩት የሾተል ጉጥ የመሰሉት ዓይኖችዋ የጨረቃን አስኳል ይመስላሉ። ደረትዋ ጉጥ የመሰሉት ዓይኖችዋ የጨረቃን አስኳል ይመስላሉ። ደረትዋ መከዳ የመሰለ ፤ ሽንጥዋ እንደ ተሳበ አረግ ዳሌና አቋቋም። መልካም ልጅ ነበረች። ሰውነትዋን ያጐናጸፈው ራስዋ ፈትላ የሰፋችው ወተት የመሰለው ቀሚስና ውብ ቅርጽዋን ሊሰውር እጅግ አልቻለም። ትሕትናና ዓይነ አፋርነትም ይህን ውበትዋን ደምድሞታል። ታዲያ ይህ ገና ዓይኑን የሚገልጠው ወጣት ይህን የውበት ጸደይ በፊቱ ተዘርግቶ ሲያስተውል አንዳንዴ አእምሮውን ቢነሣው ሊፈርድበት ይገባ ይሆን? ከዚህ ቀደም ግን ተዋበች እንዲህ የተሟላ ቁንጅና የተሰጣት ልጅ መሆንዋን ብርሃኑ አስተውሎ አያውቅም ነበረ። በፊቱ ዘርግቶት በነበረ ጋዜጣ ላይ ሐሳቡን ለመሰብሰብ ሞከረ ፤ ግን ወየው ሁሉም ከንቱ ልፋት ሆኖ ቀረ። ሐሳቡ ዙሮ ዙሮ ወደዚያ ወደ አንድ ነገር ብቻ እያንሸራተተ አስቸገረው። ዓይኑ የታተመውን ጽሑፍ አፍጥጦ ሲከተል ልቡ ግን የሚዋልለው በሌላ ሐሳብ በረሀ ውስጥ ነበረ። ሆኖም ይህ ችግር የግሉ ሁኖ ገመናውን የሚገልጥበት ወዳጅ ጠላት ስላልነበረ ሽብሩ ብዙ አልነበረም።

ብርሃኑ እንዲህ ውስጥ ውስጡን ሲሸበር ተዋበች ወዲያው ሻይ አመጣችና ትይዩው ተቀምጣ ኩባያዎቻቸውን ያጋቡ ጀመረ። እጆችዋ ሥራ እንዳይፈቱ የሥራ አገልግልዋን አቀረበችና እጅ ሥራዋን በፈጣኖቹ ፤ ከአለንጋ በሚያሳስቱ ጣቶችዋ ትጠልፍ ጀመረ። ንግግራቸው በልጅነታቸው ጊዜ በንጋት ኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አብረው ይማሩ ወደ ነበረበት ጊዜ አመራና የሰዓቱን ማለፍ ሳይመለከቱ ረጅም ጊዜ ሲጨዋወቱ ቆዩ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አብረው ጨርሰው እርሱ ወደ ነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲዛወረ እርስዋ ወደ ሴቶች ከፍተኛ ትምህርት ቤት ተዛውራ ነበረና ከዚያ ወዲህ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ማዶ ለማዶ ለዓይን ለመተያየትና የሩቅ ሰላምታ ለመሰጣጠት ያህል እንጂ እንደ ዛሬው ቅርብ ለቅርብ ተገናኝተው ተነጋግረው አያውቁም ነበረ። ዛሬ ብርሃኑ የመጣው ዓለሙን ፈልጎ ሲሆን ይህ ሐሳቡ ስላልተፈጸመለት ተደሰተ እንጂ ቅር አልተሰኘም። ከተዋበች ጋር የትምህርት ቤታቸውን ትዝታ ንግግር እንዳበቁ ወደ አገር ውስጥ ወሬ ገቡና ንግግራቸው ተፋፋመ። ዓለሙ መቸም ጨርሶ ተረሳ።

«በይ እስቲ» አለ ብርሃኑ «አሳተያየትሽ ከጨርቅ ዓይነት ዕውቀት ያልፋል ብየ አላሰብኩም ነበረ። አሁን ግን ስንነጋገረው ከቆየን ሁሉ እንዲህ አስተያየትዋ የሰፋ አስተዋይ ልጅ መሆንሽን ከተረዳሁ ከረር ስላለ ጉዳይ እንነጋገር እባክሽን።»

«ወንዶች መቸም ከራሳቸው ላይ አትወርዱ» አለች ተዋበች። «እኛን ሴቶች ስትንቁና ቆዳችሁን ስታዋድዱ ትኖራላችሁ ግን በከንቱ ትደክማላችሁ። እኛ ሴቶች እንደሆንን እኮ ፤ ከእናንተ አናንስም።» ብላ ትስቃለች።

ብርሃኑም አብሮአት ይስቅና እንዲህ ይላታል። «ዛሬስ ዕውነትሽን ነው ፤ ባገራችን ዱሮ ሴት የወንድ ምክትል ሁና የባልን ረዳትነት ስፍራ ይዛ ፤ ትኖር ነበረ። ዛሬ ግን ጊዜ



ገጽ ፺፫። የዕድላችን መሐንዲሶች ..........

በመራመዱና የምዕራባውያን ሥልጣኔና አስተያየት ባገራችን ገብቶ በመስፋፋቱ ብዙውን ነገር ሊለውጥ ከዚሁ አንዱ የሴቶች ሁኔታ ሁኖአል። ዱሮ ከቤቱ ወይም ከመንደሩ ሩቅ ሂዶ ሠርቶ ለቤተ ሰቡ የሚያስፈልገውን የሚያመጣው ወንዱ ብቻ ነበረ። ዛሬ ግን ጥዋት ባልና ሚስት እኩል ወደ እየሥራቸው ይሰማሩና ማታ በቤታቸው ይገናኛሉ። ልጃገረድም እንደ ዱሮው ባል እስኪገኝላት ድረስ በቤትዋ መጠበቅዋ ቀርቶ አስቀድማ ሥራ ትገባለች። ታድያ ይህ አዲስ ሁኔታ ልጃገረዶችን ከቤታቸውና ከወላጆቻቸው ከለላ አወጥቶ ስለ ወደፊት ዕድላቸው ራሳቸው እንዲያስቡ፥ በገዛ ራሳቸው እንዲመርቱ ፤ እንዲመሩ መብት ሲሰጣቸው፥ በሚዛኑ ደግሞ ፈተናና አላፊነት የጨመረባቸው መሆኑን ሁሉ የተገንዘቡት አይመስለኝም። ሴት ልጅ ሠርታ ፤ አግኝታ ራስዋን በመቻልዋ ከወንድ ላይ ፈላጊነትዋ ስለቀረላትና በምክንያቱም እኩል መብት ስላገኘች ለደስታዋ መጠን የለውም። ነገር ግን የወደቀባት ዕዳ ያን ያህል መሆኑን ሴቶች ሁሉ አላወቁትም መሰለኝ።» አለ ብርሃኑ።

«ይህ የምትለው እውነት ነው።» አለች ተዋበች «ዱሮ ሴት ልጅ በውድም በግድ ቢሆን ከወንድ ፈቃድ ሥር አዳሪ ነበረች፥ ዛሬዪቱ ግን የወንድን ያህል ሙሉ መብት ያላት በመሆንዋ ሁኔታዋ ተሻሽሎአል። ሁኖም ፈተናዋና የተዘረጋባት ወጥመድ ያን ያህል የበዛ ሁኑአል። ፈተናዋን ለማለፍ ያልቻለችውም መነሻ ሳይኖራት ወድቃ የምትቀር መሆንዋ አይጠረጠርም። ይህ ሁኔታ ለጊዜው የገነነው በከተማዎች ብቻ ሲሆን እንኳ፥ ውሎ አድሮ ወደ ባላገር መዝለቁ አይቀርምና ሁሉንም ያጠቃልላል ለማለት ሳንችል አንቀርም።»

«ከአባቶቻችን ከቀድሞ አያቶቻችን የወረስነው ልማድ ተሽሮ በእግሩ አዲስ እንደምን እንደሚተካው ነገር ትገነዘቢአለሽን?» አለ ብርሃኑ። «አሁን ስለምንናገርበት ጉዳይ እንኳ ጥንት ወንዱም እጮኛ ፍለጋ አይወጣ፥ ይልቁንም ልጃገረድ ቀና ብላ ጎረምሳ አታይ። የእርሱና የእርስዋ ወላጆች ወኪሎች ሁነዋቸው አስፈላጊውን ድርጅት በሙሉ ከፈጸሙላቸው በኋላ የልጆቹ ፈንታ መጋባቱና እነርሱም በተራቸው ወላጆች ሁነው ይህንኑ ትርኢይት በልጆቻቸው እየደገሙ ለተከታዩ ትውልድ ማሻገር ነበረ። ዛሬ ግን ሸክሙ በወጣቶች ጫንቃ ላይ ወደቀ። የቆየላቸውን ያባቶቻቸውን ባህል አለ ሐሳብ መከተላቸውን ትተው አዲስ ያገር ልማድ አዲስ ሥነ ሥርዓት እንዲጀምሩ ይገደዳሉ። እንደምታውቂው ሁሉም፥ ጀማሪ የሆነ ሁሉ ብዙ መድከምና ማሳሳት ዕጣው ነውና ይህ ጉዳይ ከኛ ወጣቶችን በጣም የሚያሳስበን ነው። ስለዚህ ይህ ከድሮው ወደ አዲሱ የምንሸጋገርበት ጊዜ የሚያመጣው ደግ ይሁን ክፉ ያልታወቀ በመሆኑ ፤ በተቻለው መጠን ካባቶቻችን ከመጣልን መልካም መልካሙ መርጠን ማስቀረትና ከአዲሱ ባህል ጋር ማዋሐድ ፤ ደግሞ አዲሱ ዘመንና ምዕራባዊ ሥልጣኔ የወለደው ሁሉ በጭፈና መቀበል ሳይሆን፥ ገለባውን ትተን ፍሬ ፍሬውን እንድንይዝ መጣር ዓይነተኛ ተግባራችን መሆን አለበት። ተግባራችንን ችላ ብለን እንደፈቀደው ይሁን ብንል ግን ተከታዩ ዕሬት የማይቀልን ነውና በኋላ ጸጸት በጊዜው መንቃት የሚሻል ይመስለኛል። ለወደፊት ዕድላችን ማሰቡ የእኛ የወጣቶች ፈንታ በሆነው መጠን ማሰብና መድከም አለብን። ስለዘመናችን ሁኔታ ፈጣሪአችንን ወይም አበዎችንን ማመስገን ወይም መንቀፍ ሳይኖርብን የዕድላችን መሐንዲሶች እኛው እራሳችን መሆናችንን ማወቅ አለብን። እኛ አባቶቻችን

እንደምናማርር ወይም እንደምንመርቅ ሁሉ ልጆቻችን ደግሞ ባቆየንላቸው ልክ እኛን የሚያማርሩ ወይም የሚያመሰግኑ መሆናቸውን እንገነዘባለን ወይ»

«አይ ብርሃኑ፥ ቅድም ጨርቅ ከማማረጥ በቀር ሌላ የምታውቂ አይመስለኝም ነበር ያልኸኝ» አለች ተዋበች ራስዋን ደፍታ አንዴ ብቻ ሰረቅ አድርጋ አየችውና «እኔም እንደ አንዳንድ የዘመንህ ጥራዝ ነጠቅ ወጣት በዱቤ አጊጠህ «ሰው በልጅነቱ ካልተጫወተ፥ ቁም ነገሩ ነፍስ ካወቀ በኋላ ይሆናል» የሚለውን ፈሊጥ ይዘህ እስክስታ ስትወርድ የምትውል ትመስለኝ ነበረ እንጂ እንዲህ ሩቅ አሳቢ መሆንህን አልገምትሁም ነበረ።»

ብርሃኑ ይህን ሞገስ በሴት ልጅ ዘንድ ሊገኝ የሚቻለው ሥጋዊና መንፈሳዊ መልክ ሁሉ ባለቤት ሁና ከምትታየው ልጅ አፍ ባገኘ ጊዜ ልቡን ያነደው የነበረውን የፍቅር እሳት መፍጀቱን የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነበረ። «ልብ ስልም ዓይን ጭልም» ሆነ። ድሮ ሰው የነበረችው አሁን መልአክ ሁና ትታየው ጀመረ። ከሰው ልጆች ሁሉ ርቃ በዳመና ውስጥ የምትኖር ፤ የዓለም ሰው ሊደርስባት የማይችል ረቂቅ ፍጥረት የሆነች መሰለችው። እርሱሳ ወደ እንፋሎት ጢስ ተለውጦ ወደዚያ ወዳለችበት ሰማይ ሊወጣና ሊሰግድላት ይችል ይሆን? እረ ማን አዋቂ ይህን ይንገረው? እስከዚያ ድረስ እሳቱ አሳርቶት አመድ እንዳያደርገውሳ ማን ይርዳው?

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ተዋበች ካጠገቡ አራት ክንፍ እንኳ ሳትርቅ ጣቶችዋ ሳይቦዝኑ ጥልፍዋን ትሠራለች። ደግነቱ ይህ በፊትዋ ተቀምጦ የነበረው ወጣት ልብ ውስጥ ይሆን የነበረው ሁሉ ለእርስዋ ሥውር ነበረ። አንዳንዴም ጋዜጣውን እየዘረጋ የሚነብ በመምሰል ፊቱን ይከልል ነበረ። ብርሃኑ ስለዚህ እሳት ቢያወያያት «ምናልባት እርስዋንም ይሞቃት ይሆን» ብሎ አንዳንዴ ያስብና ወዲያው የፍርሃት ብርድ ይዞ ያርበደብደው ነበረ። ንግግራቸው ቁሞ ሁለቱም ዝም ሆነ። ታድያ ጣጣው ገና ነው ልቡ ድው ድው ማለቱን አላቋረጠም።» ላቤን ተመልከታ «ምን ሆንክ» ብትለኝ ምን ብዬ እመልስላታለሁ? «ምነው እንዲህ በድንገት ዝም አልክ?» ብትልሳ «እረ ምን እላለሁ!» እያለ ከመጨነቅ አላረፈም። የተናነቀው ባላንጣ እኮ እንዲህ ፋታ የሚሰጥ አልነበረም ትንሽ ቆይቶ «ምናባቱ አንዴ ልናገራትና ያበጠው ይፈንዳ እያለ አሰበና ፍጻሜ ለማድረስም ሞከረ። ታዲያ ምን ያደርጋል ፤ ለመናገር ሲቃጣ አፉ በብረት ልጓም የተለጐመ ይመስል አልከፈት አለው። «ጉድ ፈላ አሁንስ ድዳ መሆኔ ነው እንዴ?» ብሎ ይቃዥ ጀመረ። «በወረቀት ልንገራት፥ ባፌ ይሻላል? ባፌ ነግሬአት የምትለኝን ብሰማ አይሻልም ይሆን?...»

ተዋበች፥ ከወንበርዋ ትነሣና «አንድ ጊዜ ይቅርታ አድርግልኝ እባክህን ፤ ማዕድ ቤት ፤ ደርሼ ልምጣ» ብላው ሄደች። ጀርባዋን ከመመለስዋም ብርሃኑ ትንሽ ትንፋሽ አገኘና መሐረሙን ከኪሱ መዝዞ ላቡን ጠራረገና ስትመለስለት የልቡን መልእክት እንደምን እንደሚነግራት ቁርጠኛ ዘዴ ያስብ ጀመረ። አቅዱ ግን ከወዴት ይምጣ? እንደዚያ በሐሳብ ሜዳ ሲንቆራጠጥ ተዋበች ከተፍ ብላ «በግፍ ላይ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» የባሰውኑ አደናገረችው።

ተዋበች ተመልሳ በወንበርዋ እንደ ተቀመጠች ብርሃኑ ጋዜጣውን ጣለና ሲናገር አፉን ከፈተ። ድምፁ ግን የማያውቀው የሌላ ሰው መሰለው እንጂ የራሱም ሁኖ አልተሰማው። ሲያምጥ ቆየና «ተዋበች እባክሽን አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ» አላት።

እርሱን እርሱን ታስተውልና ፤ «ምነው፥ ደኅና? ፊትህም የገረጣ ይመስላል ፤ ተናገር እንጂ ምን ሆንክ ፤ አመመህ እንዴ?» አለች ተዋበች።

«በ-ጣም እወድሻለሁ!» አለ ብርሃኑ።

ያበጠው ፊኛዳ ብርሃኑ እፍወይ ሲል ትኩሳቱ ወደ ተዋበች ዞረ። አጋጣሚ ይህኔ በሩ ተንኳኳና ዓለሙ ገብቶ ይህ ትርኢት መጨረሻው ሳይታይ መቋረጡ ቅር ያሰኛል። ተዋበች እዚያው እንግዳ ማረፊያ ክፍል ሁለቱን ትታቸው ወደ ውስጥ በረረች።

## ምዕራፍ አሥራ አራት።

# እንቅፋት

ዓለሙ በክፍሉ ውስጥ እንደ ገባ፥ የእህቱ ችኩል አካሔድና የብርሃኑ ሽብር ሁኔታ ግራ ገባው። ይልቁንም። ብርሃኑ ከ» እንዴት አመሸህ «በኋላ ደህና እደርን» ስላስከተለበት የባሰውኑ መላው ጠፋው።

«ይገርማል፥ አትመጣም ብዬ እህትህን ተሰናብቼ ልሔድ ስነሣ አንተ ደግሞ ከች ማለትህ» አለ ብርሃኑ። «በል ከነገ ወዲያ በቤትህ በጊዜ ትገኝ ይሆናል። እመጣለሁ፥ እንድትጠብቀኝ አሁን ደህና እደር መሽቶብኛል ልሒድ።»

«ትንሽ ቆይ እባክህን፥ ምነው ዛሬ አለ ወትሮህ ተጣደፍክ፥ ትንሽ አጫውተኝና ትሔዳለህ እባክህን አለ» ዓለሙ።

«የለም፥ የለም፥ መሽቶብኛል ደኅና እድር፥ ከነገ ወዲያ እመጣለሁ ጠብቀኝ» ይልና ብርሃኑ ፊቱን ሳይመልስ ጥርግ ሲል ዓለሙ «ምንድር ነው፥ እህ!» እያለ ወደ ምኝታ ክፍሉ አመራ።

ብርሃኑ ወደ ቤቱ ሲመለስ ዓይኖቹ የባቡር መንገዱን ወጭ ውራጅ ለማየት አልቻሉም። ሰላምታ የሰጡት አንዳንድ የሚያውቁት መንገድ አላፊዎችም መልስ ባለማግኘታቸው «ምነው ዛሬስ አቶ ብርሃኑም አለ ወትሮው ለሰላምታ ኮራ «ብለው ሳይሙት አልቀሩም። ብርሃኑ ግን ባንድ ነገር ዓይኑ ታውሮ ልቡ ተሠውሮ ነው እንጂ ትዕቢት የሚባል ነገር እንኳ በሆዱ አልነበረም። ሰሞኑን ቀን በውኑና ሌሊት በሕልሙ የሚታየው የአንድ ነገር ምስል ብቻ ሆኖ የቀረው ሁሉ ተደምስሶበታል። በመንገድ ወደ ወትሮ ተግባሩ ሊሔድም የሚንጠራወዘው መንገደኛ፥ ተሽከርካሪውና የኤሌክሪክ ምሰሶን የመሳሰለው ነገር ሁሉ በድንገት ባድማ ሆነበት። ይህ ፍጡር ምን ይባላል? ሬሳ አይሉት

ይራመዳል። ሕያው ነው አይሉት እንደሰው አይወዛወዝና አይገላመጥ። ብርሃኑ እንደዚህ ምትሀት እንደመሰለ በቤቱ ገባና ከፍሉን ቆልፎ አልጋው ላይ ተዘረረ። እርሱን ከሐሳቡ ጋር ሲተናነቅ ትተን እርስዋ የምትሆነውን ደግሞ እስቲ እንይ።

ተዋበች ብርሃኑ ያለውን ነገር እንደ ሰማች ጆሮዋን ለማመን ተሳናት። ይህን የመሰለ ሐሳብ ይመጣል ብላ ጨርሳ አላሰበች ኑራ ለጊዜው ምን እንደምትናገር ጠፍቶአት አፍዋ ተቆለፈ። የምታስበውም አልገለጽሽ አላት። መንታ መንገድ ላይ ሳለች ወንድምዋ እንደገባም ተቻኩላ ወደ ማዕድ ቤት ሄደችና እሳቱን እየቆሰቆሰች ነበልባሉን በፈጠጡ ዓይኖችዋ ስትመለከት የብርሃኑና የእርስዋን ንግግር ማሳረጊያ ስታወጣ ስታወርድ ቆየች። ከሁሉ ይበልጥ የጣማት ግን እ-ወ-ድ-ሻ- ያለት ነበረ። የኩረኩራት ሳይኖር በድንገት ሳቅ ሳቅ ፤ ይላት ጀመረ። አፍዋንም በግራ እጅዋ ሸፈን አደረገችው። በሰውነትዋም ሙቀት ተሰማት። ይህ ግለት ግን ምንጩ በፊትዋ ካለው እቶን ሳይሆን ከሌላ ነበረ። ብርሃኑ አብሮ አደግዋ ስለ ነበረም በባሕሪው በኩል አሳምራ ታውቀው ነበረና መጠራጠር አላሻትም። የመልኩ ማማርና የባሕሪው ጥራት ወከክ ብሎ ይታያት ጀመረ። በዓለም ውስጥ የሚስተካከለው ሌላ ወንድ ይኖር ይሆን! እርሱ ስሜቱን ገልጾላታል እርስዋሳ መቸ አግኝታው ትገልጽለት ይሆን? እስከዚያ ድረስሳ እንዲህ እየተጠበሰች እንዴት ትቆይ?

* * *

«ውሻና ቀን ሳይጠሩት ይመጣል» እንኳ ነበር የሚባለው ነገር ግን ቀኑ መምጣቱ ይቅርና እየራቀው የሚሔድ ሆኖ ስለ ተሰማው ብርሃኑ የዚህን ምሳሌ እውነትነትን ይጠረጥር ጀመረ። ብቻ እንደማያልፍ የለምና በዣልስቱ ብርሃኑ ወደ አቶ ሰብስቤ ቤት ከቀጠሮው ሰዓት በጣም አስቀድሞ መጣ። እንዲህ ያጣድፈው የነበረውንም ሳንገምት አንቀርም። በሩን እንዳንኳኳም ዕድሉ ሁኖ የከፈተችለት ያቺ በሕልሙ ሲያያት የነበረችው ልጅ ነች። ዓይኖቻቸው እንደተጋጠሙ እንደተጋጠሙ የተሰማቸውን ስሜት በብርዕ ለመተረክ ሰለማይቻል አዝለነው ይሆን? እረ እንሞክር ፤ ፀሐይ ከሰማይ ወርዳ ፊቱ ቁማ የሚያይ መሰለው። ሕይወት በፊቱ ይቻት መሬት ወድቆ እግርዋን ይሳም ወይስ እጅዋን ይሳም፥ መሬት ወድቆ እግርዋን ይሳም ወይስ እጅዋን ይሳም፥ ወይስ ጨረርዋ አደንዝዞት እንዳይቀር ዓይኖቹን ከልሎ ተገትሮ ይቅር? ብርሃኑ ይህን እያለ ሲያመነታ ተዋበች እጅዋን ዘረጋችና «እንዴት ዋልክ፥ ብርሃኑ» አለችው። ታዲያ ብርሃኑ ይህን የመልአኩን እጅ እንደምን ጨክኖ ይልቀቀው።

«እጄን ሰበርከው እባክህን፥ ልቀቀኝና ወደ ቤት ግባ ይልቅ ዓለሙ አሁን ይመጣልሀል» አለችና ሳቀች ተዋበች።

«ዓለሙ ገደል ቢገባ ምን ቸገረኝ» አለ ብርሃኑ አኅበሩን እያስተዋለ።

«እንዴ፥ ወንድሜ!» አለች ተዋበች «ታዲያ ማንን ፈልገህ መጣህ?»

«መቸ አጣሺውና ጨለማ ሲሆንብኝ ጊዜ ወደ ፀሐዬ መጥቼ ትንሽ ቢበራልኝ ብዬ ነው» አለ ብርሃኑ።

«ታዲያ ፀሐይህ የት አለች?» አለ ተዋበች።

«ፊቴ ተቀምጣ ታነጋግረኛለች» አለ ብርሃኑ።

«የዛሬ ፀሐይስ አፍ አላት?» ብላ ሳቀች ተዋበች።

«በይ ይልቁን በሰው መቀለዱን ተይና ቁም ነገሩን አጫውችኝ» አለ ብርሃኑ «ከትላንት ወዲያ እኮ መልሱን ሳትነግሪኝ ወንድምሽ መጣና አቋረጠን።»

«የምኑን መልስ እባክህን?» አለች ተዋበች ፊትዋን እንደ ኲስተር አድርጋ።

«ትወጅኛለሽ ወይ?» አለ ብርሃኑ።

«አዎን!» አለች ተዋበች።

«ተዋበችዬ፥ ካላንች ሕይወት የለኝም» አለ ብርሃኑ።

«እኔም እወድሀለሁ» አለች ተዋበች «ብቻ ወላጆቼን አስቀድመህ ማስፈቀድ አለብህ።»

* * *

ብርሃኑ የአዱኛ በር እንደ ተከፈተለት ሁኖ ተሰምቶት ተስፋው ሙሉ ቢሆን እንኳ እህል አልበላልህ ካለው ሰንብቶአል። ዛሬም አይቶአት ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ፥ ወላጆችዋን እንደምን አድርጎ እንደሚጠይቅ ሲያሰላስል ሌሊቱን አነጋና በወረቀት በቀለም አማካይነት ለመጠየቅ ወሰነ። ላባትዋ የላከላቸው ደብዳቤም እንዲህ የሚል ነበረ፡-

አገረ ሰላም።

መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻- ዓ.ም

ለክቡር አቶ ሰብስቤ ምንተስኖት

አገረ ሰላም።

ክቡር ጌታዬ ሆይ፤

የማክበር ሰላምታዬን ካቀረብኩ በኋላ አስቀድሜ ስለ ድፍረቴ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እየለመንኩ ነው። ጥያቄየም ከባድ እንደሆነው መጠን የአባትነት አስተያየትዎ ተጨምሮበት አስደሳች ፍጻሜ እንደሚያገኝ እተማመናለሁ።

ልጅዎ ወይዘሪት ተዋበች የኑሮ ጓደኛዬ እንድትሆን ልቤ ፈቅዶአልና እርስዎ ለልጅዎ አባት እንደሆኑ ለኔም እንዲሆኑኝ ስለምነዎት ይህ አሳቤ የከረመ መሆኑን በትሕትና እገልጽልዎታለሁ። እርስዎ ከፈቀዱ፥ ወይዘሪት ተዋበች ሳትፈቅድ የምትቀር አይመስለኝም። የዕድሌ ማማሩም ይህች ከሴቶች ሁሉ አብልጬ የማደንቃት ልጅ የማውቃቸውና የሚያውቁኝ የከቡራን ቤተ ሰብ ልጅ መሆንዋ ሐሳቤ ዕንቅፋት ሳይገኝው እንደሚከናወን ካሁኑ ተስፋ እያደረግሁ ደስታ ይሰማኛል። ስለዚህ የአባት ምርቃት ጨምረው የዚህ ውጥን ደምዳሚ እንዲሆኑልኝ ከልቤ የፈለቀውን ልመና አቀርባለሁ።

ልጅዎ ለመሆን የሚመኘው ባለ ተስፋ

ብርሃኑ አባይ።»

ብርሃኑ ደብዳቤውን ለአቶ ሰብስቤ እንደ ላከ፥ የሚሰጡት መልስ ምን መሳይ እንደሚሆን በማውጣትና በማውረድ ሳይጨነቅ አልቀረም። ሁኖም «ከኔ የተሻለ ወንድ ከወዴት ያመጡላታል፥ እኔስ ከማን አንሼ» እያለ ተስፋውን አልጣለም። እኒህ የዱሮ ሰው መልሱን ሳይነግሩት ቢሰነብቱ፥ እስኪያስታውቁት ድረስ ቀኑ እንደሚመሽለትና ሌሊቱ እንደሚነጋለት ነገር መሰንበታቸውን ዘዴ ሲፈልግ ሳለ፥ ዓለሙ ስልክ ደወለለትና አባቱ ሊያነጋግሩት እንደሚፈልጉና የሚመታበትን ሰዓት ለይቶ ነግሮ ገላለው።

ብርሃኑ ከአቶ ሰብስቤ ጋር ተነጋግሮ መልሱን እስኪሰማ ድረስ ሐሳቡን ወደ ሌላ ነገር ለማዘንበል የተቻለውን ያህል ቢል ቢታገል እንኳ ከ«እሺ ይሉኝ፥ እምቢ ይሉኝ ይሆን?» ሐሳብ አዙሪት ውስጥ ሊወጣ አልቻለም። ለሁሉም ነገር ማለቂያ አለውና ቀኑና ሰዓቱ ደርሶ ብርሃኑ እየተደናቀፈ ወደ አቶ ሰብስቤ ቤት ደረሰና ከፍተውለት በእንግዳ መቀበያ ክፍል መርተው አስቀመጡት። አቶ ሰብስቤም ከወደ ጓሮ መጡና በክፍሉ ውስጥ እንደ ገቡ ብርሃኑ ብድግ አለና ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።

«እንዴት ዋልክ አቶ ብርሃኑ» ብለው ሰላምታ ከሰጡት በኋላ አቶ ሰብስቤ ባጠገቡ ተቀመጡና ሻይ እንዲያመጣ አሽከሩን አዘዙ።

«በል አቶ ብርሃኑ» አሉ አቶ ሰብስቤ ጥቂት ሴኮንዶች ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ «ለምን ጉዳይ እንደ ፈለግኩህ መቸም ሳታውቀው አልቀረህም። እንደ አባቶቻችን ደንብ እንኳ የሰው ልጅ ሲፈለግ ሽማግሌ ተልኮ፥ የወጉ ደርሶ ነበረ እንጂ አንድ ብጣሽ ወረቀት አገኘሁ ብሎ ላዩ ላይ ጫር ጫር አድርጎ አልነበረም። ግን ያገራችን ሕግ ሲገሠሥ መቸም ሰንብቶአልና፥ ምን ይደረግ፥ ጊዜው ቢሆን ነውና ከማዘን አልፈን የምናደርገው የለም። አሁን እርሱን እንለፈው እና፥ አንተን የጠራሁህ በቀጥታ ከጻፍክልኝ እኔም በቀጥታ መልሱን ብነግርህ ይሻላል ብዩ ነው። አንተ እንኳን ደህና ልጅ መሆንህን አውቅ ነበረ። እንደ ዘመኑ ሰው ደሞዝህ አነስተኛ ነው፥ ወይም መኪና የለህም ብዩ በማይረባ የልጅ ምክንያት የምቃወም፣ ደግሞ ባልሆንኩ ነበረ። ብቻ ልጄን ለነጋድራስ አስፋው ልጅ ልሰጣት ገና ክርስትና ሳትነሣ ጀመረን የጨረስነው ነገር ሆኖብኝ የተመኘኸውን ጉዳይ ልፈጽምልህ ባለመቻሌ በጣም አዝናለሁ። እንዳጋጣሚ ሁኖም ለመጭው ኅዳር ኪዳነ ምሕረት ዕለት ለፍጥምጥሙ ተቃጥረናል። ታዲያ ሐሳብህ ስላልተሳካልህ እምብዛም

አትዘን ተዋበች ብትቀር ሌሎች ልጃገረዶች ሞልተውልሀል። ከፈቀድክ እኔም በማጠያየቁ ልረዳህ ዝግጁ ነኝ።

ብርሃኑ ይህን በሰማ ጊዜ የእናቱን ሞት መርዶ እንደ ሰማ ሰው ክው ብሎ ቀረ። አንጀቱ እንዳረረ እንደ ተኰማተረ እስከናካቴው አመድ እንደ ሆነ ነገር ከሆዱ ውስጥ ማን ገብቶ ይይ! አፉ ደረቀ፥ ጅማቶቹ ኩምትር አሉ። በሐሳቡ ሥርቶት ከነበረው ሰማይም በድንገት ተቅዘምዝሞ ተከሰከሰና በምድር ላይ መሆኑን አወቀ። «ምነው ሳልፈጠር በቀረሁ ዓይንዋን ሳላይ ሙቸው በነበረ እርስዋን ባየሁበት ዓይኔን እንደምን ሌላ አያለሁ፥» እያለ ያስብ ጀመረ እንዲህ የማያሻማ መልስ ሲሰጡትሳ አቶ ሰብስቤን ምን ብሎ ይናገራቸው? ሊናገር ቢፈልግስ በምኑ? ምላሱ እንደሆነ እንደ እንጨት ደርቆአል። መርዙን እንደ ጣለ ንብ ከንፉን ጥሎ ተዝለፍልፎ ዝም ነው እንጂ! ያን የቀረበለትን ሻይ አንዴ እንኳ ፉት ሳይልለት ብድግ አለና አፉን ሳይከፍት እጅ ነሥቶ ወጣ። ከቤቱ ጥቂት እርምጃ እንደራቀም እንደ ማጥወልወል እያለው፥ በዚሁም ላይ ወባው እንደ ተነሣበት ሰው እያንቀጠቀጠው ወደ ቤቱ ጉዞውን ቀጠለ።

ይህ ተዋበችን እንዲነጥቀው የተፈቀደለት ክፉ ወጣት ምን መሳይ እንደሆነ ሲያስብ አንዳንዴም ቅንቅልፉ ሽለብ ሲያደርገው ተናንቆት ሲደባደብ አደረና እንደማይነጋ የለም፥ ለማኝ ደጅ ሳይወጣ ተነሥቶ ይህን እንጉርጉሮ ለተዋበች ጻፈላት

«አገረ ሰላም።

ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም

የተወደድ ተዋበሽ።

ከሁሉ አስቀድሜ የፍቅር ሰላምታዬን እልክልሻለሁ። ትላንት ከአባትሽ ጋር በቀጠሮ ተገናኝተን የሰማሁትን ነገር ልንገርሽ። የምታውቂው ብትሆኝ ኑሮ በከንቱ እንደማታደክሚኝ ስለማምን ላንቺም ምናልባት እንግዳ ነገር ሳይሆን አይቀርም ብዬ እጠራጠራለሁ። አባትሽ የሚሉትም ለነጋድራስ አስፋው ልጅ ሊድሩሽ ከአባቱ ጋር የቆየ ንግግር እንዳላቸውና በቅርብ ቀን የፍጥምጥሙን ሥነ ሥርዓት እንደሚፈጽሙ ያለቀ ነገር መሆኑን ነው። ይህን ታውቂ ኑሮአል? አይመስለኝም፥ ብታውቂስ አትደብቂኝም ነበረ።

ምን ያህል እንደ ምወድሽ ብርዕ ሊገልሰው አይችልም። ፍቅራችንንም እንዲህ ገና ከቡቃያነቱ የሚቀጨው ሁኔታ በመፈጠሩ የኀዘኔን ልክ ልገልጽልሽ ይሳነኛል። አንቺንስ ዓይኖቼ ሳያዩ ቀርተው ቢሆን ኑሮ ይሻለኝ ነበረ።

በይ ተዋበች፥ ዘወትርም ቢሆን እኅቴ ነሽና አልረሳሽም ፤ ነገር ግን ያባትሽን ፈቃድ መፈጸም ይገባሻል። ደግሞ ላንቺ ይህን ብታደርጊ ይሻልሻል። ምናልባት ልጁ ከኔ የተሻለ ይሆናል። መልካም ዕድልና የደስ ደስ ያለበት ትዳር እንዲገጥምሽ ከልቤ እየተመኘሁ እሰናበትሻለሁ። ደህና ሁኝ።

መቸም ወንድምሽ ብርሃኑ አባይ።

ይህች የመጨረሻ ወረቀቴ ናትና

መልስ መጻፍ አያሻም። ብ. አ.»

ተዋበች የብርሃኑን ደብዳቤ አንብባ ጨረሰችና በእጅዋ ጭብጥ አድርጋ እንደ ያዘችው ቁማበት የነበረ ቦታው ጠፋት። በሩም፥ መስኮቱም፥ ዕቃውም፥ በደፈናው በክፍሉ ውስጥ የሚገኘው ነገር ሁሉ ይዞርባት ጀመረ። ከቆመችበት ወደ ጀርባዋም ስትሰፋበት የነበረች መኪና ክፍትዋን አለች። ተዋበች እንደ መንገድገድ አለችና የምትሆነው ሳይታወቃት ወደ ኋላዋ ፍንችር አለች። ደግነቱ እግዚአብሔር አወጣትና የስፌት መኪናዋን ላመል ስታ ወለሉ ላይ ተዘረረች። እናትዋ ባንደኛው ክፍል ውስጥ ሁነው የዱብታ ፤ ድምፅ ሰሙና ቢጣሩ ጊዜ ማን ይመልስላቸው? ደጋግመው ተጣርተው መልስ ሲያጡ፥ ከተቀመጡበት ተነሥተው ወደ ነበረችበት ክፍል ቢመጡ ጊዜ ተዋበች እዚያ ተሰጥታዋለች። ወይዘሮ ይታከቱ መደነቁና ፍርሃቱ አንድ ላይ ተቀላቅሎባቸው ለመጮህ እንኳ ጊዜ አላገኙም። ሌላ ረዳት እንዳይደርስላቸውም ከፋቱ በግቢው ውስጥ የነበሩ እርሳቸውና ተዋበች ብቻ ናቸው። ከመቅጽበት ብርክክ አሉና ራስዋን ቀና አድርገው ቢያዩ ጊዜ እስትንፋስዋስ አለ። የእርሳቸው እስትንፋስም ይኼኔ መለስ አለላቸውና «ልጄ፥ ተዋቡ፥ ለኔ ያድርገው፥....» ብለው ያጉተመትሙ ጀመረ። ወዲያውም በአጠገባቸው ከነበረው ወንበር ትራስ ስበው ከራውስዋ ስር አደረጉና ውሀ ሊያመጡ ወደ ማዕድ ቤት በረሩ። ቀዝቃዛውን ውሀ ራስዋ ላይ ክልስ እንዳደረጉባት ተዋበች ዓይንዋን እንደ መግለጥ አለችና አንድ ቁና አተነፈሰች። ትንሽ ሳይቆይ ሕዋሳትዋም ተመልሶ ነፍስ ዘራችና እናትዋ ከመሬት አንሥተው በወንበር ላይ አስቀመጥዋት። «ምን ነካብኝ፥ እኔን፥ ምን ሆንሽብኝ» እያሉ ሰውነትዋን ሲደባብሱም ዓይናቸው መሬት ወድቆ በነበረ አንድ ወረቀት ላይ ዓረፈና አንሥተው ካነበቡት በኋላ ብቻ እንቆቅልሹን ሊፈቱ ቻሉ። ዕጥፍ አድርገው በሸርጣቸው ኪስ ውስጥ ይሸጉጡና ተዋበችን ደግፈው ወደ መኝታ ክፍልዋ ወስደው አልጋዋ ላይ አስተኙዋት። እርሳቸው አጠገቡዋ ቁጭ ብለው ጥጥ ሲፈትሉ፥ እርስዋ እንደተኛች መሸና አቶ ሰብስቤ አንኳኩተው ገቡ።

«እንዴት አመሻችሁ፥ ምነው ይታከቱ፥ ልጄ ታማለች እንዴ?» አሉ አቶ ሰብስቤ።

«የለም፥ ደኅና ናነች። ራስዋን ትንሽ አሞአት ነው» አሉ ወይዘሮ ይታከቱ።

«አይ የዛሬ ልጆች! ገና ሳይፈጠሩ መታመም ብቻ። እኛ እንደሆንነ በልጅነታችን ጊዜ በሽታ የሚባል ነገር እኮ አናውቅም ነበረ» አሉና ወደ ውጭ ሄዱ አቶ ሰብስቤ።

ጭር ብሎላቸው እንደገና ብቻቸውን እንደሆኑ፥ ተዋበችም ከእንቅልዋ ተነሣችና ወይዘሮ ይታከቱ ወረቀቱን ከኪሳቸው አውጥተው እየሰጡዋት «ያሳመመሽ ይህ ኑሮአል እንዴ? ምነው ተዋቡ እናትሽ አይደለሁም እንዴ፥ ምነው በፊት ሳትነግሪኝ ቀረሽ?» አሉአት።

«አይ እማማ!» አለች ተዋበች፥ ቀና ፤ ብላ «ካንቺ የምደብቀው ምን ምሥጢር አለኝ ብለሽ ነው? ከእርሱ ጋር ንግግር ከጀመርን እኮ ሳምንትም አልሞላ። የተጨበጠ ነገር ሳይኖር ምኑን ልንገርሽ ብዬ ነው ያቆየሁት።»

«አባትሽም እንደሆኑ እኮ አላጫወቱኝም፥ ወይኔ፥ ከቶ እንደባዕድ ተቆጥሬአለሁ» አሉ ወይዘሮ ይታከቱ።

«እረ እንዴት፥ አባባ ለልጁ መልስ ሲሰጥ ሳያማክርሽ ነው እንዴ?» አለች ተዋበች።

«እንዲያው በጭራሽ» አሉ፥ ወይዘሮ ይታከቱ።

«ወየጉድ! ደግሞ ለፍጥምጥሙ ቀን ፤ ተቀጥሮአል» አለች ተዋበች «እማማ? ለመሆኑ ይህን የነጋድራስ አስፋው ልጅ ታውቂዋለሽ ወይ?»

«አዎን» አሉ ወይዘሮ ይታከቱ «አንቺ፥ ስትድሂ እነርሱ ጎረቤቶቻችን ነበሩ። ነገር ግን ዳር አገር ሲቀመጡ አሁን ወደ አሥራ አምሥቱ ዓመት ሳይሆናቸው አይቀርም ልጁም ይህኔስ ጎርምሶአል።

«ታዲያ እማማ፥» አለች ተዋበች «እኔ ይህን ልጅ አላውቀውም። እንዴት ሁኖ ሚስቱ እሆናለሁ?»

«አሁን ሃሳቡን ተይና ዝም ብለሽ ዕረፊ» አሉ ወይዘሮ ይታከቱ «ስትበረቺ ካባትሽ ጋር እንነጋገርበታለን። አይዞሽ፥ እኔ እናትሽ ካንቺ ጋር ነኝ። በይ መሽቶአል፥ ራትሽን ላምጣልሽ?» ይሉና ትተዋት ወደ ማዕድ ቤት ይሄዳሉ።

* * *

በማግሥቱ ተዋበች በጎ ሁና ከአልጋዋ ተነሥታ እንከስ እያለች ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍል ሄደችና ብርዕዋን አንሥታ ይህን መልእክት ለባለ አድራሻው ጽፋ ሰደደችለት፡-

«አገረ ሰላም

ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻ ዓ.ም

የተወደድከ ብርሃኑ፥

ለጤናህ እጅጉን እንደምን ሰንብተሀል? እኔ ደኅና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ አንተም ደኅና እንድትሆን የሥርክ ጸሎቴ ነው። በጥቅምት ፲፮ ቀን የጻፍክልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል። ካባቴ በሰማኸው ነገር አንተ ያዘንኸውን ያህል እኔም ሳላዝን የቀረሁ አይምስልህ። ሁኖም የመጨረሻ ደብዳቤህን ለመጻፍ እንዲህ የተጣደፍክበት ምክንያት ልረዳ አልቻልኩም። አስቀድመህ ብታማክረኝ ምን ቸገረህ ነበር ፤ እባክህ፥ ትዳርን ያህል ነገር እንዲህ እየተጣደፉ ይሆናል እንዴ? ወይስ ፍቅር መሠረት የሌለው ሆኖ ቶሎ

ቀዘቀዘን? ላንተም እንግዳ መሆኑን በጠረጠርከው አባቴ በነገሩህ ጉዳይ አልተሳሳትክም። የአቶ አስፋውን ልጅ ፊቱን እንኳ አይቼ አላውቅም እርሱም አያውቀኝም። ላባቴ የታያቸው ምን ዓይነት ትዳር ይዘን እንድንኖር መሆኑ አልገባሽ ብሎኛል። ሁኖም በተቻለኝ መጠን አባቴን በስተ እርጅናቸው ላሳዝናቸው አልፈልግም፥ ከፈቃዳቸው ልወጣም አልከጅለውም።

ነገሩ አሁን እንዲህ ጥቅጥቅ ጨለማ ቢሆንብን እንኳ ውሎ አድሮ እስኪበራልን ድረስ በትዕግሥት መጠበቅ እንዳለብን አትዘንጋ። አንተም አንዳንዴ እየመጣህ ብትጠይቀኝ ማናችንንም አይጐዳምና ባንዴ ጥፍት አትበል። ነገ በአሥራ አንድ ሰአት እቤት እጠብቅሃለሁ።

ትላለች አፍቃሪህ፤

ተዋበች ሰብስቤ።»

ተዋበች ይህን ደብዳቤ በላከችበት ሰሞን ከዕለታት አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ አቶ ሰብስቤ በእንግዳ ማረፊያ ክፍላቸው ይቀመጡና ይጠሩአታል።

«እስቲ - ቁጭ በይና የምነግርችን ፤ አድምጭ» አሉ አቶ ሰብስቤ ጉዳዩም ከበድ ያለ ሳይሆን አይቀርም። ልነገርሽ ፤ ያሰብኩት በያን ሰሞን ነገር፥ ብቻ እንደ አጋጣሚ ሁኖ ታመምሽና ሻል እስኪልሽ ድረስ ቆየሁ። ያውልሽ አንቺም አሁንስ ለዓቅመ ሔዋን ደርሰሻል፥ እንግዲህ ጎጆሽን ወጥተሽ ትዳርሽን እንድታበጂ አስበናልና ባልም የነጋድራስ አስፋው ልጅ ተገኝቶልሻልና። አብቱ ትልቅ ሰው ናቸው፥ ከርሳቸው ከተወለደ ልጁም የሚከፋ አይመስለኝም። እንግዲህ ከመሞታችን በፊት አበባሽን እንድናይ የወላጆችሽ ተስፋ መሆኑ አይጠፋሽምና ለዛሬ ወር ለፍጥምጥሙ መቃጠራችንን እወቂው።»

ተዋበች ወለል ወለሉን እያስተዋለች «ለመሆኑ ልጁ ማን ያሰኛል?» ብላ ጠየቀቻቸው።

«ጌታነህ ነው «አሉ አቶ ሰብስቤ» ታዲያ ስሙ ምን ያደርግልሻል።

«ታዲያ እኔ አውቀዋለሁ እንዴ» አለች ተዋበች።

«አሁን በአያሌው ልታውቂው አይደለም» አሉ አቶ ሰብስቤ።

«ታዲያ፥ አባባ ልጁን አላውቀው ፤ የትምህርቱንና የጠባዩን ልክ አላውቅ የእኔና የእርሱ አስተያየት የሚግባባ መሆኑን አላውቅ እኔን ይፍቀድ አይፍቀድ አላውቅ። ለመሆኑ ባገባውሳ ደስ ብሎን እንኖራለን ወይ? አባባ፥ የማላውቀውን ሰው እንደምን አግቢ ይሉኛል?» አለች ተዋበች።

«ለመሆኑ እንዲህ መላሰኛ መሆንሽ አላውቅሁም ነበረ» አሉ አቶ ሰብስቤ፥ «ወይ የዛሬ ልጆች ዓይን አውጣዎች! በኛ ጊዜ እንደሆነ፥ ወላጆቻችን ያመጡልንን እሺ፥ አሜን» በልን እንቀበል ነበረ እንጂ ገበያ ይመስል አንከራከርም። እናትሽን አባቴ አመጡልኝና

ያውልሽ ተጋብተን ዕድሜአችንን አብረን ፈጀነው። ታዲያ ላንቺ ሊከፋሽ ነው? ደግሞ ልጁ የጌታ ልጅ ነው።»

«እኔ ከልጁ እንጂ ካባቱ ምን እንኳ ምን ጉዳይ አለኝ?» አለች ተዋበች «ልጁን የማውቀው ብሆን ኑሮ እንኳ አንድ ነገር ነበረ። አላውቀው ፤ ታዲያ የማላውቀውን ልጅ አግቢ ቢሉኝ እንደምን እሺ እንደምል ግራ ገብቶኛል።

«እንዴት! እኔ ሰብስቤ! መርጬ ያመጣሁልሽን የጨዋ ልጅ እምቢ ማለት ይከጅልሽ ይሆናል እኮ! እንዴህ ታሳፍሪኝ ይሆናላ፥ ወየ ጉድ ወይ ስምንተኛው ሺ ፤ መቆየት ስንት ነገር ያሳያል እናንተ ሰዎች?» አሉ አቶ ሰብስቤ።

«የማላውቀውን ልጅ እንዴት አገባለሁ?» አለች ተዋበች አፍንጫዋን እየጠረገች።

«ልጄ አይደለሽማ፥ ኧረ ያባቴን ሥጋ፥ እከድሻሁአ።» አሉ አቶ ሰብስቤ ብድግ ብለው።

ተዋበች በተቀመጠችበት ሁና ስታለቅስ፥ አቶ ሰብስቤም ከመመለጡ የተረፈው ጠጉራቸው ቁሞ ቁና ቁና እየተነፈሱ እየተንጐራደዱ ሲደነፉ ባለቤታቸው ወይዘሮ ይታከቱ ሁከቱን ሰምተው በመጡ ጊዜ ባላቸውና ልጃቸው በተገኙበት ሁኔታ ተደናገጡና ምን ሆኑ የዓለሙ አባት፥ ምን ነካዎ?» ብለው ጠየቁአቸው።

«ያውልሽ ልጅሽ አሻፈረኝ አልዳርም ትላለች!» አሉ አቶ ሰብስቤ። «እስቲ ይምጡ ይቀመጡና ለሁሉም ነገር ዝግ ብለን እንነጋገርበት፤» አሉ ወይዘሮ ይታከቱ።

«ምኑን ተቀመጥሁት» ይሉና አቶ ሰብሰቤ በወንበሩ ላይ ይንዘፈፋሉ። «ምን አጣላችሁ» እኔ የማልሰማው ጉዳይ ኑሮአል መሰለኝ «አሉ ወይዘሮ ይታከቱ «አሀ፥ በሉ አላግጡብኝ እስቲ፥ ጊዜው የእናንተ የሴቶች ነው መሰለኝ» አሉ አቶ ሰብስቤ።

## ምዕራፍ አሥራ አምስት።

# ቆርቆሮና ሰንበሌጥ

የኅዳር ኪዳነ ምሕረት የምትውልበት ቀኑ ተቃርቦአል። ነጋድራስ አስፋው ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ከሚቀመጡበት አዲሱ አገራቸው ጥንት ወደ ነበሩበት ወደ አገረ ሰላም ከተማ የሚያስመጣቸው ጉዳይ ኑሮአቸው ለጉዞ ሲቀረቅቡ ሰንብትዋል። ከመነሣታቸው አንድ ወር ቀደም ብለውም ታማኝ አሽከራቸውን ፈረጃን አሥር ወቄት ብጫ ወርቅ እና አንዲት ድፍን ኤንቨሎፕ አስይዘው ወደ አቶ ሰብስቤ ዘንድ በገስጋሽ እንዲደርስ ላኩት።

ይህ ድሮ ያደገበት ከተማ በአሥራ አምስት ዓመት ውስጥ መንገዶቹ ሰፍተው፥ አዲስ መንገዶች ወጥተውና ብዙዎች የሚያውቃቸው የዱሮ ቤቶች ፈርሰው ያማሩ አዳዲስ ቤቶች ተከተዋቸው ቢቆዩት እንኳ፥ ፈረጃ መንገዱ ሳይጠፋው ስተት ብሎ ወደ አቶ ሰብስቤ ቤት

ደረሰና መልእክቱን አደረሰ። አቶ ሰብስቤ ወርቁን ተቀብለው በካዝና ውስጥ ከተቱና ኤንቨሎፑን በከፈቱ ጊዜ ያገኙት ደብዳቤ እንዲህ ይላል፡-

«ይድረስ ወደ ክብር ወደ ልዑል ጌታዬ ክቡር እምክ ቡራን አቶ ሰብስቤ ምንተስኖት ማእምር ወለባዊ አማን በአማን ኦርቶዶክሳዊ ርቱዓ ሃይማኖት፥ በአማን እሥራኤላዊ ዘአልቦ ጽልሁት ውስተ ልቡ። እግዚአብሔርን ፈሪ፥ ሰውን፥ አፍቃሪ፥ አገሩን ወዳድ የንጉሡ ታመኝ። ክቡር ጌታዬ ሆይ፥ ሰላምና ጤና ክብርና ምሥጋና ለእርስዎ ለክብር ጌታዬ ይሁን እያልኩ፥ መድኃኔ ዓለም ጤና ይስጥልኝ ብዬ አሥር አሥር ጊዜ እጅ እነሣለሁ። ክቡር ጌታዬ እንደ ዳዊት ለባዊ፥ እንደ ሰለሞን ጥበባዊ፥ እንደ ኢዮብ ታጋሹ፥ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎተኛው ፤ አቶ ሰብስቤ ምንተስኖት ለጤንነትዎ በእጅጉ በአያሌው እንደምን ሰንብተዋል። እኔ ከቤተ ሰቤ ሁሉ ጋር ደህና ነኝ ምሥጋና ይድረሰው ለአምላክ እሥራኤል ሁሉን የሚችለው የሰማይና የምድር ፈጣሪ ጌታ አሜን። ከናፍቆትዎ በቀር የሚጐድለኝ የለም። አሽከሬን ለልጅቱ ትንሽ ጉትቻ መሥሪያ የሚሆን አሥር ወቄት ወርቅ ልኬአለሁና ማነሱን ሳይመለከቱ እንደ ብዙ አድርገው እንዲቆጥሩት ከእግር ላይ ወድቄ እለምንዎታለሁ። ክቡርነትዎ እንደማይዘንጋው የእኔ ሀብት ከወደ ገንዘቡ እምብዛም ሳይሆን ከሥር መሠረት ከአያቶቼና ከክቡር አባቴ (ነፍሳቸውን ይማርና አጥንታቸውን ያለልም) የመጣው ርስት ላይ እኔም ዘንድሮ በግዥና በውርስ አሥራ ሁለት ጋሻ መሬት ጨምሬበት የእርስዎ የክቡር ጌታዬ ብርና የእኔ መሬት ተጋግዞ ያ አብረን አፈር የፈጨነው ፤ በድሮው ደኅና ጊዜ ድንጋይ ዳቦ ሳለ የተነጋገርነው መሠረት የያዘ ስዕለት ተፈጽሞ የእርስዎ ከተማ ሞያና ባልትና በትምህርት ረገድ የሠለጠነችው ልጅ ከልጄ ጋር ትዳርዋን በያዘች ጊዜ ያ የድሮ ፍቅራችን ሥር ሰድዶ ፤ ለዘላለም ፍንክች የማይል ማነቃነቂያ የሌለው ማሠሪያ እንዲሆን ፤ ተፋችን ወሰን የሌለው መሆኑን ስገልጽልዎ ለልቤ የሚሰማው ደስታ ከመጠን በላይ መሆኑን አሳስብዎታለሁ። ይህን ሀብት አብጅተን ለልጆቻችን በተውንላቸውም ዕድሜአቸውን ሙሉ አንዳች ነገር ሳይጐድልባቸው በተድላና በደስታ አለ አሳብ ኑርው እኛ ላባቶቻችን መታሰቢያ ተዝካርና ዝክር ሳናጐድል እንደቆየነው ሁሉ ፤ እነርሱም እኛ በሞትን ጊዜ ነፍሳቸውን ይማር እያሉ ቁርባንና ተዝካር እንዳይጐድለን አድርገው ስማችን ዕለት ምጽዓት ድረስ እንደ ተነሣና እንደ ተሞገሠ እንዲኖር ተስፋችን የማይነቃነቅ መሠረት የያዘ መሆኑን ስገልጽልዎ ለዚህ ዕድል የፈጠረን አምላክ ከሰዉ አብልጦ የሚወደን መሆኑን ማረጋገጫው ይኸው የሰጠን ሀብት ነው። የሥላሴዎች ፈቃድ ሁኖ የኅዳር ኪዳነ ምሕረት ዕለት በአገረ ሰላም ከተማ ተገኝቼ ያን ከጥንት የቆረቆረውን ቃል ኪዳን ፍጥምጥም ለመፈጸም ተስፋ አደርጋለሁ። የሴቶች ሁሉ የበላይ የሆኑት ሞያቸው በጽንፈ ዓለም የታወቀው ትሕትናቸው ቀና ብለው ልጅ እንኳ የማይመለከቱ ፤ ሃይማኖተኛ ጾምና ጸሎት አዘውታሪይቱ ውነተኛይቱ ኢትዮጵያዊ እጀ ዝርግ ሔዋን የሁሉ እናት ባለቤትዎ ፤ ክብርት ወይዘሮ ይታከቱ እንደምን ሰነበቱ ብዬ የአክብሮትና የፍቅር ሰላምታዬን አቀርብላቸውአለሁ። ደሞ ለሽማግሌው አባታችን ጻድቁ መምህር ክንፈ ሚካኤል ሰላምታዬን እንዲነግሩልኝ እለምነዎታለሁ። መድኃኔ ዓለም በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ፤ በምድር ላይ ለመገናኘት ያብቃን ይላል አክባሪና አፍቃሪ ወንድምዎ ነጋድራስ አስፋው ሺበሺ።

ተጻፈ በጥቅምት ፲፱ ቀን ሺ ፱፻- ዓመተ ምሕርት በአገረ ወይን ከተማ በዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ የቅዱስ ገብርኤል ዕለት።»

*   *   *

«አቻ ለአቻ መልካም ጋብቻ።» እረ ለመሆኑ ይህ የተዋበች እጮኛ የነጋድራስ አስፋው ልጅ፦ ስሙ ጌታነህ ነበረ? - ምን መሳይ ይሆን? አባቱ የዛሬ አሥራ ስምንት ዓመት ዳር አገር ርስታቸው ላይ ለመቀመጥ አገረ ሰላም ከተማን ለቀው ቁርበት ጠቅልለው ሲሄዱ ጌታነህ ይዘውት ሄደው ጥርሱን የነቀለው እዚያው አገረ ወይን መንደር ነው። (ይቅርታ፥ አገሬው ይህን ሥፍራ ከተማ ነው የሚለው።) አብሮ አደጐቹ የአባቱ አገልጋዮች ልጆች፥ ሌሎች የባላገር ልጆችና እረኞች ቢሆኑ እንኳ ፤ ከዋልድባ የመጡ አንድ መነኰሴ በአባቱ ቤት ጥገኛ ሁነው ሁለት ዓመት ያህል ተቀምጠው በነበሩት ጊዜ ፊደል አስቆጥረው ፤ ግዕዝ አስጀምረው ፤ ጽሕፈትም ጥቂት አሳዩትና በስዕል ጥበብ ረገድም መስቀል መልአክና የበሬ ጭንቅላት መሳል አስተምረውት ነበረ። ከፍ ብሎ ያነበበው መልእክትም የደራሲው ሙብት የነጋድራስ አስፋው ንብረት ሲሆን ገልባጩ ጌታነህ መሆኑን የማያወላውል ማስረጃ አግኝተናል። ታዲያ አባቱ እንዲት ቀን እንኳ ትምህርት ቤት ሄደው የማያውቁ ፤ ነበሩና ልጃቸው የአበሻ ትምህርት ችሎ ጽሕፈቱን ስላላመረ የአስተዋይነቱን ስፋት እያደነቁ ደግሞ የቀረውን ሞያ በልምምድ ያገኛል በሚል እምነት ከዚህ ወዲያ ትምህርቱን ለመቀጠል የሚያስፈልገው ሆኖ አልታያቸውም። እንዲያውም። «አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ሲማር ዕድሜውን በተማሪ ቤት መፍጀቱ ለልጅ ምን ያደርግለታል?» ብሎ ማስብና ማለት የሰርክ ንግግራቸው ነበረ። ልጃቸውንም ወደ ትምህርት ቤት በመላክ ፈንታ የሞያ ትምህርት እንዲሆነውና ከሕፃነነቱ አንሥቶ አደባባይ እንዲለምድ፥ እግረ መንገዱን በቅሎ እንዲይዝላቸው አስከትለውት ይሄዱ ነበረ። ትከሻው ሥራ እንዳይፈታም አንድ መውዜር ጠመንጃ ያነግትና በአንደኛው እጁ በርኖሳቸውን እቅፍ አድርጎ ይይዛል። አባቱ ችሎት ይሁን ወይም ድግስ ውስጥ ገብተው ከእኩያዎቻቸው ጋር ጊዜአቸውን በሚያሳልፉበት ጊዜ አስፋው ከእርሱ ብጤዎች ጋር የእየበቅሎአቸውን ለኮ እየያዙ ለምለሙ ሣር ላይ እየተገለባበጡ የሚጫወቱት «ከሥራ ቤት ዳሮ እኮ፥ እንትና እኮ እገሊትን...አላት» ዓይነት ጭውውት የትምህርት ክፍል ያህል አእምሮን የሚያስፋፋ አልነበረም። እነኚህ ለዳሚዎች ወሬውንና ቀልዱን ሙጥጥ አድርገው ተጫውተው ባበቁ ሰዓትም የትግል ውድድር መሳይ ያደርጉና ይህንንም ሲጨርሱ ጠጠር ለቅመው ገበጣ መጫወትና ጌስህን መባባል ነበረ። ጌታነህ በዚህ በገበጣ ጥበብ አዋቂ እንደነበረ ተረድተናል። ጀንበርዋ ስታንቃቃቸው ውላ ከአናት አልፋ ወደ ምዕራብ ቁልቁል ማዘገም ስትጀምር ሆዳቸውን በሞረሞራቸው ሰዓት ሲጨዋወቱ የሰማነው «የወንድ ልጅ ልፋት መጨረሻ ግብ ጮማና ጠጅ» የሚል ነበረ። ጌታነህ ቢሆንም የዚህ ባህል ምእመን ነበረ። የጌታነህ ትጥቅ ይህ ሲሆን እስቲ የእጮኛውን ደግሞ እንይ።

ተዋበች ስድስት ዓመት ከሞላት አንሥታ እስከ ዛሬ ዕለት ድረስ ከትምህርት ቤት አዳድላ አታውቅም። ይህም አሥር ዓመት ሙሉ ተግታ ተምራለች ማለት ነው። የትጋትዋ

ማስረጃም በበላጭነት ሽልማት ሳታገኝ ያለፈችው አንድ ዓመት እንኳ የለም። እድገትዋ በከተማ ውስጥ በመሆኑም ከኻያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተፈጠሩ መኪና ራዲዮና መጻሕፍትን የመሰሉ በሚገኙበት አካባቢ ውስጥ በማደግዋ አስተያየትዋ በብዙ ወገን ከዚያ ከቆየው የእናቶችዋ በአያሌው የራቀ ነበረ። ባለባበስ በኩል ቢሆንም ፤ በልጅነትዋ ጊዜ እናትዋ እየሰፉላት፥ ካደገች ወዲህም ራስዋ ሽንቅጥ አድርጋ እየሰፋችው ቀሚሶችዋ ከፓሪስ የመጡ እንጂ የቤት ስፌት ምልክት አይታይባቸውም ነበረ። ታዲያ ይህ ወጣት ፤ በአስተያየቱ ጨዋይቱ ሴት የማዘጋጃ ቤት የጽዳት ክፍል ረዳት የሆነውን መንገድ የሚጠርግ የቤት ፈትል ቀሚስ ለብሳ ፤ ለራስዋ ሻሽ የማትለይ ወዝዋም የሚያብለጨልጭና ከብዛቱ የተነሣ በጆሮ ግንድዋ ሲንቆረቆር የሚታይ ዛጐል ፤ ጠገራ ብር ፤ የነብር ጥፍር ፤ የእርያ ጥርስና ሌላ ጌጣጌጥ የተንጠለጠለበትን ማተብ አንግታ ፤ እጅ እግርዋ በእንሶስላ እና በአልቦ ቀልጦ እጣንዋን እያጤሰች ቡናዋን ሦስተኛ ድረስ የምታንቃርር፥ ፀሐይ ይሁን ዳመና ግድ የለም ጥላዋን ዘርግታ የምትሄደው እወነተኛዪቱ ብሔራዊት ሴት ስትሆን ተዋበች ደረቅ ፤ ዓይን አውጣሽ ፤ አውቃ ፈረንጅ ፤ ቦርሳዋን ብቻ በእጅዋ ይዛ ተረከዙ አንድ ክንድ የሚያህለውን ጫማ ሰከታ ቂብ ቂብ ስትል ሲያይ ምን መስላ ትታየው ይሆን? እንደ ሴቶቹ አትሽኰርመም ደግሞ የጉዱ ጉድ ኩታ መሳይ ሳትደርብ ራቁትዋን ትሄዳለች! መጋባቱንስ ይጋቡ ፤ እረ በኋላ ትዳሩ እንዴት ይሆናል? ቤቱ የሚመራው በማንኛው አስተያየት ሊሆነው? የጌታነህ ባሕሪያዊ የወንድ አዛዥነት በጅ ብሎ ከእርስዋ ሥር ሊሆን ነው ወይስ ተዋበች እርሱን ለማስደሰት ብላ ያደገችበትን ሁሉ ልትረሣ ነው «እኔ የለሁበትም» አለ ጥሬ ጨው። ልጆች ተወልደውሳ የሚያድጉት ባባት ነው ወይስ በእናት ባህል? እነ እንጃ፥ ይብላኝ ለጐረቤትና ላስታራቂ ሽማግሌ።

## ምዕራፍ አሥራ ስድስት።

# የዘሩትን ማጨድ የአልኮል ጠንቅ

ቸኰል ከበደ እንደገና በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ገብቶ ሲተኛ ዛሬ ስድስተኛው ነው። የመጠጥ ሱስ፥ አጥፊው መሆኑን ቢገነዘብ እንኳ አንዴ የዚህ ጨካኝ ጌታ ግዳይ ሆኖ፥ ከወጥመዱ ሊወጣ ደጋግሞ ቢፈትን ቅሉ ከግዛቱ ወጥቶ ድንበር ካለፈ በኋላ አንዳች ነገር ወደ ኋላ እየጐተተው ተውኩት ብሎ ቁርጥ ሐሳብ ያደርግና እንደገና እዚያው ይመለሳል።

ሐኪሞቹ የበሽተኛውን ጽኑ ሕመም ተመልክተው ወዲያው ክፍል ሰጠው አስተኙትና ምርመራቸውን ወዲያው ክፍል ሰጥተው አስተኙትና ምርመራቸውን ጀመሩ። ዛሬ ግን ለመዳን ብዙ ተስፋ እንዳልነበረው ወዲያው ተረዱ ፤ ከውጭ በግዙፍ የሚታየው ሰውነቱ በሙሉ እንዳበጠ ነበረ ፤ ከምርመራቸው ውጤት እንደ ተገለጸላቸውም በተለየ አደገኛ የሆነበት ጉበቱ እየተሸራረፈ አልቶ ኑሮ ከቅንጥብጣቢ በቀር ሌላ የተረፈ ስላልነበረው ነበረ። ታዲያ ይህ ሀያ አምስት ዓመት እንኳ ያልደፈነው ወጥት ዓለም አያለውሁ ሲል ሳያይ ወደ

ሞት ደጃፍ በመጠጋቱ ምርመራቸው ርኅራኄና ሐዘን ቅልቅል ያለበት ሆኖ ተስፋ ሳይቆርጡ ደከሙለት።

በክፍል ፲፫ የተኛው በሽተኛ ቸኰል ከበደ ከቀን ወደ ቀን፥ እየበሰበት ይሄድ ነበረ። በአልጋው ላይ ተዘርሮ ሥቃዩ አንዳንዴ ፋታ ሲሰጠውም እንዲህ እያለ ያስብ ነበረ ፤ በምን ፈረደብኝ አምላኪየ እኔ እንኳ ክፉ አልሠራሁም ነበረ። ሰው በድዬ አላውቅም ፤ የሰው ገንዘብ በልቼ አላውቅም ፤ መጠጡም ቢሆን እንደ ሰው ጠጣሁ እንጂ ሰው የማያደርገውን አላደረግኩም ፤ ክፉ አልሠራሁም ፤ አንዳንዴ ደግሞ መለስ ይልና አዬ ፈጣሪዬ ቅዱስ ሚካኤል የዛሬን አሳልፍልኝ እንጂ ከእንግዲህ ወዲያስ አይለምደኝም። የኑሮዬን አካሄድ ለውጨ ያኔ ዱሮ ሐኪም ዮሐንስ እስክንድር እንደመከረኝ አደርጋለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ አንዴ ልዳን እንጂ እርም ይሁንብኝ ያን መጠጥ የሚባል ነገር ካፌ አላደርስም። ቸኰል ባልጋው ላይ ሁኖ ይህን እንጉርጉሮ ገጠመ።

እረ ምን ዋጣቸው እኒያ ባልንጀሮቼ፤
ምነው አይጠይቁኝ በጠና ታምሜ ተኝቼ።?
ድሮ በመጠጥ ቤት አብረን ተቀምጠን
በእጃችን ብርሌ መለኪያ ጨብጠን
እንደ ጐርፍ ሲፈስ የወይኑ ማይ
ልውጥውጥ ቀለም በጠርሙስ ሲታይ
አዝማሪው ሲያሰማ መልካም ቅኝቱን
እርሱም ሲደክመው ርዲዮን ከፍተን
ሌሊቱን ለውጦ ሲያደርገው ቀን
ተዝናንተን በዚሁ በመሸት ቤት
ብርጭዎዎቹን እያጋባን አንድ ሁለት
ገብተን ነበረ ቃል ኪዳን
ክፉ ቢመጣ ሞትም ቢሆን
እንደማይነታጥለን ወንዳማማቾቹን።
አወይ ፤ የኔ ሞኝነት።
ይኸ መስሎኝ ነበረ እውነት
ቀድሞስ ቃል ኪዳን የሚጋቡበት
ኑሮአል ወይ የመሸታ ቤት

አወይ የኔ ተላላነት።

መጠጥን ሲያወርዱ ለጉሮሮ ሲለሰልስ

ለሆድ የሚበጅ አንጀት የሚያርስ

ካንዴ ሁለቴ ተብሎአል ፍቱን ፈውስ

አንደበት ከፋች ችግር አስረስ

ጤናን የሚመልስ ሕይወት የሚያድስ

የሚያፍታታ ሥጋን የሚነቃቃ ሕዋስ

ወንድም ከውንድም የሚያወቃቅስ

ደግሞ የሰው ልጅ ሆኖ እሱን የማይቀምስ

ከማኅበር ይወጣይበል እብስ

አገር ይልቀቅ ጐንደር ይድረስ

ሰው አይደለም አራዊት እንጂ ርኩስ

ተብሎ ይጠራል እስከ ዛሬ ድረስ።

ጐርፍ ሲወስድ ያሳስቃል

የማይጠጣ ወንድ ሴት ይባላል!

አወይ የኔ ሞኝነት

ይህን ቁም ነገር ብሎ መስማት

መርዙን መጠጥ ብለው ሰይመውት፤

ለሕይወቴ ሆኖአል መቅሠፍት

ባጭሩ አስቀረኝ አደረገኝ ቅጭት።

ሐኪሞቹ የተቻላቸውን ያህል ልዩ ልዩ ሕክምና መፈተናቸው አልቀረም ነበረ። ነገር ግን ምንም ቢደክሙለት እንኳ አዲስ ጉበት ማብቀል ከዓቅማቸው በላይ ስለ ነበረ ፤ ልፋታቸው ፍሬ ሳይሰጥ ቀረ። በሰው በኩል ሊደረግ የሚቻለውን ሁሉ ቢያደርጉለት እንኳ ቸኰል በጎ የመሆን ተስፋ ሳያሳይ ቀረ ፤ ሕመምም ያጣድፈው ጀመረ። መብላትና መጠጣት ጨርሶ ተነሣው። በኋላም ማቃሰቱ ቀረና ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይል ጀመረ ሐኪም ቤት በገባ በሦስት ወሩም ከዚህች ዓለም በሞት ተለየ።

የሐኪም ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሟቹን የቅርብ ዘመድ አድራሻ ባጣ ጊዜ ድሮ ይሠራበት ወደ ነበረ መሥሪያ ቤት ስልክ ደውሎ የሞቱን ዜና ለአለቃው አስታወቀ። ጓደኞቹ ሞቱን

በሰሙ ጊዜም ተደናግጠው አያሌ ወራት በጽኑ ታሞ ሲተኛ ለመጠየቅ ባይመቻቸው እንኳ ፤ አሁን በቀብር እንዲክሱት ቁርጥ ሐሳብ አደረጉ። ወዲያውም ለፍትሐቱ የሚሆነውን ገንዘብ አዋጡ። የመሥሪያ ቤቱ አዲሱ ዋና ዲሬክተር ልጅ መኵሪያ በላይም ለጓደኞቻቸው ስልክ አድርገው ኑሮ ብርሃኑ አባይና ዓለሙ ሰብስቤ ለቀብሩ ደረሱ።

ከዚህም ከዚያም በርከት ያለ ሰው ተጠረቃቀመና ፤ ሬሳውን አጅበው የፍትሐቱን ጸሎት እየደረሰ በዓለም ውስጥ የመጨረሻው ርስቱ ወደ ሆነው ወደ ሁለት ካሬ ሜትር መሬት ሸኙት።

ወደ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እንዳመጡት በፊታቸው ተደቅኖ የቆያቸው ትርኢት እነ መኵሪያን በጣም ገረማቸው ከዚህ ሥፍራ ከተለዩ አያሌ ዓመታት አልፈው ነበረና በነዚህ ዓመታት ውስጥ ተለዋውጦ ያገኙት ነገር በልባቸው ውስጥ መደነቅን እና ደስታን ሞላ። ሕዝቡ ለሃይማኖቱ ቀናተኛ በሆነው መጠን ቅዱስ ስፍራውን እንደሚያከብረው አኳሆን እዚህ ቦታ ይታይ ነበረ። ያ ድሮ የማያውቁት ወጣ ገባ መንገድ ቀርቶ በትክክል የተሠሩ መንገዶች የቤተ ክርስቲያኑን ምድረ ግቢ አፋፍለውታል። ኅብራቸው እንደ ቀስተ ደመና ቀለሞች ያማረ አበባዎችና በመንገዶቹ ርዳቻ ጉች ጉች ያሉት ቁጥቋጦዎች የተመልካቹን ዓይን በውበታቸው ያጠግቡ ነበረ። ግን ድንቁ ይህ ብቻ አይደለም ፤ የበለጠ ይጠብቃቸው ነበረ።

መቃብሮቹ ወዳሉበት ወደ ጓሮ በዞሩ ጊዜ የተመለከቱት ነገር ለዓይኖቻቸው እንግዳ ነበረ። መቃብሮቹ በረድፍ በረድፍ ተሰልፈው፥ ተርታቸው ስሕተት የለበትም። የለምለሞቹ መስኮችና የአበባ መደቦች ሥራም ፤ እንከን በማይገኝበት ቅያስ ተፈጽሞአል። የሐውልቶቹ ሥራ ለዓይን እንዳይሰለች ልውጥውጥ ሁኖ ሁሉም በኪነ ጥበባዊ ጌጥ አምረው ይታያሉ። የዚህ ስፍራ ጽዳትና ወበት አያት የልጅ ልጆቹን ይዞ እንዲናፈስበት፥ ወይም እጮኛዎች እሑድ ከሰዓት በኋላ እጅ ለእጅ ተያይዘው የወደፊት ማረፊያቸውን እያሰቡ እንዲንሸራሸሩበት የሚያስመኝ፥ ወይም ከአገሩ ተሰዶ በሰው አገር የሚኖረው የአገር ተወላጅ የአባቶቹ አገር ትዝ ሲለው ከመሞቱ በፊት አንዴ እንደ ገና ሊያየው የሚናፍቅ ስፍራ ሁኖአል። ግሩም ነው እኮ! የዚህ ደብር ባለ አደራዎች ለበላይነት ፤ መፎካከራቸውን ትተው ሥራ ለመሥራት የሚሽቀዳደሙ መሆናቸው ካከናወኑት ተግባር ጉልህ ሁኖ ይታይ ነበረ። በብዙ ሺሕ ዓመታት ታሪኩ የሚመካውና ለወደፊትም ከዓለም ታሪክ ተራ እንዳይታጣ የሚፈልገው ሕዝብ ዜናዊው አገሩን እንዲጐበኙ ለሚመጡት እንግዶች ኮርቶ የሚያሳያቸው፥ በወሬ ከሰሙት በልጦ የሚገኘው ትንግርታዊ ትርኢት ይኸው! ግንጫቸውን መልጠው ጠጉራቸውን ላጭተው፥ ከል ለብሰው የሚያለቅሱት ፤ «አብሬ ልቀበር» ብለው የሚተናነቁት ሐዘንተኞች ለሞቱት ዘመዶቻቸው መድበው በክቡር የሚጠብቁት ስፍራ ይኸውና። ገና በሕይውታቸው ሳሉ የገዛ ተዝካራቸውን አውጥተው የሚያበሉት ሰዎች የወድፊት ማረፊያቸውን እንደምን አድርገው እንደሚያስቡለት አጉልቶ የሚያሳይ እዚህ አለላችሁ። ጽዳትና ሥርዓት ዓይነተኛ መልኩ የሆነ የተመልካችን መንፈስ አድሶ «ገና ትንሽ ቆይ» የሚል ስፍራ ሁኖአል። በኑሮና በጤና የሰው ልጅ እልፈት ምሳሌ የሆኑት ነዳያን ሌላ ማረፊያ ተደርጎላቸው በዚህ ቦታ ጨርሶ አይታዩም። መሞታቸው የተቃረበ፥ አረጋዊ ቀርቶ ወጣቱ እንኳ ሳይቀር፥ ይህን ስፍራ

ተመልክቶ «የዓለም ጉዞዬ ተፈጽሞ እዚህ ንጹሕ ስፍራ መቸ መጥቼ ዓርፌ» የሚያሰኝ ስፍራ ሁኖአል። ዕድሉ ሆነና ቸኰልንም የመጡት ወደዚህ ስፍራ ነው።

በሞት በሳምንቱ የቸኰል ዜና ሞት ከእነ ፎቶግራፉ እና ከአጭር የሕይወት ታሪክ ጋር በጋዜጣ ወጣ። ከዚሁም የታሪኩን ክፍል ዘልለን የአባቱን የሐዘን እንጕርጕሮ ብቻ ቀድተን እናቀርባለን፦0

<u>የአቶ ከበደ የሐዘን እንጕርጕሮ።</u>

አወይ ቸኰል ልጄ፥ አልለቅ ብልህ
ትተኸኝ ለመሄድ ምን፥ አስቸኰለህ?
ትንሽ ብትታገስ እረ ምን ቸገረርህ።
ተው ቆይ እባክህን፥ አታጣድፈን፤
ተራዬን ልቀቅ ፍጆታ ስጠኝ
እኔስ ባንተ ላይ ተስፋ ነበረኝ።
ችለህ ራስህን እንድትይዝ ትዳር፤
ተነጋግሬልህ ፤ ነበረ ከጨዋ ሰው ጋር፤
እርሱም አቻችን ልጁም ወላላ ማር።
ግን ፤ ቸኰል ብሎ ስም ካወጣሁልህ፤
አንተስ ብትጣደፍ በደል የለብህ፤
ጥፋቱ የኔ ነው የዝንጉው አባትህ።
እረ ቸኰል ልጄ ሥነ ሥርዓት ተማር፤
በዕድሜ የሚበልጥህን ታላቅህን አክብር፤
እኔ ልቅደምና አንተ ወደኋላ ቅር።
ሽማግሌ እያለ ልጅ ሲቀድም፤
ሰልፍ ተበላሸ፥ አገባብ አይደለም፤
ለዓይን ደስ አይል ለወሬም አይጥም።
አታሳፍረኝ አደራ ፍጥምጥሙ አይቅር ከንቱ፤
ጐጆአችን አይፍረስ አይሰበር ቤቱ፤
ወራሽ አጥቶ ፤ አይባክን ንብረቱ።

እንደዚህ ባጭሩ ልትቀር፤

እረ የሚያስቸኩልህ ምንድር ነበር፤

አይሻልም ነበር ወይ ዓርፎ መማር?

ቀንድ ይነክሳል የጅብ ችኩል፤

ብለው አባቶቻችን ተርተዋል፤

ዛሬም ቢሆን አልተሻረም ይህ ቃል።

ያ ልጅ በትምህርት የበረታ፤

የሥጋውን አምሮት የገታ፤

ለወገኑና ለአገሩ ሆነ ዋልታ።

ግን ወዳዱ የጨዋታ የቧልት፤

ለወለደችው እናት ነው ጸጸት፤

አለ ቀንዋ አደረሳት ከሞት።

ልጄ ቸኩል ፤ ልጄ ቸኩል፤

አትጣደፍ ተው ዝግ በል።

የዝላይ ትርፍ የለው ከመንከባለል።

እረፍ በል ቸኩል ከልክ ደንብ አላከብርም፤

ዘፈኑን ጥገበው በአያሌው በጣም።

በሄድክበት አገር ጓደኞችህን አታጣም።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት።

# የአጋጣሚ ጉዳይ።

አንድ እሑድ ከሰዓት በኋላ ልጆቹ ደጅ ኳስ ሲጫወቱ ፤ በዕረፍት ጊዜ ልማዱ እንደ ሆነው ሁሉ አቶ ብርሃኑ አባይ በእንግዳ መቀበያው ሳሎን ተቀምጦ መጽሐፍ ይመለከት ነበር። ከልጆቹ አንዱ ገብቶ ያቋርጠውና «አባባ ለማኝ ፤ መጣ፥ እባክህን ገንዘብ ስጠው» አለ። ልጁ ይህን ብሎ ከማለቱ ሰማዩ እያጕራ ዝናሙ ጠብ ጠብ ይል ጀመረና ሰውየው ወደ ስብሳቡ ጠጋ ብለው አጠለሉ። ዝናሙ ግን እንዲህ በዋዛ የሚለቅ አልነበረም። ብርሃኑም ልጁን ልኮ ለማኙ ቤት እንዲገቡ አደረገ።

እኒህ ሰው ከውጭ አገር በቅርብ ጊዜ የመጡ መሆናችው በአለባበሳቸውና በሌላው ሁኔታቸው ጐልቶ ይታይ ነበረ። ብዙ ችግር ያሳለፉ ለመሆናቸውም በግንባራቸውና በዓይኖቻቸው ዳርቻ የሚታዩት ኩምትር መሥመሮች ይመሰክሩ ነበር። ቁመታቸውም ዘለግ ያለ መልካቸው የቀይ ዳማ፥ ጺማቸው ላይ አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ያደረገበት ዓይነጐረጥ ውብ ሰው ነበሩ። የራስ ፀጕራቸውን ሁኔታ ለማየት እንዳንችል ተላጭተውታል። እይለበሱት ካባም ፤ ስለብዙ ዘመን አገልግሎቱ ጡረታ እንጂ ወር ተራ የሚገባው አልነበረም። ከእግሮቻቸው ብዙ ውለታ አግኝተው፥ እንደ ነበረም ከተረከዞቹ ለመገመት ይቻላል።

«ዝናቡ እስኪያባራልዎ ድረስ ዓረፍ ይበሉ፥ መምሩ» አለ ብርሃኑ።

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ፥ እግዚአብሔር ያቆይዎ፥ እሺ እንጂ ምን ሽፋኝ ጌታው» ይሉና መምህርቱ ወንበሩን እንደ መፍራትና እንደ ማክበር ብለው ከዳርቻው ቁጢጥ አሉ።

«አሳምረው ይቀመጡና» አለ ብርሃኑ። «እባክዎን ከወዴት አገር መጡ?» ብሎ ይጠይቃቸዋል።

«ኸጐንደር ነው የመጣሁትኝ አሉ» መምህሩ።

«ከዚያ ካገር ቂጥ እዚህ ድረስ ምን አመጣዎ?» አለ ብርሃኑ «ጐንደር እኮ ከዚህ በጣም ሩቅ ነው።»

«ለርቀቱስ ኸጽንፌ ምድር ነው፥ ዛድያ ፤ ምን ይሆናል ነገር ኻለ! ያውልዎ ጌታው በነገር መጥቼ ጉዳዩ አልቆረጥ ብሎኝ ስንቄን ጨርሼ ኸዚሁ ኸረምኩ» አሉ መምህሩ።

«አገርዎ ጐንደር ሳይሆን አይቀርም አነጋገርዎ የዚያ አገር ሰው ነው» አለ ብርሃኑ።

«እረ አገሬስ ኸዚሁ ነበረ ፤ ዳሩ ግን ሙጫቅላ ሳለሁ ወደ ጐንደር ለትምህርት ሄጄ ጊዜና ኸዚያው ወልጄ ዘምጄ ቀረሁኝ። ዛድያ እንዲህ አገሬ እርሱው መሆኑ አልቀረም መሰለኝ አሉ መምህሩ።

«ወደ ጐንደር ከሄዱ ስንት ዓመት ሆነዎት?» አለ ብርሃኑ።

«ልክም የለው፥ እንግዲህስ ኸወደ ሠላሳው ዓመት ይጠጋል» አሉ መምህሩ።

ይህን ጊዜ ብርሃኑ ደውሉን ይደውልና ገረዲቱ ስትመጣ ቡና እና ቁርስ እንድታመጣላቸው አዞአት እንደገና ወደ እንግዳው መለስ ብሎ ንግግራቸውን ይቀጥላሉ። እንዲህ እያለም ጥያቄውን ያከታትልባችዋል።

«በልጅነትዎ እዚህ አገረ ሰላም ሲኖሩሳ ሠፈርዎ ወዴት ነበር?»

«ትንሽ ትንሽ እንደሚታወሰኝ፥ ኸቦታችን አቅራቢያ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነበረ» አሉ መምህሩ።

«አለመሆኑ በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በኔብረ አንድ የቄስ ትምህርት ቤት ይማሩ ነበር ወይ?» ብሎ ቀጠለ ብርሃኑ።

«አዎን እንጂ ፤ አለቃ ክንፈ የሚባሉ ሽማግሌው አስተማሪአችን፥ ነፍሳችውን ይማርናቸ፥ አንቱ ነበሩ» አሉ መምሩ

ብርሃኑ ይህን በሰማ ጊዜ ፊቱን ጨምደድ አድርጎ ራሱን በእጆቹ ያዘና አጥልቆ ያስብ ጀመረ። አእምሮው ወደ አበሻ ትምህርት ቤት ጊዜ ተመለሰና ያኔ ጓደኞቹ የነበሩትን ሊያስታውስ ይጣጣር ጀመረ። ጥቂት እንደቆየም ቀና ይልና «መምህሩ ስምዎ ይኄይስ ነው ወይ?» ብሎ ይጠይቃቸዋል።

«እረገኘ፥ ጉድ ነው፥ አዎን እንጂ፥ ስሜ ይኄይስ ነው ኸወዴት ሰሙት ጌታው?» አሉ መምህሩ ተደናግጠው። ነጋሪ ሌላ ሰው በክፍሉ መኖር አለመኖሩንም በዓይናቸው፥ ይሰልሳሉ።

ብርሃኑ ግን ለጥያቄአቸው መልስ ሳይሰጥ ይህን ያስከትልባቸዋል፦ «ለመሆኑ ብርሃኑ አባይ የሚባል እዚያ አለቃ ክንፈ ዘንድ ይማር የነበረ ልጅ ያስታውሳሉ ወይ?» አላቸው።

«እጅግ እንጂ እኔ ኸዚያው ኻለቃ ክንፈ ትምህርት ቤት ስቀር እርሱ ወደ ንጋት ኮከብ ትምህርት ቤት ተዛወረ። ኸዚያ ወዲህ ተያይተንም አናውቅ። በዓለም ይኑር ይሙት የሚነግረኝ ሰውም አላገኘሁም» አሉ መምህሩ።

«ብርሃኑ እኮ እኔ ነኝ!»

«ወንድሜን ፤ እነነ ክንብል ያርገኝ፤» ብለው ብድግ ይሉና ተናንቀው እየተላቀሱ ተሳሳሙ።

ወይዘሮ ተዋበች ሰብስበ የብርሃኑ ባለቤት ከወደወጥ ቤት መጥተው ባላቸው ከለማኙ ጋራ ሲሳሳሙ ከተፍ ባሉ ጊዜ እንቆቅልሽ መፍታት አቅቶአቸው በቆሙበት በበሩ አጠገብ እንደ ዕንጨት ደርቀው ቀሩ። ብርሃኑም ይጣራና «ተዋበች ፤ ነይ ሰላምታ ስጭው እባክሽ ፤ መምህሩ እኮ አብሮ አደጋችን ይሄይስ ነው። ያኔ ድሮ ፤ ድሮ በቄስ ተማሪ ቤት በኔታ ክንፈ ዘንድ ስንማር አብሮን ይማር እኮ ነበረ። መሰነብት መልካም ነው ወይ ስንት ነገር ያሳያል!» አላቸው።

*  *  *

ወይዘሮ ተዋበች በርረው ይመጡና ይሄይስን አገላብጠው ከሳሙት በኋላ አብረዋቸው ቁጭ ብለው ሦስቱም ተጨዋወቱ። ጣፋጭ ሕልም ነበረ!

«ይኸን መነጽር አድርገህ እንዲህ አምሮብህ ቆሲል መስለህ ቤተ መንግሥት በመሰለ ሕንፃ ውስጥ አገኝሀለሁ ብዬ በውኔ ቀርቶ በሕልሜም አላሰበው። እረ በል እስቲ፥ ይኸን ሁሉ ዘመን ኸየት ትኖር ነበረ? እስቲ ታሪክህን ንገረኝ እባክህን፥ ልሰማው ጕምጅቻለሁ። ይኸን ቤት ተከራይተውኸ ነህ? አለ ይሄይስ።

«እረ የራሴ ነው፥ ዓምና ሠራሁት» አለ ብርሃኑ «የሕይወቴ ታሪክ ግን ጊዜ እንዳይፈጅብህና እንዳላስመሽብህ ለሌላ ጊዜ ብናደርገው አይሻልም ወይ?።

«እኔ ምን ሥራ አለኝ ብለህ ነው እባክህን፥ ስዞር መዋሌ ነበረ እኮ አንተ የምትኼድበት እንዳይኖርብህና ሥራ እንዳላስፈታህ እንጂ» አለ ይሄይስ። «አሁንማ ቸሩ እግዚአብሔር እንዴ አገናኝቶን ኼእንግዲህ ወዲያ ኼየት ተላቅቀን። እረ በል እስቲ ንገረኝ ይልቁን ወይ ብርሃኑ፤»

«እንግዲያስ ያውልህ» አለ ብርሃኑ «ከአለቃ ክንፈ ትምህርት ቤት ወደ ንጋት ኮከብ አንደኛ ደረጃ አባቴ አዛወሩኝና በዚሁ ስድስት ዓእምት ተምሬ ሳበቃ ወደ ነቅዓ ጥበብ ሁለተኛ ደረጃ ተዛወርኩ። በነቅዓ ጥበብ አራት ዓመት እንደ ተማርኩ ዕድል አጋጠመኝና በመንግሥት ኪሣራ ወደ ፈረንጅ ፤ አገር ሄድኩ። ትምህርቴን በስድስት ዓመት ውስጥ አከናወንኩ የምስክር ወረቀቴን ተቀብዬ ከተመለስሁ እንግዲህ ወደ አምስቱ ዓመት ተጠግቶአል። አሁንም የኔን ያህል ዕድል ላልገጠማቸው የአገሬ ሰዎች ያገኘሁአትን ዕውቀት በማካፈል የተደረገልኝን ውለታ መመለስና የአገሬን ሰው በሞላው ተደስቶ እንዲኖር ማሰብን የሕይወቴ ዓላማ አድርጌ በትምህርት ሚኒስቴር እሠራለሁ። ከፈረንጅ አገር እንደተመለስኩ ባመቱ ይህችን ያየኻትን ተዋበችን አገባሁና እግዚአብሔር ፍሬ ሰጥቶን ልጆቻችንን ፤ ደጅ አይተኻቸዋል። ይህን ቤት ደሞ አምና «ሠርተን ጨረስን። ያውልህ፥ እስቲ አንተ ደግሞ ተረቴን መልስ አፌ በዳቦ አብስ።»

ይሄይስ ይህን ታሪክ አቀርቅሮ ሲያዳምጥ ቆየና እንዲህ አለ - «እህ፥ ግሩም ነው፥ እንዲህ አድርጎም ዕጣ የለ አንተስ የተፈጠርከው በርጥብ ቀን ኑሮአል፥ ከቶ ምሩቅ ብትሆን ነው። ደሞዝህሳ ስንት ነው?»

«በወር ፭፻ ብር አገኛለሁ፤» አለ ብርሃኑ።

«እሰይ፥ አሳምረህ ትዝቀው የለም እንዴ» አለ ይሄይስ።

«በል ተራህን ንገረኝ እኮ አለ ብርሃኑ።»

«የኛማ ምን ታሪክ አለው ብለህ ነው ፤ ያው የምታውቀው ነው ፤ አዲስ ነገር የለበት። ስንለምን አድገን ስናድግ እንለምናለን። ከደብር ወደ ድብር፥ እየተዘዋወርን ኼትህልልቆቹ መምህራንና ሊቃንው ዘንድ የሀገራችንን ትምህርት እንቀሥማለን። እኔ ኼአለቃ ክንፈ ትምህርት ቤት ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄጄ ጊዜና ሦስት ዓመት ብሉይና ሐዲስን ተማርኩ። ኼደብረ ሊባኖስ ተነሥቼ በደብረ አባይ አምስት ዓመት ዜማ ተማርኹ። ኼደብረ አባይ ወደ ደብረ ዝቋላ ሄድኩና ጊዜ አሥራ አምስት ዓመት ቅኔ ተማርኩ። ጊዜዬን የፈጀብኝ ደግሞ እንደምታውቀው የታተሙ መጻሕፍት ባለማግኘቴ ትምህርቴን ሁሉ በቃል ማጥናት ስለነበረብኝ ነው። ወደ ኻያ አምስቱ ዓመት ያህል ተምሬአለሁኝ ፤ ነገር ግን ምንም አላለፈልኝ። ሥጋችንን በድለን ለነፍሳችን አድረናል። ሥላሴዎች በወዲያ እንዲክሱን ተስፋ አለን» ይልና «እህህህ» ብሎ ብዙ ይተነፍሳል።

«የገዛ ራስህን ብታማርር በውነቱ ተሳስተሀል» አለ ብርሃኑ «አንድ ተማሪ የተመደበለትን ተግባር ከፈጸመና ጉድለቱ ከቀረበለት የትምህርት ገበታ ከሆነ፥ በተማሪው ላይ እንደ ምን መፍረድ ይቻላል? አንተ ደግሞ ያን የቀረበልህን ትምህርት በትጋት ሳትሳተፍ የቀረህ አይመስለኝም። አንድ ሰው ነፍስ ባወቀ ጊዜ የሚሠራው፥ አእምሮው ገና ለጋ ሳለ በሕፃንነቱ ከቤቱ ከትምህርት ቤቱ እና በጠቅላላው ካካባቢው ሰምቶ፥ አይቶና ዳስሶ ባጠናው መሠረት አእምሮው በተቀረጸ እንደሆነ የሥነ አእምሮ ጥበብ ተመራማሪዎች ይገልጹልናል። ያገራችን የዱሮ ዓይነት ተማሪዎች ግን ከሌላው ትምህርታቸው ጋር «ብላዕ በሀፈ ገጽከ» የሚለው ከእጅ ሥራ ድካም በኋላ የሚገኘው ጣፋጭ እንጀራ ጐድሎባቸው ያገድሉ። አብሮ ያደገ ሁኔታም እስከ ዕለተ ሞት የሚቀይ እንጂ እንዲህ በዋዛ የሚለቅ አይመስለኝም የእጅ ሥራ የሌለበት ሞያም ያፍ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ከስፖርት የሚገኘውን የሰውነት ጥንካሬና ፤ ተባብሮ የመሥራትን መልካም ልማድ ሥነ ሥርዓት እንዳያገኙ መቸ ተጨዋወቱ እጃቸውን የቆዳ ሕመም ካላሸከረ በቀር መለስለሱ የወይዘሮ እጅ ምሥጋና ይንሣው። መጻሕፍት የላቸው የቃል ጥናት ብቻ። የደንበኛ ክፍልንና የጠመኔን ሞያ አላዩ ፤ ንጽሕናና፥ ሂሳብ ፤ ስነ ጥበብን ማን ገልጾላቸው። ታድያ፥ ይኄይስ ወንድሜ ሆይ የምታዝንበት ምንም የለ ፤ ጉድለቱ ከአንተ አይደለም።

«ይኸ የተናገርኸው እውነት ነው ለመሆኑ ብልህ ወጥቶሀል» አለ ይሄይስ «ታዲያ ምን ይበጀው ይመስልሃል?»

«የሰው ልጅ፥ እንዲያውም የማናቸው ፍጡር ቀዳሚ ተግባሩ» አለ ብርሃኑ «በወላጆቹ ወይም በማኅበሩ ትከሻ? እንዳይኖር ራሱን መቻል ነው። ይልቁንም ሰው በዚህ ዓለም የተፈቀደለት ዕድሜ ማቋረጫውን ስለማያውቅ፥ እያንዳንዱ አዲስ ቀን እንደጨረሻ ቀን ቈጥሮ ለራሱና ለማኅበሩ ጥቅም በትጋት ለመሥራት አለበት ፤ ለወገኖቹ እና ለማኅበሩ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ራሱን ከቻለ በኋላ ብቻ ነው። ነገር ግን እነዚያ ተምረው ከመሃይምኖቹ ይሻላሉ የሚባሉት እጃቸውን እየዘረጉ ለኑሮአቸው ካልተማረው ላይ ፈላጊዎች ከሆኑ፥ ትምህርታቸው ረባ የሌለው መሆኑ፥ ጉልህ ነው። ስለዚህ እናንተ የሕዝብ መሪዎች ሁናችሁ ከፍተኛውን ሥፍራ በያዛችሁት መጠን ለመንጋችሁ በአኗኗራችሁ መልካም አርአያ መሆን እንዳለባችሁና መንጋችሁም የሚከተለው ትእዛዛችሁን ወይም ምክራችሁን ሳይሆን ፋናችሁን መሆኑን ማወቅ አለባችሁ። ለቀረው ብርሃን ካልሆናችሁ፥ በእውነቱ በከንቱ ተፈጠራችሁ።

«ይሁን እኛንስ ውረድብን» አለ ይኄይስ ዘመናዊውን የባዕድ ትምህርት ፤ ተምሮ ሠልጥኖአል የሚባለው ኰበሌው ወጣት እንዴት ነው ልትለኝ ነውሳ? አርብ ረቡዕ አይል፥ ቤተ ክርስቲያን አይስም የነፍስ አባት የለው፥ ደግሞ የባሰ አለ፥ እንጂ ጌታ የረገማትን አበው ያወገዙአትን ጢምባሆን ማንም ሳይፈራ እያቅበጠበጠ ያጤሳል። ያለባበሱንማ ተወው! ሸማ አጣፍቶ የሚችል ከሺ አንድ እንኳ አይገኝም። ንግግሩንም ለውጦአል እንጂ «ዓረፍ በል» ወይም «ተኮፈስ» እንደ ማለት «ወንበር ውሰድ ይባልልኛል።» ቡና ጠጣ እንደማለትም «አንድ ቡና ፤ ውሰድ» ይላሉ። በል እስቲ አምጣ እስቲ አሌ በል «ይኸን

ለምሳሌ ያህል አልኩህ እንጂ ሁሉን ብቈጥረውማ ሌላ ስንት አለ። ደግሞ የባሰ አለ ገና እንጂ አቶ ኃይሌ የሚባሉት ዘመዴ የሆኑ ሰው ልጃቸውን ሊድሩት ከጨዋ ሰው ጋር ተነጋግረው ጨርሰውለት ልዳርህ ባሉት ጊዜ አሻፈረኝ ብሎና ጉድ አመጣ። አባቱ ይህን ሲሰሙ ጊዜ በድንጋጤ ሁለት ሰንበት ታመሙ በአልጋ ወድቀው በጎ ሲሆኑ ሽማግሌ ሰብስበው ቢያስጠይቁት ጊዜና፥ ኻንዲት ልጅ ጋራ ራሱ ተነጋግሮ ተጫጭተው፥ ሊጋቡ መጨረሻቸውን አይነግራቸውም! እንዲህ ያለ ጉድ እንኳን በኛው በክርስቲያኑ አገርና በአረመኔዎቹ ዘንዳም ተሰምቶ አያውቅ። እግዚአ ካላልን ፈጣሪ መዓቱን አያውርድብንም ብለህ ነው?»

«ይህ ያልከው ሁሉ እውነት ነው» አለ ብርሃኑ «ነገር ግን አጥልቀህ ብታስብበት ጥፋቱ እምብዛም የወጣቶቹ አለመሆኑን ልትረዳ ትችላለህ። ባገራችን ተራራማነትና በውሃ ሙላት ምክንያት ጥንት ከውጨኛው ዓለም ጋራ ይቅርና፥ አውራጃ ካውራጃ ጋር እንኳ በቂ ግንኙነት አልነበረምና ኢትዮጵያ ከሌሎች ክፍለ ዓለማት ጋራ የነበራት ተራክቦ በጣም የተወሰነ ሆኖ የውጭ ስሜት ምንም ያህል አይደርስባትም ነበረ። ስለዚህ ሕዝቡ ካባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣለትን ወግና ባሕል አክብሮ ይዞ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ ዱሮ ይቀለው ነበረ። ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ጨርሶ ተለውጦአል። ለአስተማሪነትና ለማናቸውም ሌላ ተግባር ወደ አገራችን በሚመጡት የውጭ አገር ሰዎች ሳቢያ የሚገባው አዲስ አሳብ ይልቁንም የአገራንን ይዞ በነበረው ወራሪ ምክንያት ብዙ የዱር በመለወጡና በዚሁም ላይ የዛሬ ዘመን ልጆች የሚማሩት በውጭ አገር ቋንቋ በተጻፉ መጻሕፍትና በውስጣቸው በሚገኘው አዲስ አስተያየት ስለሆነ ልጆቹም ከትውልድ አገራቸው ወጥተው ባህሉና ሕጉ ሌላ ወደ ሆነ አገር ሄደው ተምረው ሲመለሱ ቅድም በነገርኩህና በሰላም ልዩ ልዩ ምክንያት የኑሮና የሐሳብ ሁኔታ ይለወጣል። ስለዚህ የዘመኑ ልጆች የአባቶቻቸውን ባህል አክብረው እንዲይዙ ከፈለጋችሁ ይህ ባህል ከዘመኑ እርምጃና ከዕውቀት መራቀቅ ጋራ የሚወዳደር መሆን አለበት። የምታቀርቡላቸውን እንዲቀበሉ ከፈለጋችሁ ይኸው ዘመናዊውን የመንፈስ ፍላጎታቸውን የሚያጠግብ መሆን አለበት።

«እባክህን አሁን ይኸን እንተውና ሌላ ሌላውን እንጫወት። ይህን ጉዳይ እንደሆነ እንዲህ እኔና አንተ ብቻ ተነገግረን የምንፈጅው አይደለም» አለ ይኄይስ።

«ይሁን፥ አንተው ካልክስ ለመሆኑ ከመጣህ ስንት ቀን ሆኖሀል?» ብሎ ጠየቀ ብርሃኑ።

«ወደ መንፈቁ ይጠጋል» አለ ይኄይስ።

«መሰንበትህ ነው ወይስ መመለሻህ ተቃርቦአል?» አለ ብርሃኑ።

«መኼዴ ነው እንጂ አሁንስ የመጣሁት ጉዳይ ተፈጽሞልኛል፥ ያገራችሁ ውሀ የጠጣውን ሰው አይለቅም አሉ» አለ ይኄይስ ሳቅ ይልና።

«ያገራችሁሳ እንዴት ነው? ለመሆኑ ከመሔድህ አስቀድሞ እንገናኝ የለ? አለ ብርሃኑ።



ገጽ ፻፷፪። ምንከፋኝ ጌታው ፤>> ይሉና......

«እንዴታ መጥቼ እሰናበታሁአለሁኝ እንጂ። በል ደህና እደር! ደኅና እደሪ በልልኝ ለወይዘሮ ተዋበች» አለ ይኄይስ

«ቆይ እባክህን ፤ ራትህን በልተህ ትሄዳለህ» አለ ብርሃኑ። ይልቁን ተቀመጥና ራት እስኪቀርብ ድረስ እንጫወት። ይገርማል ፈጣሪ እንዲህ ያገናኘን።»

ይኄይስ ይቀመጥና «ምኑን ተጫወትነው እባክህን የሀገራችን ልብስ ትታችሁ የባዕዱን ፈቅዳችሁአል። ዛሬ አቡነ ዘበሰማያት እንኳ ደግሞ የሚችል ልጅ ያለ አይመስለኝም። በአባቶቻችን ጊዜ ሞያው ተኩስና በፈረስ ሁኖ ጉግስ መጫወት ነበረ። ዛሬ ጊዜና ልብስ አሳምሮ እየተጀነኑ ጢምባሆ ማቡነን ሆኖአል። ተወኝ እባክህን ፤ የከተማን ነገር ኸዚያው ኸባላገሬ ሂጄ ጊዜና ልርሳው እንጂ ምንም ደስ አልልህ ብሎኛል።

«ምነው አለ ብርሃኑ። ከተማችን ምን ወጣው? እግርህን ጭቃ አይንካው ፤ ዕንቅፋት አይጠጋህ ፤ ኩል በመሰለ ባቡር መንገድ ትንጐራደዳለህ ፤ ሲመሽ ደግሞ ከቀን የሚያሳስት ፀሐይ የመሰለ ኤሌክትሪክ ቁልጭ አድርጎ እያበራልህ ወደ ፈለግህበት ትደርሳለህ። ልብሳችን ምን ወጣው ልትል ነው? ቤቶቻችን ቢሆኑም ከዚያ ከጥቀርሻህ አያንሱ። እኛ ደግሞ እንዳንተ በአገራችን ስንኳትን አንውልም በመኪና እንሄዳለን።»

«እውነትህን ነው፤» አለ ይኄይስ በመኺና መሄዳችሁ መቼ ገረመኝ፥ ሰዉ እንደ መኺና መሆን እንጂ።»

## ተፈጸም።

# ስለደራሲው በጥቂቱ

በእምነት የተወለዱት በ፲፱፻ ዓ.ም. ነበር፡፡ በኤርትራ ገጠራማ አካባቢ የተወለዱት በእምነት ከቤተሰቦቻቸው ጋር አዲስ አበባ በመምጣት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በስዊድን የሚሲዮን ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን መከታተል ቢጀምሩም በጣሊያን ወረራ ምክንያት ለማቋረጥ ተገደዋል፡፡ ቀጥሎም ጣሊያን ኮንስላታ ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን ቀጥለው በቤተሰብ ችግር ምክንያት አቋርጠዋል፡፡ ለጣሊያኖች በፎቶግራፍ አንሺነት ተቀጥረው ሰርተዋል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በኃይል ተሸንፎ ከተባረረ በኋላ በፖሊስ ሠራዊት ዋና መሥሪያ ቤት ለስድስት ዓመታት አገልግዋል፡፡ ወደ አሜሪካ በመሄድ ትምህርት መማር ቢጀምሩም በአየር አለመስማማት ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በመከታተል በ፲፱፶፰ ዓ.ም. በቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በማዕረግ ተመረቁ፡፡ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የማስተማር ዕድል አጋጥሟቸው በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ለመሥራት አሜሪካ የሄዱ ቢሆንም ነገር ግን የቤተሰብ ችግር ስላጋጠማቸው ትምህርታቸውን ሳይጨርሱ ለመመለስ ተገደዋል፡፡

ለአማርኛ ቋንቋ ማደግ ይከራከሩ የነበሩት በእምነት የተለያዩ የትርጉም ሥራዎች ቢኖሯቸውም በእጅጉ የሚታወቁት ግን "ልጅነት ተመልሶ አይመጣም" በሚለው ተወዳጅ ድርሰታቸው ነው፡፡

**ምንጭ:** የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ ካሌንደር።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ልጅነት ተመልሶ አይመጣም(ልብወለድ)